
MINISTÈRE
DE L'INTÉRIEUR
*Liberté*
*Égalité*
*Fraternité*

በአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር

በፈረንሣይ የውጪ ዜጎች ዋና መምሪያ



# በፈረንሳይ የጥገኝነት አመልካቾች መመሪያ

gDAሰፕቴምበር 2020

# ማዉጫ


1. የተለያዩ የጥበቃ/ከለላ አይነቶች 5

1.1. ሙሉ የስደተኛ ከለላ 5

1.2. ሰብአዊ ከለላ 5

2. የጥገኝነት አበቱታ ሂደት ዉስጥ መግባትና አበቱታን ማስመዝገብ 6

2.1. ለጥገኝነት አበቱታ አቅራቢዎች የሚሰጥ የመጀመሪያ አቀባበል 6

2.2. የጥገኝነት አበቱታን በጊሼ ኡኒክ ማስመዝገብ 7

2.2.1. ደረጃ አንድ፡- የጥገኝነት አበቱታዎን በፕሬፈክቱር ማስመዝገብ 8

□ የጥገኝነት አበቱታዎን ለመመርመር ኃላፊነት ያለበት አገር መወሰን 8

□ የጥገኝነት አበቱታዎ ምድብ 9

□ ለቃለመጠይቅ የቋንቋ ምርጫ 11

□ የጥገኝነት አመልካች ማስረጃ አሰጣጥ 11

□ ከጥገኝነት አበቱታ ጋር ባልተያያዙ ምክንያቶች የመኖሪያ ፍቃድ ስለመጠይቅ 13

2.2.2. ደረጃ ሁለት : የሚያስፈልግዎትን የOFII ድጋፍና ክትትል መገምገም 13

□ ትኩረት የሚሹ ልዩ ፍላጎቶችዎ በጊሼ ኡኒክ ግንዛቤ ማግኘት 13

□ የድጋፍና የክትትል አቅርቦት 14

2.3. ከጊሼ ኡኒክ ቦኃላ ያለዉ ክትትል 15

3. የጥገኝነት አበቱታ ምርመራ 15

3.1. የስደተኞችና ዜግነት አልባ ስዎች ከለላ ጽ/ቤት(OFPRA)የሚደረግ ምርመራ 15

□ የOFPRA ቅጽ አሞላል 16

□ የአበቱታዎን ፋይል ወደ OFPRA መላክ 16

□ አበቱታ ለOFPRA ስለመቅረቡ ማስረጃ 17

□ በመደበኛ ሂደት ወይም በተፋጠነ ሂደት የአበቱታ ምርመራ 18

□ ከOFPRA ጋር በግል የሚያደርጉት ቃለ መጠይቅ 18

□ የጤና ምርመራ 20

□ የOFPRA ዉሳኔ 20

□ የOFPRA ውሳኔን ይግባኝ ስለመጠየቅ 22

□ የOFPRA ዉሳኔ ማሳወቅን ተከትሎ የመቆየት መብት ስለመቋረጥ 22

3.2. የስደት መብት ብሔራዊ ችሎት (CNDA) ምርመራ 23

□ ይግባኝ ማቅረቢያ የቆይታ ገደብ 23

□ የጥብቅና ዉክልና ስለማግኘት 23

□ ይግባኝ ስለማቅረብ 24

□ የይግባኝ አበቱታ ስለመድረሱ ማስረጃ 26

□ በይግባኝ እገዳ 26

□ የCNDA የችሎት ሂደት 27

□ የCNDA ውሳኔ 28

□ የCNDA ዉሳኔ ተከትሎ የመቆየት መብት ስለመቋረጥ 29

3.3. የተዘጋ አበቱታ ዳግም እንዲከፈት ስለመጠየቅ 29

3.4. በድጋሚ ስለመመርመር 30

4. የጥገኝነት አመልካች ቁሳዊ አቀባበልና መብቶች 31

4.1. የጥገኝነት አመልካች መጠለያ ........ 32
መጠለያ የሚገኝበት ሥፍራ ........ 32
ወደ መጠለያ ሥፍራ ስምሪት ........ 32
የመጠለያ ሥፍራ መግቢያና መልቀቂያ ........ 33
4.2. የጥገኝነት አመልካቾች ድጎማ (ADA) ........ 34
ADAን ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችሉ ሁኔታዎች ........ 34
የጥያቄ አቀራረብ ........ 35
የድጎማው መጠን ........ 35
ክፊያዉ ........ 35
ይግባኝ ስለመጠየቅ ........ 35
4.3. ትምህርት ማግኘት ........ 36
4.4. ሕክምና ማግኘት ........ 37
ሕክምና የት ይሰጣል? ........ 37
የሕክምና ወጪዎን የሚሸፍን የጤና መድን ዋስትና እንዴት ያገኛሉ? ........ 38
4.5. ሥራ-ዓለም ስለመግባት ........ 40

5. የጥገኝነት አበቱታዎ ውድቅ መሆን በመቆየት መብትዎ ላይ ያለው ተጽዕኖ ........ 41
5.1. በOFPRA ወይም በCNDA ዉሳኔ ውድቅ መሆን ........ 41
የOFPRA ውሳኔ ማሳወቅን ተከትሎ የመቆየት መብት መቋረጥ ........ 41
የ CNDA ዉሳኔ በይፋ ችሎት መነበቡን ወይም ማሳወቅን ተከትሎ የመቆየት መብት ስለመቋረጥ ........ 43
5.2. ወደአገር መመለሻ የሚሰጥ ዕርዳታ ........ 44
5.3. በግዳጅ ወደ አገር ስለመመለስ ........ 46

6. የከለላ ተጠቃሚዎች ያላቸው መብቶች ........ 46
6.1. ኑሮ በፈረንሳይ ........ 47
6.2. የቤተሰብ ቆይታ ........ 47
ለቤተስብዎ አባላት የቆይታ/የመኖሪያ መብት/ፍቃድ ........ 47
ቤተሰብ የማሰባሰብ/የማገናኘት መብት ........ 48
6.3. የመቋቋም ጎዳና ........ 49
ከፈረንሳይ የኤምግሬሽንና ዉህደት (መቋቋም) ጽ/ቤት (OFII) ጋር የሚፈረም የሬፑብሊክ ዉህደት(የመቀላቀል) ውል ........ 49
6.4. የማህበራዊ ድጋፎችን የማግኘት መብት ........ 50
መጠለያ ማግኘት ........ 50
ወደ ሥራ ዓለም የመግባት መብት ........ 50
ሕክምና የማግኘት መብት ........ 50
የማሕበራዊና ቤተሰብ ነክ ጥቅማጥቅሞች ........ 51
6.5. የውጭ አገር ጉዞ ........ 52
6.6. ዜግነት የማግኘት መብት ........ 53
6.7. የከለላ መቋረጥ ........ 53

አባሪ ፡ አስፈላጊ አድራሻዎች ........ 55
1. ብሔራዊ አድራሻዎች ........ 56
ተቋማት ........ 56
ዓለማ አቀፍ ድርጅት ........ 56

- ማህበራት ... 56

2. የክልል አድራሻዎች ... 59

- Guichets uniques(ጊሼ ኡኒክ) ... 59
- Préfectures (ፕሬፈክቱር) ... 61
- Directions territoriales de l’Office français de l’immigration et de l’intégration (OFII) ... 66

# 1. የተለያዩ የጥበቃ/ከለላ አይነቶች

የጥገኝነት አበቱታ ካቀረቡና አበቱታዎን የመመርመር ሃላፊነት የፈረንሳይ ከሆነ ፥ አበቱታ የመመርመርና ጥበቃ የማድረግ ስልጣን ባለው የፈረንሳይ የስደተኞችና አገር/ዜግነት-አልባ ሰዎች ጥበቃ ጽ/ቤት (OFPRA) የጥገኝነት ከለላ መብት ብሔራዊ ፍርድ ቤት (CNDA) በሚያደርገዉ ቁጥጥር ስር የሚከናወን ይሆናል።

የጥገኝነት አበቱታዎ ከተጠና ቦኃላ የጥበቃ ባለሥልጣናት የስደት ከለላ እንዲደረግልዎ ሊወስኑ ይችላሉ፥ የሚሰጥዎት ጥበቃም ሙሉ የስደተኛ ከለላ ወይም ሰብአዊ ከለላ ሊሆን ይችላል።

## 1.1. ሙሉ የስደተኛ ከለላ

ሙሉ የስደተኛ ከለላ የሚሰጠው የሚከተሉትን ሶስት ምክንያቶች መሰረት በማድረግ ነዉ፡-

- **የጀነቫ ስምምነት** የስደተኞች ከለላን በተመለከተ ጁላይ 28, 1951 ያስቀመጠውን፥ "የሰደተኛ ከለላ ለማናቸውም ከዘሩ፣ ከሓይማኖቱ፣ ከዜግንቱ፣ ከተወሰነ ማህበራዊ ቡድን አባልነቱ ወይም ከፖለቲካ አመለካከቶቹ ጋር በተያያዘ የመሰቃየት ወይም የመሳደድ ምክኒያታዊ ፍርሃት (...) ሳቢያ ከአገሩ ዉጪ ሁኖ ከፍርሃቱ የተነሳ በገዛ አገሩ ጥበቃ እንዲደረግለት መጠየቅ ለማይቻለው ሰው የሚሰጥ ይሆናል" ፣
- **"ህገመንግስታዊ" ጥገኝነት የሚባለዉና** ከ1946 የህገመንግስት መግቢያ 4ኛው አዲስ መስመር የሚመነጭ፥ "ለማንም ለነጻነት ስል በፈጸመዉ ድርጊት ሳቢያ ማሳደድ ለደረሰበት" የሚሰጥ የስደተኛ ከለላ ነዉ ፣
- **በተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽን (HCR) ውክልና**፥ በተቋቋመበት ሕግ አንቀፅ 6 እና 7 መሠረት በ(HCR) የስደተኛ እውቅና ካገኙ ነው።

## 1.2. ሰብአዊ ከለላ

የሰብአዊ ከለላ ተጠቃሚነት የሚሰጠው፥ ለማንም ሙሉ የስደተኛ ከለላ ለማግኘት መስፈርቱን ላላሟላ ሰዉ፤ ነገር ግን ወደአገሩ ቢመለስ ከሚከተሉት ከባድ ጥቃቶች ውስጥ ለአንዱ ሊጋለጥ እንደሚችል የተረጋገጠና አሳማኝ ስጋት ዉስጥ ላለ ነው ፡

- የሞት ቅጣት ወይም ግድያ፣
- ማሰቃየት(ቶርቸር) ወይም ቅጣት ኢሰብአዊ አያያዝ ወይም ስብዕናዉን ማዋረድ፣
- ሲቪል ከሆነ፥ ከአገር ዉስጥ ወይም ከውጪ በተቀሰቀስና በተስፋፋ ግጪት(ሁከት) ሳቢያ የሰዎች ደህንነት፥ የግል ሁኔታቸዉ ምንም ይሁን ምን ለአደጋ የተጋለጠ በመሆኑ ለግል ሕይወቱ ከፍተኛ ስጋት ዉስጥ ላለ ሰው ነው።

**ዜግነት አልባ**

ዜግነት አልባ ሰዎችን በተመለከተ የሰፕቴምበር 28, 1954 የኒዉዮርክ ስምምነት መሰረት “ማንኛዉም አገር በሕገ-መንግስቱ አተገባበር እንደዜጋው ለማይቀበል ሰው” የዜግነት አልባ ሁናቴ ይሰጠዋል።

ይህ ሁናቴ፥ ከላይ ከተጠቀሱት ሁለቱ የጥበቃ ሁናቴዎች የሚለይ ሁኖ የጥገኝነት አበቱታ ሂደት ውስጥ የሚካተት አይደለም፤ ወደ ፕሬፈክቱር መሄድ ሳያስፈልግዎ በቀጥታ ለOFPRA ካመለከቱ አበቱታዎን ፥ በአስተዳደር ፍ/ቤት ቁጥጥር ሥር መርምሮ የዜግነት አልባ ሁናቴ እንዲሰጥዎ ያደርጋል።

# 2. የጥገኝነት አበቱታ ሂደት ዉስጥ መግባትና አበቱታን ማስመዝገብ

በፈረንሳይ አገር የጥገኝነት አበቱታ ለማስገባት፥ በቅድሚያ ወደ አንድ የስደተኞች የመጀመሪያ አቀባበል መዋቅር (SPADA) በመሄድ የጥገኝነት አበቱታ ሂደት መረጃ ከተሰጠዎ ቦኃላ፤ ባሉበት ክልል የጥገኝነት አመልካቾች ምዝገባ ወደሚመለከተው የጥገኝነት አመልካቾች ዴስክ (*guichet unique*-ጊሼ ኡኒክ) ቀጠሮ እንዲያዝልዎ ማድረግ ያስፈልጋል።

ጊሼ ኡኒክ አበቱታዎን የመመዝገብ፣ በየትኛው ሂደት ውስጥ እንደሚመረመርና፣ ተጋላጭነትዎን በመገምገም በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ በመመርኮዝ ሊደረግልዎ ስለሚገባ ቁሳዊ አቀባበል እንደ (መጠለያና የጥገኝነት አመልካቾች ድጎማ) የመወሰን ኃላፊነት አለበት።

**የጥገኝነት አበቱታዎን ማቅረብ የሚችሉት ምን ሁኔታ ላይ እያሉ ነው ?**

የመኖሪያ ፍቃድን በተመለከተ፥ ቆይታዎ የተፈቀደም ይሁን ያልተፈቀደ፥ የጥገኝነት አበቱታ ማቅረብ ይችላሉ፡ ያለፍቃድ ፈረንሳይ መግባትዎ፥ የጥገኝነት አበቱታዎን ለማስመዝገብ እንቅፋት አይሆንም።

ፈረንሳይ በቪዛ የገቡና የቪዛው የአገልግሎት ጊዜ ያላበቃ እንኳን ቢሆን፥ ከደረሱ ቦኃላ በተቻለ መጠን በአጭር ጊዜ ዉስጥ የጥገኝነት አበቱታዎን ማቅረብ አለብዎት፡ አበቱታዎ ፈረንሳይ ከደረሱ ከ90 ቀናት ቆይታ ቦኃላ ከቀረበ የአቀባበል አቅርቦት ላያገኙ ይችላሉ።

## 2.1. ለጥገኝነት አበቱታ አቅራቢዎች የሚሰጥ የመጀመሪያ አቀባበል

ወደ የስደተኞች መቀበያ ዴስክ (GUDA- *guichet unique pour demandeurs d'asile*) ከመሄድዎ አስቀድመው ወደ አንድ SPADA ለጥገኝነት አመልካቾች የቅድሚያ አቀባበል የሚያደርግ መዋቅር መሄድ አለብዎት፡ እነዚህ የቅድሚያ አቀባበል የሚሰጡት መዋቅራት በመርህ ደረጃ በማህበራት የሚመሩ ሁነው የጥገኝነት አበቱታ ሂደት ዉስጥ መግባት ይችሉ ዘንድ ክትትል ያደርጉልዎታል።

እነዚህ የቅድሚያ አቀባበል ላይ የተሰማሩት የሚከተሉ ተልዕኮዎች አላቸዉ:-

- ጥገኝነትን በተመለከተ ለእርስዎ መረጃ መስጠት፤
- ስለራስዎ ሁኔታ በሚሰጡት መረጃ መሰረት የጥገኝነት አበቱታዎን መመዝገቢያ የኦንላይን ቅጽ መሙላት፤
- ከጊሼ ኡኒክ ቀጠሮ ይዘው የቀጠሮ መጥሪያ ለእርስዎ መስጠት፤ በመጥሪያዉ ላይ የቀጠሮዉ ቀን፣ ቦታና ሳዓት የተገለጸበት ሲሆን ይህንኑን አክብረዉ ጊሼ ኡኒክ መቅረብ ይጠበቅብዎታል፡ በአሰራር ደረጃ፥ ይህ ቀጠሮ ወደ መዋቅሩ ከመጡ አንስቶ በ3 ቀናት ዉስጥ የሚሰጥ ነው፡ የአበቱታ አቅራቢዎች ብዛት ከፍ ያለ ከሆነ እስከ 10 ቀናት ድረስ ሊዘገይ ይችላል፡
- ጊሼ ኡኒክ ይዘው መሄድ ያለብዎትን የመታወቂያ ፎቶግራፍ ማንሳት ናቸው።

  አጠቃላይ ፋይልዎ ወደ ጊሼ ኡኒክ የሚተላለፈው በዲጅታል የመረጃ ልውውጥ (ኮምፒዩተር) አማካይነት ብቻ ይሆናል።

<u>ማሳሰቢያ</u> : በቀጠሮ መጥሪያው ላይ የተጠቀሰውን ቀንና ሳዓት ማክበር አለብዎት፡ ዘግይተው የሚደርሱ ከሆነ ላይስተናገዱና ወደ የጥገኝነት አበቱታ አቅራቢዎች የቅድሚያ አቀባበል መዋቅር ተመልሰው አዲስ ቀጠሮ መያዝ ግድ ሊሆንብዎ ይችላል።

በተጨማርም ፥ ምዝገባዎን በጊሼ ኡኒክ ከፈጸሙ ቦኃላ በጥገኝነት አመልካቾች መጠለያ ማዕከል (CADA) ወይም በተመሳሳይ ቋሚ መጠለያ ቦታ ካላገኙ SPADA እርስዎን 'የማስጠጋት' ኃላፊነት አለበት (ክፍል 2.2.1 « አድራሻዎን እንዴት ያረጋግጣሉ ? »ን ይመልከቱ)።

## 2.2. የጥገኝነት አበቱታን በጊሼ ኡኒክ ማስመዝገብ

አበቱታዎን ለማስመዝገብ በ SPADA በተሰጠዎት የቀጠሮ ጥሪ መሰረት ወደ ጊሼ ኡኒክ (ክፍል 2.1ን ይመልከቱ) መሄድ አለብዎት፡

ጊሼ ኡኒክ፥ አቀባበልዎን ለማረጋገጥ ብቻ ከፕሬፈክቱርና ከፈረንሳይ የስደተኞች እና ዉህደት (ስደተኞችን ማቋቋም) ጽ/ቤት (OFII) የተወከሉ ሰራተኞን የያዘ ነው፡

በተለያዩ የአገርቱ (የፈረንሳይ ሜትሮፖል) ክፍሎች በቁጥር 33 ጊሼ ኡኒኮች ይገኛሉ (ለዝርዝር አባሪን ይመልከቱ)፡

የጊሼ ኡኒክ ምዝገባ ሁለት ደረጃዎችን ያካተተ ነዉ:-

- ደረጃ አንድ፡- የፕሬፈክቱሩ ተወካዮች ፊት ቀርቦ መመዝገብ (2.2.1ን ይመልከቱ) ሲሆን
- ደረጃ ሁለት፡- የOFII ተወካዮች ፊት በመቅረብ ልዩ ሁኔታዎን በመገምገም የሚያሻዎትን አቀባበል (2.2.2ን ይመልከቱ) የሚወስን ይሆናል።

**የጥገኝነት አበቱታዎን ለማስመዝገብ የፖስታ አድራሻ ሊኖርዎት የግድ ይላል ?**

የጥገኝነት አበቱታዎን ለማስመዝገብ የፖስታ አድራሻ አያስፈልግዎትም፡

ነገርግን የጥገኝነት አበቱታ ያቀረቡ መሆንዎን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ወረቀትዎን ለማሳደስ የፖስታ አድራሻ አስፈላጊ ይሆናል (« የጥገኝነት አመልካች ማስረጃ አስጣጥ » ክፍል 2.2.1ን ይመልከቱ) ።

## 2.2.1. ደረጃ አንድ፡- የጥገኝነት አበቱታዎን በፕሬፈክቱር ማስመዝገብ

**ታዳጊ ልጆችዎ ከርስዎ ጋር አሉ ?**

ከታዳጊ ልጆችዎ ጋር ከሆኑ፥ እነሱም እንደጥገኝነት አመልካቾች ተቆጥረው የጥገኝነት አመልካች ማስረጃ ወረቀትዎ ላይ ይመዘገባሉ፡ ሁለቱም ወላጆች ጥገኝነት ጠያቂዎች ከሆኑ፥ ታዳጊዎች የሚመዘገቡት የአበቱታዉ ሂደት እስኪጠናቀቅ ድረስ እንደተጠቃሽ ወላጅ በሚወሰዱት በእናታቸው የጥገኝነት አመልካች ማስረጃ ላይ ነው፡ ይህ ዶክሜንት የቤተሰብዎን ይዘት የሚያረጋግጥ ሳይሆን በመካሄድ ላይ ላለዉ የጥገኝነት አበቱታ ነዉ።

### ■ የጥገኝነት አበቱታዎን ለመመርመር ኃላፊነት ያለበት አገር መወሰን

የፕሬፈክቱሩ ተወካይ፥ ከስደተኞች የቅድሚያ አቀባበል መዋቅር ወደ ጊሼ ኡኒክ የተላለፈዉን ሙሉ መረጃ ካጸደቀ ቦኃላ የጥገኝነት አበቱታዎን የመመርመር ኃላፊነት የፈረንሳይ ይሁን አይሁን ይወስናል፡

ለዚህም ዕድሜዎ 14 ዓመት ወይም በላይ ከሆነ የጣት አሻራ ይወስዳል፡ ከአገርዎ ከወጡ ቦኃላ ያቋረጧቸውን አገራት ለመረዳት ከርስዎ ጋር ቃለመጠይቅ በማድረግ፥ ለምሳሌ በሌላ የሕብረት አገራት ዉስጥ ሊኖርዎት ስለሚችል የዝምድና ትሥሥር ይለያል፡ በነዚህ መረጃዎችና የአውሮፓ ፓርላማና ምክር ቤት የጁን 26, 2013 የዱብሊን III (Dublin III) ተብሎ በሚታወቀው ሕግ ቁ.604/2013 መሰረት፥ የጥገኝነት አበቱታዎን የመመርመር ኃላፊነት የየትኛው አገር መሆኑን ይለያል።

**የዱብሊን III ተፈፃሚነት የሚመለከታቸው አገራት**

28ቱ የአዉሮፓ ሕብረት አባል አገራት፥ ጀርመን፣ ኦስaትሪያ፣ ቤልጂየም፣ ቡልጋሪያ፣ ክሮሽያ፣ ሳይፕረስ፣ *ደንማርክ፣ ስፓኝ፣ ኤስቶኒያ፣ ፊንላድ፣ ፈረንሳይ፣ ግሪክ፣ ሃንጋሪ፣ አየርላንድ፣ ጣልያን፣ ላቲቪያ፣ ሊቱዌኒያ፣ ሉክሳምቡርግ፣ ማልታ፣ ኔዘርላንድስ፣ ፖላንድ፣ ፖርቱጋል፣ የቼክ ሬፑብሊክ፣ ሩማኒያ፣ እንግሊዝ፣ ስሎቫኪያ፣ ስሎቬኒያና ስዊድን እና ሌሎች አራት ተባባሪ አገራት አይስላንድ፣ ኖርዌይ፣ ስዊዘርላንድና ሊችቴንስተይን ናቸው።

* ደንማርክ “ዱብሊን III”ን ባትፈርምም ጁን 15, 1990 የተፈረመውን የዱብሊን ስምምነት ተግባራዊ እያደረገች ነዉ።

**በዚህ መሰረትም፥ የጥገኝነት አበቱታዎን የመመርመር ኃላፊነት የፈረንሳይ ሳይሆን የሌላ የአዉሮፓ ሕብረት አባል አገር ሊሆን ይችላል ለምሳሌ፡-**

- አንድ አባል አገር የሰጠዎት የመቆያ ፈቃድ ካለ ወይም የሰጠዎት ቪዛ ጊዜዉ ያላለቀ ከሆነ፣
- የአንድን አባል አገር የዉጪ ወሰን ያለፍቃድ በየብስ በአየር ወይም በባሕር ማቋረጥዎ ከተረጋገጠ፣
- የአውሮፓ ሕብረት ክልል መጀመሪያ የገቡት በአንድ ቪዛ በማያስፈልግዎት አባል አገርን ወሰን አቋርጠው ከሆነና
- ቀደም ሲል በሌላ አባል አገር የጥገኝነት አበቱታ አቅርበው ከሆነ ነው።

**የጥገኝነት አበቱታዎን መመርመር የሌላ አባል አገር ኃላፊነት ይሆን ?**

“ዱብሊን III” የሚባለው ሂደት ይጀምራል፡ ፕሬፈክቱር ኃላፊነት ያለበት አገር መልሶ እንዲቀበልዎ ለመጠየቅ አስፈላጊውን ሂደት ይጀምራል፡ ኃላፊነቱን ወደተቀበለዉ አገር እስኪተላለፉ ድረስ፥ ፈረንሳይ አገር መቆየት የሚያስችልዎ የጥገኝነት አመልካች ስለመሆንዎ ለአንድ ወር የሚያገለግልና ለየአራት ወራት የሚታደስ ማረጋገጫ ወረቀት ይሰጥዎታል።

ይህም ማስተላለፍ በፕሬፈክቱር የአገልግሎት ክፍል የሚከናወን ሁኖ የመተላለፍዎን ዉሳኔና አተገባበሩን በተመለከተ እርስዎም እንዲያዉቁት ያደርጋሉ፡ የዚህን ውሳኔ ተቃዉሞ ለአስተዳደር ፍ/ቤት ለማቅረብ የ15 ቀናት የቆይታ ገደብ አለዎት።

## ■ የጥገኝነት አበቱታዎ ምድብ

**የጥገኝነት አበቱታዎን የመመርመር ኃላፊነት የፈረንሳይ ከሆነ፥** በመደበኛ ሂደት ወይም በተፋጠነ ሂደት የመመርመር ሥልጣን ባለው OFPRA የሚከናወን ይሆናል፡ በተፋጠነ ሂደት የOFPRA የምርመራ ቆይታ አጭርና በመርህ ደረጃ አሥራ አምስት ቀናት ሲሆን ሁለቱም ህደቶች የሚሰጡት ዋስትና ተመሳሳይ ነዉ።

- **የጥገኝነት አበቱታዎ በተፋጠነ ሂደት እንዲመረመር** በጊሼ ኡኒክ እንደተመዘገበ ወዲያውኑ የሚወሰነዉ የሚከተሉ ሁለት ምክኒያቶች ካሉ ነዉ፡ እነዚህም ፡-
  - ባለዎት ዜግነት ከአንድ የተረጋጋና አስተማማኝ ነዉ ተብሎ ከሚታይ አገር (የእነዚህ አገራት ዝርዝር በፕሬፊክቱር ወይም በOFPRA ኢንቴርነት ድረገጽ ላይ ይገኛል) የመጡ ከሆነና
  - ቀደም ስል ያቀረቡት የጥገኝነት አበቱታ በመጨረሻ ውሳኔ ውድቅ ሁኖ በድጋሚ እንዲታይልዎ የሚጠይቁ ከሆነ ነዉ።

- በሚከተሉት ሁኔታዎችም ፥ የጥገኝነት አበቱታዎ **በጊሼ ኡኒክ ሲመዘገብ ወዲያውኑ በተፋጠነ ሂደት እንዲመረመር** ሊወሰን ይችላል፡-
  - የጣት አሻራዎን ለመስጠት ፍቃደኛ ካልሆኑ፣
  - ባለሥልጣናትን ለማሳሳት ብለዉ የሃሰት ዶክሜንት ካቀረቡ፣ የሃሰት ጥቆማ ካደረጉ ወይም አንዳንድ መረጃዎችን ከደበቁ፣
  - በርካታ አበቱታዎችን በተለያየ ማንነት አቅርበው ከሆነ፣
  - ፈረንሳይ ከገቡ አንስቶ ዘግይተዉ (ከ90 ቀናት ቦኃላ ለGuyane 60 ቀናት) የጥገኝነት አበቱታየዎን ያቀረቡ ከሆነ፣
  - የጥገኝነት አበቱታ ያቀረቡት እርስዎን ለማራቅ እየተወሰደ ያለዉን እርምጃ ለማደናቀፍ ብቻ ከሆነና መቆየትዎ፥ ለሕዝብ ወጥቶ በሰላም መግባት ለመንግስት ደህንነት ከፍተኛ ስጋት ከሆነ ነዉ።

ሆኖም ግን OFPRA በምዝገባ ወቅት በተፋጠነ ሂደት ዉስጥ የተመደቡትን አበቱታዎች፥ ለሕዝብ ወጥቶ በሰላም መግባት ሳቢያ የተመደበ ካልሆነ በስተቀር ወደ መደበኛ ሂደት ሊመልስ ይችላል።

የጥገኝነት አበቱታዎ በተፋጠነ የምርመራ ሂደት ዉስጥ ከተመደበ፥ ይሄንኑን እንዲያውቁት ከተጨማሪ ኮፒዎች ጋር ይሰጥዎታል፡ የዚህኑን አንድ ኮፒ ለOFPRA ከሚያቀርቡት አበቱታዎ ጋር አያይዘዉ መላክ አለብዎት፡ የ OFPRA ዉሳኔን ይግባኝ ካሉም አንዱን ኮፒ ለ CNDA መላክ ይጠበቅብዎታል።

**ልዩ ሁነታ ፡ በአስተዳደራዊ ወይም በመደበኛ ፍ/ቤት የተላለፈ እርስዎን ከአገር የማስወጣት እርምጃ ሂደት ወይም አገር የመልቀቅ ፍርድ አለ ?**

እርስዎን የሚመለከትና የእንዲህ ዓይነት ከአገር የማስወጣት ሂደት መኖር የጥገኝነት አበቱታዎን ማስመዝገብ አያደናቅፍም፡

የጥገኝነት አበቱታዎን የመመርመር ኃላፊነት የፈረንሳይ ከሆነ፥ በመኖሪያዎ የቁም እስር ወይም በአንድ የጥበቃ ማዕከል ዉስጥ መታገት ሊያጋጥምዎ ይችላል፡

ይህ ከሆነ፥ OFPRA አበቱታዎን የቁም እስር ወይም የታገቱበት ማዕከል ከገቡ አንስቶ በአጭር ጊዜ (96 ሳዓታት ዉስጥ) መርምሮ ዉሳኔ ይሰጣል፡ አበቱታዎ ተቀባይነት ካጣ ወይም ዉድቅ ከሆነ የመቆየት መብትዎ ያበቃል፡ በ48 ሳዓታት ዉስጥ እርስዎን ከአገር የማስወጣት ሂደት CNDA ይግባኝዎን መርምሮ ዉሳኔ እስኪሰጥ ድረስ እንዳይተገበር የአስተዳደራዊ ፍ/ቤትን መጠየቅ ይችላሉ (ክፍል 5.1ን ይመልከቱ)።

## ለቃለመጠይቅ የቋንቋ ምርጫ

**የጥገኝነት አበቱታዎን የመመርመር ኃላፊነት የፈረንሳይ ከሆነ** ልዩ ሁኔታ ካለ በስተቀር፥ አበቱታዎን ካቀረቡ ቦኃላ ከOFPRA ጋር ቃለመጠይቅ ያደርጋሉ፡

በመሆኑም አበቱታዎን ሲያስመዘግቡ ከ OFPRA ጋር የሚደረገው ቃለመጠይቅ በምን ቋንቋ መካሄድ እንዳለበት ምርጫዎን ከ115 ቋንቋዎች መካከል መለየት አለብዎት፡ ይህን ምርጫ ቦኃላ መቀየር የማይቻልና የአበቱታዎ የምርመራ ሂደት እስኪጠናቀቅ ድረስ የሚያገለግል ቋንቋ ይሆናል፡

በመረጃ ማስታወቂያዉ ዉስጥ ካሉት ቋንቋዎች ካልመረጡ፥ ቃለመጠይቁ በደንብ በሚረዱት ሌላ ቋንቋ ታግዞ የሚካሄድ ይሆናል፡

በአበቱታዎ ምርመራ ወቅት ለቃለ መጠይቅ የቋንቋ ምርጫ ላይ ተቃዉሞ ካሉዎት፥ ይህን ተቃዉሞዎን ማቅረብ የሚችሉት ለጥገኝነት አበቱታዎ OFPRA የሰጠዉን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኝ ብለው ለCNDA በሚያቀርቡት አበቱታ ሂደት ዉስጥ ብቻ ይሆናል፡

<u>ማሳሰቢያ</u> : ከOFPRA የሚደረገዉ ቃለመጠይቅና የሚወስደዉ ጊዜ በጥቅሉ ከመረዳት የላቀ የቋንቋዉ ዕዉቀት ይጠይቃል፡ በመሆኑም የሚመርጡት ቋንቋ በሚገባ የሚረዱትና እራስዎን በደንብ መግለጽ የሚያስችልዎ መሆን አለበት።

## የጥገኝነት አመልካች ማስረጃ አሰጣጥ

አበቱታዎን የመመርመር ኃላፊነት ያለበት አገርና የጥገኝነት አበቱታዎ የምርመራ ሂደት ምድብ ከተለየ ቦኃላ፥ የጥገኝነት አበቱታ ያቀረቡ ስለመሆንዎ ማስረጃ ይሰጥዎታል፡

**አበቱታዎን የመመርመር ኃላፊነት ያለበት ሌላ አባል አገር ከሆነ፥** ይህ ማረጋገጫ ሰነድ መጀመሪያ ለአንድ ወር አገልግሎት እንዲዉል ይሰጣል፡ ለየአራት ወራት ቆይታ የሚታደስም ነዉ (የጥገኝነት አበቱታዎን ለመመርመር ኃላፊነት ያለበት አገር መወስን (ክፍል 2.2.1ን ይመልከቱ) ፡

**አበቱታዎን የመመርመር ኃላፊነት ያለበት አገር ፈረንሳይ ከሆነ፥** የጥገኝነት አመልካች ስለመሆንዎ የመጀመሪያ ማስረጃ ይሰጥዎታል ፡ ይህ ማስረጃ ፥

- የጥገኝነት አበቱታዎ በመደበኛ ሀዴት የሚታይ ከሆነ ለአስር ወር፥
- የጥገኝነት አበቱታዎ በተፋጠነ ሀዴት የሚታይ ከሆነ ለስድስት ወር የሚያገለግል ነዉ፡

የሚከትሉት ሁኔታዎች ካሉ በስተቀር፥ ፕሬፌክቱር ይህን ማስረጃ ሊከለክልዎት አይችልም፡

- ቀደም ስል ያቀረቡት በድጋሚ ይታይልኝ ጥያቄዎ ዉድቅ ሁኖ በድጋሚ ይታይልኝ ጥያቄ የሚያቀርቡ ከሆነ (ክፍል 3.4ን ይመልከቱ) ፡
- ከአገርዎ ሌላ ወደ ሶስተኛ አገር እንዲተላለፉ የተሰጠዎ የመጨረሻ ዉሳኔ፣ የአውሮፓ ወይም የዓለም አቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤት የመያዝዎ ትዕዛዝ ካለ ነዉ።

በፕሬፌክቱር የተሰጠዎትን የጥገኝነት መጠየቂያ ቅጽ በ21 ቀናት ( 8 ቀናት የድጋሚ ምርመራ ወይም የተዘጋ ፋይል በድጋሚ የመክፈት ጥያቄ ከሆነ (ክፍል 3.3 እና 3.4ን ይመልከቱ) ወደ OFPRA መላክ (ክፍል 3.1 «የOFPRA ምርመራ»ን ይመልከቱ)፡ ፋይልዎ የተሟላ ከሆነ፥ OFPRA መረከቡን በደብዳቤ ያረጋግጣል፡

የጥገኝነት አመልካች ማስረጃ እንዲታደስልዎ በአድራሻዎ ወደሚገኘዉ የፕሬፌክቱር ጽ/ቤት መቅረብ ይጠበቅብዎታል፡ ይህ ማስረጃዎ የጥገኝነት አበቱታዎ በመደበኛም ይሁን በተፋጠነ ህዴት ይመርመር ለየስድስት ወራት የሚታደስ ይሆናል፡

እንዲታደስልዎ ጥያቄ ሲያቀርቡ፥ በፕሬፌክቱር የሚጠየቁትን ተጨማሪ ማስረጃዎች ሁሉ በተለይም ያሉበትን አድራሻ የሚያረጋግጥ ማቅረብ አለብዎት፡ ለ CNDA የይግባኝ አበቱታ ማቅረብዎን ለማረጋገጥ ከፍ/ቤቱ (ክፍል 3.2 « የስደት መብት ብሐራዊ ችሎት (CNDA) ምርመራ »ን ይመልከቱ) የተላከልዎትን ደረሰኝ ማቅረብ አለብዎት።

**አድራሻዎን እንዴት ያረጋግጣሉ ?**

ከጃንዋሪ 1, 2019 ጀምሮ የተመዘገቡ የጥገኝነት አመልካች ከሆኑ አድራሻዎን እንደሚከተለዉ ማረጋገጥ ይችላሉ :-

- በጥገኝነት ጠያቂዎች የመጠለያ ማዕከል ወይም በየትኛውም የጥገኝነት አመልካቾች ቋሚ መጠለያ (የሆቴል ክፍል ሣይጨምር) የሚኖሩ ከሆነ ይህንን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ፣

- የግልዎ በሆነ ወይም በተከራዩት ቤት ወይም የባለቤትዎ/ልጅዎ/ወላጆች ቤት ወይም እነሱ በተከራዩት ቤት የሚኖሩ ከሆነ የዚሁኑ ማስረጃ በማቅረብ፣

- አለበለዚያም በአንድ ዕውቅና ባለው የጥገኝነት አመልካቾ የቅድሚያ አቀባበል ማስጠጋት (ክፍል 2.1 ይመልከቱ) የተደረገልዎ ከሆነ ማስረጃ በማቅረብ ነው፡

ከጃንዋሪ 1, 2019 በፊት የተመዘገቡ የጥገኝነት አበቱታዎች ከላይ በተዘረዘሩት ዉስጥ መጠለል ወይም እንዳስፈላጊነቱ ባስጠጋዎት ሶስተኛ ወገን አድራሻ ልቀጥሉ ይችላሉ።

ይህ የጥገኝነት አመልካች ማስረጃ እዚህ አገር የመቆየት መብትዎ እስከተጠበቀ ድረስ የሚታደስ ነው፡ በመርህ ደረጃ፥ የጥገኝነት አበቱታዎ ተመርምሮ የOFPRA ዉሳኔ እስኪደርስዎ ወይም ይግባኝ ብለዉ ከሆነም የCNDA ዉሳኔ እስኪደርስዎ አለዚያም ዉሳኔዉ በክፍት ችሎት እስኪነበብ የመቆየት መብት አለዎት፡

ሆኖም ግን፥ ቀጥሎ በተጠቀሱት ሁኔታዎች የጥገኝነት አመልካች ማስረጃዎ ሊሰረዝ ወይም ላይታደስ ይችላል፡-

- OFPRA አበቱታዎ ዉድቅ መሆኑን ወይም ተቀባይነት የለለዉ መሆኑን ካሳወቀዎት የመቆየት መብትዎን የሚያቋርጥ ይሆናል (ክፍል 5.1 « በ OFPRA ወይም በ CNDA ውሳኔ ዉድቅ መሆን »ን ይመልከቱ)
- ለ CNDA የይግባኝ ማቅረቢያ የቆይታ ገደብ ያልተከበረ (ክፍል 3.2 « የስደት መብት ብሔራዊ ችሎት (CNDA) ምርመራ »ን ይመልከቱ) ከሆነ ነዉ።

<u>ማሳሰቢያ</u> : የጥገኝነት አመልካች ማስረጃዎ በሌሎች የአውሮፓ ህብረት ሀገሮች ውስጥ በነፃነት መዘዋወር አያስችልዎትም።

### ■ ከጥገኝነት አበቱታ ጋር ባልተያያዙ ምክንያቶች የመኖሪያ ፍቃድ ስለመጠይቅ

የጥገኝነት አበቱታዎን የመመርመር ኃላፊነት የፈረንሳይ ከሆነ፥ ከጥገኝነት አበቱታ ዉጪ የመኖሪያ ፍቃድ የሚጠየቅባቸው ለሎች ሁኔታዎችን በተመለከተ መረጃ ይሰጥዎታል፡

ይህንን በተመለከተ፥ በሚሰጥዎት አንድ የመረጃ ማስታወቂያ ላይ ጥያቄዎን ለማቅረብ ያለው የቆይታ ገደብ ይብራራል፡ ይህ የቆይታ ገደብ ያለበቂ ምክንያት ካለፈ የመቆየት ፍቃድ ጥያቄ ማቅረብ አይቻሎትም።

## 2.2.2. ደረጃ ሁለት : የሚያስፈልግዎትን የOFII ድጋፍና ክትትል መገምገም

### ■ ትኩረት የሚሹ ልዩ ፍላጎቶችዎ በጊሼ ኡኒክ ግንዛቤ ማግኘት

በጊሼ ኡኒክ ቀጠሮዎ፥ የጥገኝነት አበቱታዎን በፕሬፈክቱር ካስመዘገቡ በኃላ ልዩ ሁኔታዎችዎን ከሚደረግልዎ አቀባበል አኳያ ለመገምገም የ OFII ተወካይ በግል ይቀበሉዎታል/ያነጋግሩዎታል፡

ቃለመጠይቁ ሚስጥራዊና የጥገኝነት አበቱታዎን ምክንያት የሚመለከት አይደለም፡ ለየት ያለ አቀባበል የሚያሻዎ መሆኑን ለመገምገም ዝርዝር ጥያቄዎች ይቀርቡልዎታል፡ ሁኔታዎ አስፈላጊ ካደረገዉ፥ የOFII ተወካዩ ግንዛቤ በመስጠት ወደ አመቺ መጠለያ ይመራዎታል፡

የሚቀርቡልዎትን ጥያቄዎች መመለስ አለመመለስ መብትዎ ነዉ፡ ሆኖም ግን፥ ለመመለስ ፍቃደኛ ካልሆኑ ላሉበት ሁኔታ አመቺ ወዳልሆነ መጠለያ ቢመሩ ወይም ሁኔታዎ ለOFPRA ባለመጠቆሙ ለሚፈጠረዉ ሁኔታ አስተዳደሩ ተጠያቂ አይሆንም፡

የሕክምና ዶክሜንት ይዘዉ ፈረንሳይ ደርሰዉ ከሆነ፥ የOFII ተውካዩ ይህንኑ በታሸገ ፋይል ለOFII ሐኪም በመላክ ልዩ አቀባበል ካሻዎት ግንዛቤ ይወስዳል፡ የጤና መታወክ ካለብዎት፥ ወደሚታከሙበት ወይም በአቅራቢያዉ ወደሚገኘው ሆስፒታል ድንገተኛ ክፍል ይመራዎታል፡

የOFII ተወካዩ ተጋላጭነትዎን ከተገነዘበና የእርስዎ ስምምነት ካገኘ ይህንኑን ሁኔታ ለ OFPRA ጥቆማ መስጠት ይችላል፡ የዚህ መረጃ ዓላማ፥ OFPRA አስፈላጊነቱ ከታየዉ የአበቱታዎን ምርመራ ሂደት አመቺ ለማድረግ (ለምሳሌ፥ የአካል ጉዳተኞች መቀበያ በር ወይም የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ አቅርቦት) ያስችለው ዘንድ ነዉ። የማመቻቸቱን አስፈላጊነት የሚገመግመው OFPRA ነው፡

ከተጋላጭነት ጋር የተያያዙ ልዩ ፍላጎቶችዎ፥ የአበቱታዎ ሂደት እስኪጠናቀቅ ድረስ በማሕበራዊ ሰራተኞች፣ በመጠለያ ማዕከላት ወይም ማከናወን በሚገባዎት የአስተዳደርና ማሕበራዊ ህደቶች ላይ ሊረዱዎት ኃላፊነት ባለባቸዉ ማህበራት ግንዛቤ ያገኛል።

## ■ የድጋፍና የክትትል አቅርቦት

በጊሼ ኡኒክ ቀነቀጠሮ፥ OFII ከአቀባበል ጋር የተዛመዱና በጥገኝነት አበቱታ ሳቢያ እዚህ የመቆየት መብትዎ እስከተጠበቀ ድረስ ተጠቃሚ መሆን ስለሚችሉት የድጋፍና ክትትል ኃሳብ ያቀርብልዎታል፡

በጊሼ ኡኒክ OFII የሚስጥዎት ዶክሜንት፥ በቁሳዊ አቀባበል ረገድ የመብትዎን ደረጃ ለመወሰን ይረዳ ዘንድ የቤተሰብዎን ይዘት የሚያረጋግጥ ይሆናል፡ ይህ ሰነድ፥ የጥገኝነት አበቱታዉ በሂደት እያለ ልጅ ከተወለደ ወይም መጥቶ ከወላጆቹ ከተቀላቀለ ቁሳዊ አቀባበል እንደገና ለማስላት እንዲቻል አስፈላጊዉ ለውጥ በOFII ይደረግበታል፡

በዚህ መመሪያ ክፍል አራት እንደተመለከተው የአቀባበል ቁሳዊ ይዘት የሚከተሉትን መብቶች እንዲኖሩዎት የሚያደርግ ነው፡

- እስካሁን መጠለያ ካላገኙና እንዲሰጥዎ ከጠየቁ ወደአንድ የመጠለያ ማዕከል የመመራት (ክፍል 4.1. « የጥገኝነት አመልካች መጠለያ » ን ይመልከቱ)፡

- በሕግ የተወሰነ ካልሆነ በስተቀር፥ የጥገኝነት ጠያቂ ድጎማ (ክፍል 4.2. « የጥገኝነት አመልካቾች ድጎማ (ADA) » ን ይመልከቱ) የማግኘት ነዉ፡

በአንድ ክልል የአቀባብል ጭንቅንቅ ከተስተዋለ፥ OFII በጥገኝነት አበቱታዎ የሂደት ወቅት መቆየት ወዳለብዎ ሌላ ክልል (ክፍል 4.1 « የጥገኝነት አመልካች መጠለያ » ን ይመልከቱ) ሊልክዎት ይችላል።

## 2.3. ከጊሼ ኡኒክ ቦኃላ ያለዉ ክትትል

ከጊሼ ኡኒክ ክንዉን ቦኃላ፥ በተጠለሉበት የጥገኝነት አመልካቾች መጠለያ ማዕከልም (CADA) ይሁን ሌላ ቋሚ የሚባሉ የአስቸኳይ ጊዜ መጠለያ (ሆቴልን ሳይጨምር) ዉስጥ ስለሚደረግልዎት ክትትልና ድጋፍ ኃሳብ ይቀርብልዎታል፡

በነዚህ ቦታዎች ያልተጠለሉ ከሆነ፥ OFII ክትትል ወደሚያደርግልዎ አንድ የጥገኝነት አመልካቾች የቅድሚያ አቀባበል መዋቅር (SPADA) ይመራዎታል (ክፍል 2.1 ይመልክቱ)፡

ይህ ማህበራዊ፣ ሕጋዊና አስተዳደራዊ ክትትሎች ማስፈር ወይም አድራሻ መስጠት (ክፍል 2.2.1 « አድራሻዎን እንዴት ያረጋግጣሉ ? »ን ይመልክቱ) እና አበቱታዎን መመርመር የፈረንሳይ ከሆነም ለOFPRA በሚያቀርቡት የአበቱታዎ ፋይል ጥንቅር ላይ እገዛ ማድርግን ይጨምራል፡

<u>ማሳሰቢያ</u>: አድራሻዎ SPADA ከሆነ እሱ በሚሰጥዎት የጊዜ ሰለዳ ተመላልሰው ደብዳቤዎችን መውሰድ የእርስዎ ኃላፊነት ነዉ።

# 3. የጥገኝነት አበቱታ ምርመራ

የጥገኝነት አበቱታዎን የመመርመር ኃላፊነት የፈረንሳይ ከሆነ፥ አበቱታዎ በስደት መብት ብሔራዊ ችሎት ቁጥጥር ስር በፈረንሳይ የስደተኞችና ዜግነት አልባ ስዎች ከለላ ጽ/ቤት ይመረመራል፡

## 3.1. የስደተኞችና ዜግነት አልባ ስዎች ከለላ ጽ/ቤት(OFPRA)የሚደረግ ምርመራ

አበቱታዎ ሲመዘገብ፥ መርምሮ ዉሳኔ መዉሰድ ይቻለዉ ዘንድ ሞልተዉ ወደ OFPRA መላክ ያለብዎ አንድ ቅጽ በፕሬፌክቱሩ ተሰጥዎታል፡

የጥገኝነት አበቱታ በOFPRA ዉድቅ ከተደረገ የይግባኝ አበቱታ ለCNDA (ክፍል 3.2 « የስደት መብት ብሔራዊ ችሎት ምርመራ » ይመልከቱ) ማቅረብ ይቻላል።

የጥገኝነት አበቱታዎን በሚያቀርቡበት ወቅት የሚያሻዎትን የከለላ ዓይነት (የሙሉ ስደተኛ ወይም ሰብአዊ ከለላ) መሆኑን መለየት አይጠበቅብዎትም፡

የምርመራ ሀደቱ አንድ ሆኖ፥ OFPRA በቅድሚያ አበቱታዎን ከሙሉ ስደተኛ መብት ከለላ አንጻር መርምሮ መስፈርቶቹን የማያሟላ ከሆነ ከሰብአዊ የከለላ መብት አንጻር የሚገመግም ይሆናል።

## ■ የOFPRA ቅጽ አሞላል

**ቅጹ በፈረንሳይኛ ተሞልቶና** ተፈርሞ እንደዚሁም የአግልግሎት ቆይታዉ ካልተገባደደ የጥገኝነት አመልካች ማስረጃ ኮፒ፣ ከሁለት የመታወቂያ ፎቶግራፍና የያዙት የመጓጓዣ ሰነድ ጋር ተያይዞ መላክ ይኖርበታል፡ በተጨማሪም የጥገኝነት አበቱታዎ በተፋጠነ የምርመራ ሂደት ዉስጥ ተመድቦ ከሆነ፥ በምዝገባዉ ቀን ይህን በተመለከተ የተሰጠዎትን ማስረጃ ኮፒ ማያያዝ አለብዎት፡

አበቱታዎን OFPRA ለማስመዝገብ እነዚህ ማስረጃዎች የግድ አስፈላጊ ናቸዉ።

አብረዎት ያሉ ልጆችዎ በግል ለአደጋ ተጋላጭ ሁነው ካሉ፥ ይህም በጥገኝነት ማመልከቻ ቅጽዎ ውስጥ መጠቀስ አለበት፡ ሁለቱም ወላጆች የጥገኝነት አበቱታ አመልካች ከሆኑ፥ የልጆቹ ስጋት በእናታቸዉ ቅጽ ዉስጥ መጠቀስ ይኖርበታል።

በጥገኝነት ማመልከቻዎ ውስጥ የተካተቱት መረጃዎች በሚስጥር የሚያዙና በማናቸዉም ሁኔታ ለትውልድ አገርዎ ባለስልጣናት ተላልፎ የሚሰጡ አይደሉም።

## ■ የአበቱታዎን ፋይል ወደ OFPRA መላክ

ፋይልዎ ከተሞላ በኃላ፥ የጥገኝነት አመልካች ማስረጃ ከተሰጠዎት ቀን አንስቶ **እጅግ ቢዘገይ በ21ኛዉ ቀን** (8ኛዉ ቀን የተዘጋ ፋይል የማስከፈት ጥያቄ ከሆነ ክፍል 3.3— የተዘጋ አበቱታ ዳግም እንዲከፈት ስለመጠየቅ— ወይም የድጋሚ ምርመራ (ክፍል 3.4 « የድጋሚ ምርመራ »)ን ይመልከቱ) **መላክ አለብዎት**፡

በፖስታ ቤት ብቻ ቀጥሎ በተመለከተው አድራሻ መላክ አለብዎት፡-

OFPRA
201, rue Carnot
94 136 FONTENAY-SOUS-BOIS CEDEX

ለምሳሌ ፥ የጥገኝነት አመልካች ማስረጃ ጃንዋሪ 10 ከተሰጠዎ ፣ የጥገኝነት አበቱታ ፋይልዎ እጅግ ቢዘገይ ጃንዋሪ 31 ለOFPRA መላክ አለበት፡ የፖስታ ቤት ማህተም ማስረጃ ይሆናል፡

ፋይልዎን በተመዘገበ ደብዳቤ፥ ላኪው (*Expéditeur*) በሚለዉ ቦታ ላይ ስምዎን በግልጽ በመጻፍ ከተመላሽ ማረጋገጫ ደረሰኝ ጋር እንዲልኩ ይመከራሉ፡

ፋይልዎ ያልተሟላ ከሆነ OFPRA ወደእርስዎ መልሶ በመላክ በ8 (የድጋሚ ወይም የተዘጋ ፋይል መልሶ የማስከፈት ጥያቄ ከሆነ በ4) ቀናት ተጨማሪ ቆይታ ዉስጥ አሟልተዉ መልሰዉ እንዲልኩ ይጠይቃል፡ በተሰጠዎት ተጨማሪ ቆይታ አሟልተው ካልላኩ OFPRA የአበቱታዎን ፋይል ይዘጋል፡ እዚህ የመቆየት መብትዎ ይቋረጣል፡ የጥገኝነት አመልካች ማስረጃዎ አይታደስም፡

የጥገኝነት አበቱታዎ በሂደት ላይ እስካለ ድረስ፥ በማናቸውም ጊዜ ተጨማሪ ማስረጃዎችን ለOFPRA በፖስታ መላክ ይችላሉ፡ ማናቸዉንም ለOFPRA የሚልኳቸዉን መረጃዎች ኮፒና ስለመላክዎ የፖስታ ቤት ማስረጃ እንዲሁም ከOFPRA የሚላኩልዎትን ሁሉ አንድ ላይ መያዝ አለብዎት።

**በሂደት ላይ እያሉ የአድራሻ ለውጥ አደረጉ ?**

ለOFPRA እንደአድራሻ ከነበረዎት ጥግ የተለየ ከመጠለያ ሥፍራዎ ጋር የተያያዘ አድራሻ ከሰጡና ይህን መጠለያ የሚቀይሩ ከሆነ፥ በተቻለ ፍጥነት OFPRAን ማሳወቅ አለብዎት፡ ይህንንም በኦንላይን አገልግሎት በOFPRA ድረገጽ : www.ofpra.gouv.fr « *Démarches en ligne* » ቢያሳዉቁ ይመረጣል፡ OFPRA የሚልካቸዉን ደብዳቤዎች በተለይም ለቃለመጠይቅ ጥሪና የጥገኝነት አበቱታዎን መርምሮ የወሰደዉንም ዉሳኔ የሚልከዉ ለመጨረሻ ጊዜ በተሰጠው አድራሻ ነዉ፡

የግልዎ በሆነ ወይም በተከራዩት ቤት ወይም የባለቤትዎ/ልጅዎ/ወላጆችዎ ቤት ወይም እነሱ በተከራዩት ቤት የሚኖሩና አድራሻ የሚቀይሩ ከሆነ OFIIን ማሳወቅ አለብዎት።

## ■ አበቱታ ለOFPRA ስለመቅረቡ ማስረጃ

ፋይልዎ ተሟልቶ በተገደበዉ ቆይታ ከደረሰ፥ OFPRA የጥገኝነት አበቱታዎ ጽ/ቤቱ መድረሱንና የፋይልዎን ቁጥር በደብዳቤ ያሳዉቃል፡

ይህ ደብዳቤ፥ የጥገኝነት አበቱታዎ ለOFPRA ስለመቅረቡ ማረጋገጫ ኦፊሴላዊ ሰነድ ነው፡

ይህ ሰነድ መጀመሪያ የተሰጠዎትን የጥገኝነት አመልካች ማስረጃ (ክፍል 2.2.1 « የጥገኝነት አመልካች ማስረጃ አሰጣጥ »ን ይመልከቱ) ማሳደስ ያስችልዎታል፡

በአብዛኛው፥ ለቃለመጠይቅ ጥሪም ከዚሁ የአበቱታ ደረሰኝ ጋር አብሮ ይላካል፡ ይህ ከሆነ፥ የቃለመጠይቁ ጥሪ በደብዳቤዉ ጀርባ ላይ ይጻፋል፡ ይህ ካልሆነ፥ የቃለመጠይቁ ጥሪ በሌላ ደብዳቤ ቦኃላ የሚላክ ይሆናል።

## ■ በመደበኛ ሂደት ወይም በተፋጠነ ሂደት የአበቱታ ምርመራ

የጥገኝነት አበቱታዎ በመደበኛ ሂደት ወይም በተፋጠነ ሂደት ይመረመራል፡

በክፍል 2.2.1 (« የጥገኝነት አበቱታዎ ምደባ » ይመልከቱ) እንደተመለከተዉ፥ በተፋጠነ ሂደት የምርመራ ጊዜ 15 ቀናት ብቻ የሚቆይ ቢሆንም የሚያገኙት ዋስትና ከመደበኛዉ የምርመራ ሂደት ጋር ተመሳሳይ ነዉ፡ አበቱታዎ በOFPRA በተፋጠነ ሂደት የሚመረምረዉ በጊሼ ኡኒክ በተመዘገበበት ወቅት በተፋጠነ የምርመራ ሂደት ውስጥ ከተመደበ ነዉ፡ ነገር ግን OFPRA አበቱታዎንና የግል ሁኔታዎን ከተገነዘበ በኃላ አስፈላጊ ሁኖ ከታየዉ፥ እዚህ አገር መቆየትዎ ለማህበራዊ ስርዓት፣ ለህዝብና ለመንግስት ደህንነት ከፍተኛ ስጋት ካልሆነ በስተቀር ወደ መደበኛ ሂደት ማዛወር ይችላል።

በሌላ በኩል፥ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ከተስተዋሉ OFPRA በተፋጠነ ሂደት ሊወስን ይችላል፡-

- OFPRAን ለማሳሳት ሆን ብለዉ ሃሰተኛ ዶክሜንት ካቀረቡ፣ የሃሰት ጥቆማ ከሰጡ ወይም መረጃና ሰነድ ከደበቁ፣
- ሌሎች የጥገኝነት አበቱታዎችን በተለያየ ማንነት ካቀረቡ፣
- ለጥገኝነት አበቱታዎ ያቀረቡት መንስዔ የከለላ አስፈላጊነት ጋር ግንኙነት የለላቸዉ ክሆኑና
- የሚናገሩት ወጥነት ከጎደለዉ፣ የሚቃረን፣ ግልጽ ሃሰት ወይም የማይታመንና ጽ/ቤቱ በአገርዎ ላይ ከሚያዉቀው ጋር የተቃረነ ከሆነ ነው፡

በተፋጠነ ሂደት መመደብዎን መቃወም የሚቻልዎት ለCNDA ይግባኝ በሚያቀርቡት ሂደት ዉስጥ ብቻ ነዉ።

## ■ ከOFPRA ጋር በግል የሚያደርጉት ቃለ መጠይቅ

አበቱታዎ ለOFPRA ከቀረበ ቦኃላ ለቃለመጠይቅ ጥሪ ይደርስዎታል፡

ከዚህ በታች በተጠቀሱት ሁለት ምክንያቶች ብቻ ለቃለመጠይቅ ላይጠሩ ይችልሉ፡-

- በፋይልዎ አካትተዉ የስጡት መረጃዎች ለOFPRA የስደት መብትዎን ማክበር በቂ ከሆኑና
- ከፍላጎትዎ ዉጪ በዘላቂ የሕክምና ሰበብ ለመቅረብና ቃለመጠይቁን ለማካሄድ ካልተቻለዎ ነዉ፡

ለቃለመጠይቅ ጥሪ ከደረሰዎ፥ *Fontenay-sous-Bois* ወደሚገኘዉ የOFPRA ዋና መሥሪያ ቤት መሄድ አለብዎት፡ እዚያ ቃለመጠይቁ የከለላ ኦፊሰር ተብሎ ከሚጠራው የOFPRA ተወካይ ጋር አስፈላጊ ከሆነም OFPRA በሚያቀርበውና እርስዎ በጊሼ ኡኒክ አበቱታዎን ሲያስመዘግቡ የመረጡት ቋንቋ ወይም ሌላ እርስዎ በብቃት የሚችሉት ቋንቋ (ክፍል 2.2.1 « ለቃለመጠይቅ የቋንቋ ምርጫ »ን ይመልከቱ ) አስተርጓሚ በተገኘበት

ይካሄዳል፡ ሆኖም ግን፥ በማናቸዉም ወቅት በፈረንሳይኛ እንዲካሄድ መጠይቅ ይችላሉ፡ በቃለምልልሱ ቋንቋ ላይ ያሉዎትን ተቃዉሞ ማቅረብ የሚቻልዎት ለ CNDA ይግባኝ በሚያቀርቡት ሂደት ዉስጥ ብቻ ነዉ፡

**ለዚህ ቃለመጠይቅ ካልቀረቡ፥ ቀሪ መሆንዎ OFPRA ያቀረቡትን ፋይል መሰረት በማድረግ እንዲወስን ወይም ፋይልዎን እንዲዘጋ ሊያደርግ ይችላል፡** በመሆኑም፥ ዕክል ከገጠመዎት ከ48 ሳዓት በፊት OFPRAን ማሳወቅና መዘግየት ካጋጠመም በጥሪ ደብዳቤው ላይ በተመለከተዉ አድራሻ በኢሜል ማሳወቅ አለብዎት፡

ለቃለ መጠይቁ፥ አስፈላጊ ከመሰለዎት ከጠበቃ ወይም በOFPRA ዕውቅና ካለው ማህበር ተወካይ ጋር መምጣት ይችላሉ፡ ከቃለመጠይቁ በኃላም የራሳቸውን አስተያየት መስጠት ይችላሉ፡ ነገር ግን ጠበቃዉ ወይም የማህበር ተወካይ በቀጠሮ ሳዓት ባይገኙም ቃለ መጠይቁ ለሌላ ጊዜ አይተላለፍም፡ የአካል ጉዳተኛ ከሆኑ፥ ለቃለ መጠይቁ በቋሚነት ከሚከታተልዎ የጤና ባለሙያ ወይም ለአካል ጉዳተኞች ዕገዛ ከሚያደርግ ማህበር ተወካይ ጋር መምጣት ይችላሉ፡

የጥገኝነት አበቱታዎ መንስዔ መግለጽ የሚያስቸግር፥ በተለይም ከጾታዊ ጥቃት ጋር የተያያዘ ሆኖ ቃለመጠይቁ በመረጡት የከለላ ኦፊሰርና ወይም የአስተርጓሚ ጾታ እንዲሆን ከፈለጉ ከቃለ መጠይቁ ቀን አስቀድመው OFPRAን መጠየቅ ይችላሉ፡

**ቃለ መጠይቁ ሚስጥራዊ ነዉ፡** የሰጧቸውን ቃለ ምልልሶች ከእርስዎ ጋር ያካሄዱት የከለላ ኦፊሰር የሚመዘግቡ ሆኖ ይህም እንዲሰጥዎ ከጠየቁ (ለመደበኛ ሂደት) ዉሳኔ ከመሰጠቱ አስቀድሞ በተፋጠነ ሂደት ከሆነ ደግሞ እጅግ ቢዘገይ ከዉሳኔዉ ጋር ይላክልዎታል፡

በተጨማሪም የቃለ ምልልሱ ድምጽ የሚቀዳ ሲሆን የድምጹን ቅጂ ማግኘት የሚችሉት ግን OFPRA አበቱታዎን ዉድቅ ካደረገና እርስዎ ይህንን ዉሳኔ በመቃወም ለይግባኝ በሚያደርጉት ሂደት ዉስጥ ብቻ ነዉ።

**Fontenay-sous-Bois ከሚገኘዉ የOFPRA ዋና መስሪያ ቤት ዉጪ ሌላ ቦታ ቃለ ምልልስ ማድረግ ይችላሉ?**

በጂዮግራፊያዊ ርቀት በተለይም (ከባሕር ማዶ) የሚገኙ ወይም ባሉበት ልዩ ሁኔታ (በሕክምናና ቤተሰብ ጉዳዮች መንቀሳቀስ ዕክል ከሆነብዎ ወይም ጥበቃ ሥር ከሆኑ) ቃለ ምልልሱ በFontenay-sous-Bois ሳይሆን በቴሌኮሚኒከሽ (ኦዲዮቪዥዋል) አማካይነት ይደረጋል፡

ይህ ክሆነና አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም በቃለ ምልልሱ ወቅት የሚገኝ ጠበቃ ወይም የማህበር ተወካይ ከእርስዎ ጎን ይሆናል፡ አስተርጓሚዉ ከከለላ ኦፊሰሩ ጎን ይሆናል፡

በባሕር ማዶ በሚገኙት ክፍለግዛቶች ወይም በአንዳንድ የሜትሮፖል ክልሎች የሚገኙ ከሆነም በቀጥታ ከ OFPRA ተወካይ ጋር Guyane ካሉ በCayenne የ OFPRA ጽ/ቤት ወይም በተካለሉ ለሎች ስፍራዎች በ OFPRA የስምሪት ተልዕኮ ወቅት ቃለ ምልልስ ሊደረግ ይችላል።

## ■ የጤና ምርመራ

OFPRA የጤና ምርመራ እንዲያደርጉ ሊጠይቅዎ ይችላል፡ ይህን ምርመራ ማድረግ አለመቀበልዎ ፋይልዎን ያልተሟላ አያደርግም፡ OFPRA መርምሮ እንዳይወስን አያደርግም፡ ታዳጊ (ለአቅመ አዳም ያልደረሱ) ከሆነና በስምዎ ለግርዛት ተጋላጭነትዎ ምክንያት የጥገኝነት አበቱታ የቀረበ ከሆነ፥ የዚህ ጤና ምርመራ ወጪ በOFPRA ይሸፈናል፡ መርማሪ ሐኪሙ የምርመራ ዉጤቱን በቀጥታ ለOFPRA ይልካል፡ አንዱን ኮፒ ለወላጆችዎ ወይም ለሕጋዊ ተወካይዎ በእጅ ይሰጣል።

## ■ የOFPRA ዉሳኔ

### ✓ ቆይታ

የ OFPRA ዉሳኔ ማግኘት የተለያየ ቆይታ ይጠይቃል፡- ለተፋጠነ ሂደት የ15 ቀናት ቆይታ ሲሆን ለመደበኛ ሂደት የበርካታ ወራት ቆይታ ሊሆን ይችላል፡ የ OFPRA የረዥም ጊዜ ዝምታ የአበቱታዎ መዉደቅን የሚያመለክት አይደለም፡ በ6 ወራት ዉስጥ የማይወስን ከሆነ OFPRA በደብዳቤ ያሳዉቅዎታል፡ ስለሆነም ደብዳቤዎን በየጊዜዉ መፈተሽ አለብዎት።

### ✓ ተስማሚ ውሳኔ (ክፍል 1 « የተለያዩ የጥበቃ ዓይነቶች »ን ይመልከቱ)

ለአበቱታዎ ተስማሚ ዉሳኔ የተሰጠው ከሆነ እርስዎ ወይ፡-

- **ሙሉ ስደተኛ ሆኑ፥** ማለት OFPRA የስደተኛ ሙሉ መብት እውቅና የተደረገልዎ መሆኑን የሚገልጽ ዉሳኔ ይልክልዎታል፡
- **የሰብአዊ ከለላ ተጠቃሚ ሆኑ፥** ማለት OFPRA የሰብአዊ ከለላ እንደተሰጠዎት የሚያረጋግጥና

  በየአስተዳደሩ ከለላ ስለማግኘትዎ እንደማስረጃ የሚቀርብ ደብዳቤ ይልክልዎታል፡

### ✓ ተስማሚ (አመቺ) ያልሆነ ውሳኔ

ለጥገኝነት አበቱታዎ፥ OFPRA ሶስት ዓይነት አመቺ ያልሆኑ ውሳኔዎችን ሊሰጥ ይችላል፡-

- **በውሳኔ ውድቅ ማድረግ**

ይህን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለ CNDA ማመልከት ይችላሉ፤ በጥገኝነት አበቱታ ሳቢያ የእርስዎ እዚህ የመቆየት መብትን በተመለከተ (ክፍል 3.1 « የOFPRA ዉሳኔ ማሳወቅን ተከትሎ የመቆየት መብት ስለመቋረጥ »ን ይመልከቱ) ዝርዝር ሁኔታ ተቀምጧል፡

- ***ያለመቀበል (ተቀባይነት ያጣ) ዉሳኔ*** ከዚህ በታች በተጠቀሱት ምክንያቶች፡-
- በአገልግሎት ላይ ያለና ከአንዱ የአዉሮፓ ሕብረት አባል አገር ያገኙት የስደት ከለላ አለዎት፡
- ተፈጻሚነት ያለዉ ተመልሰዉ መግባት ከሚችሉበት ሶስተኛ አገር የስደት ከለላ አለዎት፡

ይህን ዉሳኔ ተቃዉመው ለCNDA ይግባኝ ማለት ይችላሉ፤ ለCNDA ይግባኝ ቢያቀርቡም፥ በጥገኝነት ጋር የተያያዘ የመቆየት መብትዎ (ክፍል 3.1 « የOFPRA ዉሳኔ ማሳወቅን ተከትሎ የመቆየት መብት ስለመቋረጥ»ን ይመልከቱ) አይራዘምም፡

- ***የአበቱታ ፋይል የመዝጋት ውሳኔ*** ፥ ይህም የሚሆነዉ:-
- የጥገኝነት አበቱታዎን ማንሳትዎን ለOFPRA በቃለምልልስ ወቅት ወይም በደብዳቤ ካሳወቁ፣
- አበቱታዎን በተሰጠው የ21 ቀናት የጊዜ ገደብ ካላቀረቡ ወይም ለቃለምልልስ ካልቀረቡ፣
- ሆን ብለው ለአበቱታዎ ምርመራ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ካልሰጡ፣
- በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ አድራሻዎን ለጽ/ቤቱ ባለመስጠትዎ እርስዎን ማግኘት ካልተቻለና
- አበቱታዎ በጊዜ ኡኒክ ያለበቂ ምክንያት የተመዘገበ ከሆነና የአበቱታ ፋይልዎን ለOFPRA ካልላኩ ነው፡

ይህንን ውሳኔ መቃወም የሚችሉት ወደ CNDA በመሄድ ሳይሆን ወደአስተዳደራዊ ፍ/ቤት በማቅረብ ነው፡ ከዚህ ቦኃላ በስደት ስም እዚህ የመቆየት መብትዎ (ክፍል 3.1 « የOFPRA ዉሳኔ ማሳወቅን ተከትሎ የመቆየት መብት ስለመቋረጥ »ን ይመልከቱ) ይቋረጣል፡ የአበቱታ ፋይልዎ መዘጋት ውሳኔ ከደረሰዎት ቀን አንስቶ በ9 ወራት **ውስጥ አንዴ ፋይልዎ እንደገና እንዲታይልዎ (እንዲከፈት)** (ክፍል 3.3 ይመልከቱ) መጠየቅ ይችላሉ።

✓ **የOFPRA ውሳኔ አላላክ**

**OFPRA** ውሳኔውን በፈረንሳይኛ የሚልክ ሲሆን አበቱታዎ ውድቅ ከሆነ የውሳኔውን ይዘት በአንድ በብቃት ይረዳሉ ተብሎ በሚወሰድ ቋንቋ ትርጉም ከያዘ ዶክሜንት ጭምር ይልካል።

**OFPRA የጥገኝነት አበቱታ ስለማቅረብዎ የሚገልጽ ማስረጃ፣ ለቃለምልልስ የጥሪ ደብዳቤና አበቱታዎን መርምሮ የሚወስደዉን ውሳኔ በዲጂታል የመረጃ ልውውጥ (ያለወረቀት) ሊልክዎ ይችላል ?**

OFPRA የጥገኝነት አበቱታ መቀበሉን የሚገልጽ ማስረጃ፣ ለቃለምልልስ የጥሪ ደብዳቤና አበቱታን መርምሮ የሚወስደዉን ውሳኔ በዲጂታል የመረጃ ልውውጥ (ያለወረቀት) በግል መለያ አካውንት የመላኪያ አሰራር ዘርግቷል፡

ይህ አሰራር እርስዎን በተመለከተ ተፈጻሚ የሚሆን ከሆነ የጥገኝነት አበቱታዎን በሚያስመዘግቡበት ጊዜ ወይም በተራ ቁጥር 2.2.1 በተዘረዘረው መሰረት የዱብሊን ህዴትዎ ሳይሳካ ቀርቶ አበቱታዎን የመመርመር ኃላፊነት ወደ ፈረንሳይ ሲዛወር እንዲያዉቁት ይደረጋል፡ ይህ ከሆነ እንግዲህ አተገባበሩን በተመለከተ መረጃ በጽሁፍ ይሰጥዎታል።

## ■ የOFPRA ውሳኔን ይግባኝ ስለመጠየቅ

የOFPRAን ውሳኔ ከደረሰዎ ቀን አንስቶ በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ ለCNDA (ክፍል 3.2 « የCNDA ምርመራ »ን ይመልከቱ) ይግባኝ ማቅረብ ይችላሉ፣ ለCNDA ይግባኝ ካላቀረቡ ወይም የአንድ ወር የቆይታ ገደቡን አሳልፈው ካቀረቡ የመቆየት መብትዎ ይቋረጣል፣ የጥገኝነት አመልካች ማስረጃዎ ይሰረዛል ወይም አይታደስም፡ ፈረንሳይ መልቀቅ አለብዎት።

የይግባኝ አበቱታን ለCNDA ለማቅረብ የህግ አገልግሎት ዕርዳታ (ጠበቃ) ካስፈለገዎ የOFPRA ውሳኔ እጅዎ ከደረሰበት ቀን አንስቶ በ15 ቀናት ውስጥ መጠየቅ አለብዎት፣ ይህን ከጠየቁ እንግዲህ ለCNDA ይግባኝ የማቅረቡ ቆይታ ገደብ ቆጠራ ተቋርጦ ላቀረቡት የጠበቃ (ክፍል 3.2 « የጠበቃ ዕገዛ »ን ይመልከቱ) ጥያቄ ውሳኔ ከሚሰጥበት ቀን አንስቶ እንደገና ለቀሪው ቆይታ መቁጠር ይጀምራል፡

የCNDA ውሳኔ በመቃወም ለመንግስት የመማክርት ጉባዔ የሰበር አበቱታ ማቅረብ ይቻላል።

## ■ የOFPRA ዉሳኔ ማሳወቅን ተከትሎ የመቆየት መብት ስለመቋረጥ

በመርህ ደረጃ፤ የጥገኝነት አበቱታዎ የምርምራ ሂደት እስኪጠናቀቅ ድረስ የይግባኝ ሂደትን ጨምሮ የመቆየት መብት አሉዎት፡

ሆኖም ግን፤ ቀጥሎ ከተዘረዘሩት የOFPRA ውሳኔዎች መካከል የሚመለከትዎ ካለ የመቆየት መብትዎ ይቋረጣል፥

1. አበቱታዎ ተቀባይነት የለውም፤ ተፈጻሚነት ያለው ከለላ ከአንድ አገር የተሰጠዎ ሁኖ ይህ አገር የአውሮፓ ህብረት አባል ካልሆነ ተመልሰው የመግባት ፍቃድ አሉዎት (ክፍል 3.3 ይመልከቱ)፣
2. የአበቱታዎ ፋይል ተዘግቷል (ክፍል 3.3 ይመልከቱ)፣
3. አበቱታዎ በተፋጠነ የምርመራ ሂደት ውድቅ ሆነ፣ ከተረጋጋ አገር የመጡ በመሆንዎ፣
4. አበቱታዎ በተፋጠነ የምርመራ ሂደት ውሳኔ ውድቅ ሆነ፣ በሃገሪቱ ብሄራዊ ግዛት መቆይትዎ ለህዝቡ ስነአኗኗር ከፍተኛ ስጋት በመሆኑ፣

5. በድጋሚ የምርመራ አበቱታዎ ውድቅ ሆነ፣
6. ለመጀመሪያ ጊዜ በድጋሚ እንዲመረመርልዎ ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት ካጣ፣
7. አበቱታው ተቀባይነት አጣ ወይም ውድቅ ሆነ፤ እርስዎን የሚመለከት ከአገር የማስወጣት ሂደት ወይም የእዚህ አገር አስተዳደራዊ ወይም ህጋዊ ግዛት ክልከላና በቁም እስር ውይም የጥበቃ ማዕከል ውስጥ ነዎት (ክፍል 2.2.1 « በአስተዳደራዊ ወይም በመደበኛ ፍ/ቤት የተላለፈ እርስዎን ከአገር የማስወጣት እርምጃ ሂደት ወይም አገር የመልቀቅ ፍርድ አለ ? »ን ይመልከቱ)፡

በእንደዚህ ሁኔታ፥ የጥገኝነት አመልካች ማስረጃዎ ይሰረዛል ወይም አይታደስም፡ በግዳጅ ከፈረንሳይ ግዛት እንዲለቁ የማድረግ ሂደት ልገጥሞት ይችላል (ክፍል 5 ይመልከቱ)።

## 3.2. የስደት መብት ብሔራዊ ችሎት (CNDA) ምርመራ

### ■ ይግባኝ ማቅረቢያ የቆይታ ገደብ

የOFPRA ውሳኔ እጅዎ ከደረሰበት ቀን አንስቶ በአንድ ወር ቆይታ ውስጥ አበቱታዎን ለCNDA ማቅረብ አለብዎት፣ ይህም፤

- አበቱታዎ በOFPRA ተቀባይነት ካጣ ወይም ውድቅ ከተደረገ CNDA ይህን ውሳኔ በመሰረዝ የከለላ መብት እንዲሰጥዎ መጠየቅ
- የሰብአዊ ከለላ ተጠቃሚ ከሆኑ የስደተኛ ሙሉ መብት እንዲከበርልዎ መጠየቅ ይችላሉ፡ ይህ ከሆነ ከሰብአዊ ከለላ ጋር የተያያዙ ጥቅማጥቅሞችን (ክፍል 6 « ከከለላ ጋር የተያያዙ መብቶች »ን ይመልከቱ) እያገኙ የCNDAን ውሳኔ ይጠባበቃሉ፡ በሌላ በኩል፥ CNDA የስደት ሙሉ መብት የማይሰጥዎ ከሆነ OFPRA የሰጠዎትን የሰብአዊ ከለላ መሰረዝ እይችልም፡

ይህ የይግባኝ አበቱታ የተገደበው የአንድ ወር ቆይታ ሳይገባደድ ለCNDA መቅረብ ይኖርበታል፡ (ለምሳሌ የተላከልዎን ውሳኔ ጃንዋሪ 20 ከፖስታ ቤት የተቀበሉ ከሆነ የይግባኝ አበቱታዎ እጅግ ቢዘገይ ፋብሯሪ 21 እኩለ ሌሊት CNDA መድረስ አለበት)፡ የይግባኝ አበቱታው ለCNDA በአደራ ደብዳቤ ከተመላሽ ደረሰኝ ጭምር፣ በተራ ደብዳቤ ወይም በፋክስ መላክ ይኖርበታል፡ የይግባኝ አበቱታዎ፥ ለጥንቃቄ ተብሎ ከአንድ ወሩ የቆይታ ገደብ በፊት መላክ ወይም በፋክስ ከሆነ የመጨረሻው ቀን እኩለ ሌሊት በፊት መላክ ያስፈልጋል፡ የይግባኝ አበቱታው ይህ ቀነገደብ ከተገባደደ ቦኃላ ለይግባኝ ሰሚው ችሎት ከደረሰ ተቀባይነት አያገኝም፥ ይህ ማለት ለችሎት ሳይቀርብና ሳይመረመር ውድቅ ይሆናል ማለት ነው።

### ■ የጥብቅና ዉክልና ስለማግኘት

የይግባኝ አበቱታዎን ለCNDA በማቅረብና በችሎት ሂደት ላይም እንዲያግዝዎ የጠበቃ አገልግሎት ዕርዳታ መጠየቅ ይቻላል፡ ይህን የህግ አገልግሎት ዕርዳታ ለማግኘት መጠየቅ ይኖርብዎታል፡ የህግ እገልግሎት ዕርዳታ ከተፈቀደልዎ የጠበቃዎ ክፊያ ሙሉ በሙሉ በመንግስት የሚከፈል በመሆኑ ጠበቃው እንዲከፍሉት ሊጠይቅዎት አይችልም፡

የህግ (የጠበቃ) አገልግሎት ዕርዳታ ጥያቄዎን የOFPRA ውሳኔ እጅዎ ከደረሰበት ቀን አንስቶ በ15 ቀናት ውስጥ ለCNDA የህግ እገልግሎት ዕርዳታ ቢሮ በአድራሻ፡

Bureau de l'aide juridictionnelle (BAJ) de la CNDA :

Cour nationale du droit d'asile
35, rue Cuvier
93 558 MONTREUIL-SOUS-BOIS
ማቅረብ አለብዎት፡

በዚህ ሂደት ላይ ሊያግዝዎ ፍቃደኝነት ያሳየ ጠበቃ ካለ ስሙን ለህግ አገልግሎት ዕርዳታ ቢሮ መስጠት የሚችሉ ሲሆን አለዚያም CNDA አንድ ጠበቃ እንዲመድብልዎት መጠየቅ ይችላሉ፡ የህግ አገልግሎት ዕርዳታ ተጠቃሚ ከሆኑ በምንም ረገድ ለጠበቃዎ እሱ ቢጠይቅ እንኳን ክፊያ መፈጸም የለብዎትም፡ የይግባኝ አበቱታዎ በግልጽ ተቀባይነት ከለለው በስተቀር የህግ እገልግሎት ዕርዳታ አይከለከሉም፡

የህግ አገልግሎት ጥያቄዎ በሂደት ላይ እስካለና ይሄው ጥያቄ ውሳኔው እጂዎ ከደረሰበት ቀን አንስቶ በ15 ቀናት ውስጥ የቀረበ ከሆነ፤ የይግባኝ እበቱታዎን ለCNDA የማቅረብ የቀይታ ገደብ ቆጠራ እንዲንጠለጠል ይደረጋል፡ የህግ አገልግሎት ዕርዳታ ቢሮ ለጥያቄዎ ውሳኔ ስጥቶ ሲያሳውቅዎ የቀይታ ገደቡ እንደገና መቁጠር ይጀምራል፡ በዚሁ መሰረት የይግባኝ አበቱታዎን ለCNDA ለማቅረብ አዲስ የቀይታ ገደብ መቁጠር ይጀምራል፤ ይህም የOFPRA ዉሳኔ እጅዎ ከደረሰበት ቀን አንስቶ የህግ አገልግሎት ዕርዳታ እስከጠየቁበት ያሉትን ቀናት ከአንድ ወር ቀንሶ ቀሪው ይግባኝ ለማቅረብ የሚኖርዎት አዲስ የቀይታ ገደብ ይሆናል፡

ይህ ማለት ለምሳሌ፥ OFPRA ውሳኔውን ጃንዋሪ 15 ካሳወቀዎት የህግ አገልግሎት ዕርዳታ ለመጠየቅ የ15 ቀናት የቀይታ ገደብ አሉዎት፣ የህግ አገልግሎት ዕገዛ ጃንዋሪ 20 ማለት የOFPRA ውሳኔ እጅዎ ከደረሰ ከ5 ቀናት በኃላ ካቀረቡ የህግ አግልግሎት ዕርዳታ ቢሮ ለጥያቄዎ ዉሳኔ ከሚሰጥበት ቀን አንስተው የይግባኝ አበቱታዎን ለማቅረብ ቀሪ የ26 ቀናት ቆይታ ይኖርብዎታል።

## ■ ይግባኝ ስለማቅረብ

ቀጥሎ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች መከበር አለባቸው፤

- ከሁሉ አስቀድመው በOFPRA የውድቅ ዉሳኔ ሰነድ ጀርባ ላይ የሚገኘውን ማብራሪያ በደንብ ያንብቡ፣
- የይግባኝ አበቱታው በፈረንሳይኛ በነጭ ወረቀት ላይ ተጽፎ (ለዚህ የሚውል ልዩ ቅጽ የለም) ሙሉ ስም፣ የትውልድ ቀንና ቦታ፣ ዜግነትዎንና አድራሻዎን የያዘ መሆን አለበት፣

- የይግባኝ አበቱታዎ ላይ መፈረም፥ ታዳጊ ከሆኑ ህጋዊ ወክልዎ መፈረም አለበት፣
- የOFPRA ውሳኔ አንድ ኮፒ ከይግባኝ አበቱታዎ ጋር ማያያዝ አለብዎት፣
- የጥገኝነት አበቱታዎ በተፋጠነ ምርመራ ሂደት ውስጥ የተመደበ ከሆነ ይህንኑን ለመግለጽ የጥገኝነት አበቱታዎ የምዝገባ (ክፍል 2.2.1 « የጥገኝነት አበቱታዎ ምድብ »ን ይመልከቱ) ቀን የተሰጠዎትን ማስረጃ ያያይዙ፣
- የይግባኝ አበቱታዎን በምክንያት ይደግፉ፥ ይህ ማለት OFPRA አበቱታዎን ውድቅ ያደረገበት ምክንያት ወይም ሙሉ የስደት ከለላ ሳይሆን ሰብአዊ ከለላ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የወሰነበትን ምክንያት ለምን እንደማይቀበሉ ማብራራት ያስፈልጋል፣
- በእጅዎ የሚገኝ ማንነትዎንና ዜግነትዎን የሚገልጽ ማስረጃ ማያያዝ አለብዎት፣
- ማሚያ ዶክሜንት ማያያዝ፣
- በOFPRA የቃልምልልስ ቋንቋን በተመለከተ ቅሬታ ወይም ተቃውሞ ካሉዎት በይግባኝ አበቱታዎ ውስጥ ማብራራትና በቀጣይ የችሎት ሂደት የትኛው ቋንቋ እንዲሆንልዎ እንደሚፈልጉ ማመልከት አለብዎ፡ ችሎቱ ተቃውሞዎን ከተቀበለና በፈለጉት ቋንቋ አስተርጓሚ ማግኘት ካልቻለ እርስዎ በብቃት ይረዳሉ ተብሎ በሚወሰድ ቋንቋ የሚካሄድ ይሆናል፡
- የይግባኝ አበቱታዎ የመላኩ ማስረጃና የይግባኝ አበቱታዎን ኮፒ መያዝ አለብዎት፣
- የአድራሻ ለውጥ ካለ CNDAን ማሳወቅ አለብዎት፣
- የይግባኝ አበቱታዎ ከተመዘገበ ቦኃላ ፋይልዎ ያለበትን ሁናቴ መረጃ እንዲሰጥዎ መጠየቅ ይችላሉ፡

የዜግነት ማስረጃዎን በተመለከተ፥ የፓስፖርትዎን ወይም የመታወቂያ ወረቀትዎን ኦሪጅናል ይዘው ፎቶኮፒ መላክ ይመረጣል፡ እነዚህን ዶክሜንቶች በእጅዎ መኖር ከCNDA የሚላኩልዎትን የተመዘገቡ ደብዳቤዎች ከፖስታ ቤት ለመረከብ አስፈላጊ ይሆናሉ፡ የችሎቱ ዕለት፥ የዳኞች ሸንጎ ከጠየቀዎት የእነዚህን ዶክሜንቶች ኦሪጂናል ማሳየት ይቻልዎታል፡

የህይወት ታሪክዎን ማስረጃዎች በተመለከተ፥ ኦሪጅናል በመላክ ፎቶኮፒዎቹን መያዝ ይመረጣል፡ እነዚህ ዶክሜንቶች የችሎቱ ዕለት እርስዎ ከጠየቁ ይመለሱልዎታል ወይም ቦኃላ በፖስታ ቤት ይላኩልዎታል፡ ታሪክዎ ነክ ዶክሜንቶች ወደፈረንሳይኛ መተርጎም አለባቸው፡ የፈረንሳይኛ ትርጉሙ ካልተያያዘ CNDA ሊገለገልባቸው አይችልም፡ ቢሆንም ዶክሜንቱ፥ የወሳኝ ኩነት ማስረጃ፣ የፍትህ ተቋማት ወይም በፖሊስ የተሰጡ ካልሆነ በስተቀር የትርጉም ሥራው የሕጋዊ ትርጉም ሥራ ክህሎት ፍቃድ ባለው አስተርጓሚ ተተርጉሞ እንዲቀርብ ግዴታ አይደለም፡ ለክፍት ችሎት እንዲቀርቡ ማዘዣ ቢደርስዎትም፥ ተጨማሪ መረጃዎችን በጥሪ (ማዘዣው) ወረቀቱ ላይ እስከተጠቆመው የጊዜ ገደብ ማቅረብ ይችላሉ።

## ■ የይግባኝ አበቱታ ስለመድረሱ ማስረጃ

የይግባኝ አበቱታዎ ከተመዘገበ ቦኃላ፥ እርስዎ በሰጡት አድራሻ CNDA አንድ « accusé de réception d'un recours » የሚል አርዕስት የያዘ ዶክሜንት ይልክልዎታል፡ ይህ የይግባኝ አበቱታዎ ስለመመዝገቡ ማስረጃ የሚሆን ነው፡

ልዩ ሁኔታ ካለ በስተቀር (ከታች « በይግባኝ እገዳ »ን ይመልከቱ) ይህ ዶክሜንት የጥገኝነት አመልካች ማስረጃዎን ማሳደስ ያስችልዎታል፡ ምክንያቱም CNDA የይግባኝ አበቱታዎን መርምሮ እስኪወስን ድረስ ፈረንሳይ እንዲቆዩ ስለሚፈቀድልዎ ነው።

## ■ በይግባኝ እገዳ

ባጠቃላይ፥ በ OFPRA **የአበቱታዎን ውድቅ መሆን በመቃወም ለ CNDA የይግባኝ አበቱታ የማቅረብ መብት አሉዎት፡ የዚህ ይግባኝ መቅረብ በራሱ እገዳ የሚጥል ነው፡ ይህ ማለት ይግባኝ የማቅረብ የቆይታ ገደብ እስኪያልፍ ድረስ ወይም ይግባኝ ካቀረቡም ችሎቱ መርምሮ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ በቀጣይ ፈረንሳይ የመቆየት መብት አለዎት ማለት ነው፡**

ነገር ግን፥ የጥገኝነት አበቱታዎ የመጨረሻ ውሳኔ ከማግኘቱ በፊት በፈረንሳይ የመቆየት መብትዎ ከተቋረጠ (ክፍል 3.1 « የOFPRA ዉሳኔ ማሳወቅን ተከትሎ የመቆየት መብት ስለመቋረጥ »ን ይመልከቱ) OFPRA አበቱታዎን ውድቅ ማድረጉን ወይም ተቀባይነት ማሳጣቱን ተቃውመው የማቅረብ መብትዎ የተጠበቀ ቢሆንም ይህ ይግባኝ የእገዳ ኃይል ቀጥሎ በተዘረዘሩ ሁኔታዎች አይኖረውም፥ ወይ

- ✓ **ይግባኙ የዕገዳ ኃይል የለውም** እና እርስዎን ከአገር የማራቅ (የማስወጣት) ሂደት ከሚከተሉት ውሳኔዎች መካከል የሚመለከትዎ ካለ ሊተገበር ይችላል፥

1. አበቱታዎ በOFPRA ተቀባይነት አጣ፥ በሌላ አገር የተሰጠዎ የስደት ከለላ ይዘዋል፡ ይህ አገር የአውሮፓ ህብረት አባል ካልሆነ ተመልሰው መግባት ይችላሉ (ክፍል 3.3 ይመልከቱ)፤
2. OFPRA የአበቱታ ፋይልዎን ዘግቷል (ክፍል 3.3 ይመልከቱ)፤
3. OFPRA አበቱታዎን ተቀባይነት አሳጣ፥ ከአገር የማስወጣት ሂደት ለማደናቀፍ ሲባል ብቻ ለመጀመሪያ ጊዜ በድጋሚ እንዲመረመር የቀረበ አበቱታ ከሆነ ነው፡

- ✓ **ወይም ይግባኝ በራሱ ስለማያግድ ፥ ከሚከተሉት ሁኔታዎች እርስዎን የሚመለከት ካለ፣ የይግባኝ አበቱታዎን በCNDA እስኪወስን እርስዎን ከአገር የማስወጣት ሂደት እንዲያግድ ለአስተዳደራዊ ፍ/ቤት ማመልከት ይችላሉ፥** ይህን ማድረግ የሚችሉት ከሚከተሉት ሁኔታዎች መካከል የሚመለከትዎ ካለ ነው፤

1. በተፋጠነ የምርመራ ሂደት፥ በOFPRA ውድቅ የተደረገ አበቱታ፤ የደህንነት ዋስትና ካለበት የተረጋጋ አገር የመጡ በመሆንዎ፣
2. በተፋጠነ የምርመራ ሂደት፣ በOFPRA ውድቅ የተደረገ አበቱታ፣ በብሄራዊ ግዛት መቆየትዎ ለህዝብ ሥነአኗኗር ከፍተኛ ስጋት በመሆኑ፣
3. በOFPRA ውድቅ የተደረገ አበቱታ፣ በድጋሚ እንዲመረመር ለቀረበ ጥያቄ፣
4. በOFPRA ተቀባይነት ያጣ አበቱታ፣ ከአገር የማስወጣት ሂደትን ለማደናቀፍ ብቻ በድጋሚ እንዲመረመር ለቀረበ ጥያቄ፣
5. በOFPRA ተቀባይነት ያጣ ወይም ውድቅ የተደረገ አበቱታ፤ እርስዎን የሚመለከት ከአገር የማስወጣት ወይም የአስተዳደራዊ ወይም ህጋዊ ውሳኔ ምክንያት በቁም እሥር ወይም የጥበቃ ማዕከል ታግተዋል (ክፍል 2.2.1 « በአስተዳደራዊ ወይም በመደበኛ ፍ/ቤት የተላለፈ እርስዎ ከአገር የማስወጣት እርምጃ ሂደት ወይም አገር የመልቀቅ ፍርድ አለ ? »ን ይመልከቱ):

ይህ ውሳኔ እንዲታገድ፥ ከአገር የማስወጣት ሂደት በመቃወም በሚያቀርቡት እበቱታ ውስጥ ወይም ከአገር የማስወጣቱ ውሳኔ የጥገኝነት አበቱታዎ ከመመዝገቡ በፊት በመሆኑ ይግባኝ ማቅረብ የማያግድ ከሆነ፤ በቁም እሥር ወይም የጥበቃ ማዕከል ከገቡበት አንስቶ በ48 ሳዓት ውስጥ መጠየቅ ይችላሉ።

## ■ የCNDA የችሎት ሂደት

ያቀረቡትን ይግባኝ ለመስማት CNDA ወደችሎት እንዲመጡ ጥሪ ይልክልዎታል፡ ይህ ጥሪ በደብዳቤ ከቀነ ቀጠሮ አንድ ወር ቀድሞ የሚደርስዎ ይሆናል፡የይግባኝ አበቱታዎ በተፋጠነ ሂደት የሚመረመር ከሆነ ከችሎት ቀጠሮ 15 ቀናት ቀድሞ ይደርስዎታል፡

ይህ እንዳለ ሆኖ፥ የይግባኝ አበቱታዎ ፍሬሃሳብ የOFPRAን ውሳኔ ጥያቄ ውስጥ የማያስገባ ከሆነ ፋይልዎ በአንድ ራፖርተር ከተጠና ቦኃላ CNDA እርስዎን ሳይጠራ አበቱታዎን በማዘዣ ውሳኔ ውድቅ ሊያደርግ ይችላል፡

እንዳስፈላጊነቱ ችሎቱ ወይ፥

- Montreuil ወይም Palais de justice (Ile de la Cité) በሚገኘው የCNDA ሥፍራ (ህንጻ) ይካሄዳል፣
- ወይንም በቪዴዮ አማካይነት በፍትህ ሚኒስቴር ህንጻ ሥፍራዎች ይካሄዳል፡ የቪዴዮ ችሎት ሚስጥራዊነትና የጥራት ዋስትና አስተማማኝ ነው።

### ✓ የዳኞች ሸንጎ

የCNDA ችሎት የዳኞች ሸንጎን አንድ ዳኛ በፕሬዝዳንትነት ይመራል፡ በተለይም አንድ ከተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽን (HCR) የተመደበ ስብዕናና ብቃት ያለው ሰው ያካተተ ነው፡ ዳኞቹ ባቀረቡት ይግባኝ

ላይ ውሳኔ የሚሰጡት ፥ አንድ ራፖርተር የእርስዎን ማብራሪያና ካሉዎትም የጠበቃዎንም መሰረት በማድረግ የጥገኝነት አበቱታዎን ወደ ውሳኔ ኃሳብ ሳያደላ በንባብ የሚያቀርበውን ትንተና ካዳመጡ ቦኃላ ነዉ፡

የጽ/ቤቱ (የOFPRA) ውሳኔ በተፋጠነ የምርመራ ሂደት ወይም አበቱታዎን ተቀባይነት ያሳጣ ከሆነ፤ የይግባኝ ጥያቄዎ በአንድ የCNDA ዳኛ ብቻ ተመርምሮ በአምስት ሳምንታት ቆይታ ውስጥ ውሳኔ ያገኛል፡

ችሎቱ በራሱ ተነሳሽነት ወይም እርስዎ በሚያቀርቡት ጥያቄ በዳኞች ሸንጎ እንዲወሰን፣ በተፋጠነ የምርመራ ሂደት የማይመደብ፣ ተቀባይነት የማያጣና ከበድ ያለ ጉድለት አለው ማለት ይችላል።

✓ **ትርጉም**

የጥገኝነት እበቱታዎ ሲመዘገብ በመረጡት ቋንቋ አስተርጓሚ በCNDA አማካይነት ይቀርባል (« ለOFPRA ቃለምልልስ የቋንቋ ምርጫ »ን ይመልከቱ)፡.ይህ ካልተገኘ ወይም ካልተቻለ በአንድ በብቃት በሚገባዎ ቋንቋ የሚካሄድ ይሆናል፡ OFPRA በነበረው የትርጉም አገልግሎት ላይ ተቃዉሞ ካለዎትም ለCNDA በሚያቀርቡት ይግባኝዎ ውስጥ ማካተት ይችላሉ፡ የችሎት ውሎዎ በቴሌኮሚንክሽን ኦዲዮቭዧል (ድምጽና ምስል) ከሆነ፥ አንድ አስተርጓሚ እርስዎ በሚገኙበት ክፍል ከጎንዎ ይሆናል፡ አስተርጓሚው በአካል ከእርስዎ ጎን መሆን ካልተቻለ በችሎቱ ወገን ይህ አስተርጓሚ መኖሩ ሳይረጋገጥ ችሎቱ ይግባኝዎን መስማት አይቀጥልም።

✓ **በችሎት ስለመገኘትዎ**

በችሎት እንዲገኙ በጥብቅ ይመከራሉ፡ የማይገኙ ወይም የሚያረፍዱ ከሆነ፥ CNDAን በቅድሚያ ማሳወቅ አለብዎት፡ ለችሎት ቀጠሮ መቅረብ የማይቻልዎት ከሆነ ይህ የሆነበት ምክንያት በጽሁፍ በማቅረብ ለሌላ ቀን እንዲተላለፍ መጠየቅ ይችላሉ፡ ሌላ ቀጠሮ መጠየቅ መብት ባለመሆኑ የCNDA የዳኞች ሸንጎ ፕሬዝዳንት ያቀረቡትን ምክንያት ብቻውን አጥንቶ ካመነበት ሌላ ቀጠሮ እንዲሰጥዎ ይወስናል።

✓ **የችሎቱ ሂደት ለሕዝብ ይፋ/ክፍት ስለመሆኑ**

የችሎቱ ህደት ለሕዝብ ይፋ ሁኖ የሚካሄድ ነው፡ ሆኖም ግን በዝግ ችሎት ማለት ለህዝብ ዝግ እንዲሆን ለፕሬዝዳንት ዳኛው ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ፡ የፕሬዝዳንት ዳኛም በዝግ ችሎት እንዲሆን ይፈቅዳል፣ የዳኞች ሸንጎ ፕሬዝዳንትም በራሱ ተነሳሽነት ዝግ እንዲሆን ሊወስን ይችላል።

## ■ የCNDA ውሳኔ

ለይግባኝ አበቱታዎ ውሳኔ ከሰጠ ቦኃላ CNDA ይህንን ውሳኔ በተመዘገበ ደብዳቤ ከተመላሽ ደረሰኝ « *en lettre recommandé avec avis de réception* » ጭምር ለእርስዎ ይላካል፡

ውሳኔው በፈረንሳይኛ የተጻፈ ሁኖ እርስዎ በብቃት በሚረዱት አንድ ቋንቋ የውሳኔውን መንፈስ ሊረዱ የሚያስችልዎ ትርጉም ከያዘ ዶክሜንት ጋር ተያይዞ ይደርስዎታል፡

CNDA በዉሳኔው፥

- የOFPRA የውድቅ ውሳኔ በመሰረዝ የስደት ሙሉ መብት ወይም የሰብአዊ ከለላ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሊወስን ይችላል፣ ይህ ከሆነ፥ OFPRA ከሁለቱ ከለላዎች አንዱን ወስኖልዎት ቢሆን ኖሮ ሊያገኙ የሚቻልዎት ተመሳሳይ መብቶች በዚህ ዉሳኔም ይከበሩልዎታል፡
- OFPRA የወሰነውን ሰብአዊ ከለላ ተጠቃሚነትዎን በመሰረዝ የስደት ሙሉ መብት ሊያከብርልዎ ይችላል፣
- የOFPRA የውድቅ ውሳኔ ማጽደቅና የይግባኝ ጥያቄዎን ውድቅ ማድረግ እና
- አልፎ አልፎ፥ የየOFPRA ውሳኔ በመሰረዝ እራሱ መልሶ እንዲመረምር ሊጠይቀው ይችላል፡

የCNDAን ውሳኔ በመቃወም በመንግስት የመማክርት ጉባዔ የሰበር አበቱታ ማቅረብ ይቻላል፡ ይህም አበቱታዎን በአጠቃላይ በድጋሚ የሚመረምር ሳይሆን አንዳንድ ህግነክ ጉዳዮችን ብቻ የሚያይ ነው፡ ይህ አሰራር ረዥምና ብቃት ያለው ጠበቃ የሚፈልግ ነው፡ የህግ እገልግሎት ዕርዳታ መጠየቅ ይቻላል፡ ይህን አበቱታ ማቅረብ በፈረንሳይ ቆይታዎ እንዲራዘም የማይፈቅድ በመሆኑ ወደአገርዎ በግዳጅ የመመለስ ሂደትን አያቆምም፡ ይህንን ሂደት በተመለከተ አንድን ማህበር ወይም ጠበቃን ቢያማክሩ ይመረጣል።

## ■ የCNDA ዉሳኔ ተከትሎ የመቆየት መብት ስለመቋረጥ

*የመቆየት መብትዎ፥*

- የCNDA ውሳኔ በይፋ ችሎት ከተነበበት አንስቶ ይቋረጣል፥ ለማናቸውም ውሳኔ እንዲያውቁት ይላክልዎታል፡

- የCNDA ውሳኔ በማዘዣ (እርስዎ ወደ ችሎቱ ሳይጠሩ) የተወሰደ ከሆነ ውሳኔው እጅዎ ከደረሰዎት ቀን አንስቶ የሚቋረጥ ይሆናል፡

የመቆየት መብትዎ እንዳበቃ ፈረንሳይ መልቀቅ አለብዎት፡ ተገደው ፈረንሳይን እንዲለቁ የማድረግም እርምጃ ሊኖር (ክፍል 5ን ይመልከቱ) ይችላል።

# 3.3. የተዘጋ አበቱታ ዳግም እንዲከፈት ስለመጠየቅ

የጥገኝነት የአበቱታ ፋይልዎ ምርመራ ተዘግቶ ከሆነ (ክፍል 3.1 « የOFPRA ውሳኔ » ን ይመልከቱ) ለአንዴ ብቻ ከተዘጋበት ቀን አንስቶ በ9 ወራት ቆይታ ውስጥ ተመልሶ እንዲታይልዎ መጠየቅ ይችላሉ፡ ይህንንም ለማድረግ ወደ የጥገኝነት አመልካቾች የመጀመሪያ አቀባበል መዋቅር (SPADA) በመመለስ ከዚያም በጊሼ ኡኒክ (ክፍል 2ን ይመልከቱ) እንደአዲስ መመዝገብ አለብዎት፡

ከዚሁ በፕሬፈክቱር የምዝገባ ቀን አንስቶ በ8 ቀናት ቆይታ ውስጥ ለOFPRA የፋይልዎን መልሶ መክፈት ጥያቄ ማቅረብ አለብዎት፡ በዚሁ መሰረት ፋይልዎ ሲዘጋ ከነበረበት ደረጃ አንስቶ እንዲመረመር ያደርጋል፡

የመልሶ መክፈት ጥያቄዎ በተገደበው የ9 ወር ቆይታ ውስጥ የቀረበ ከሆነ ተጨማሪ ቆይታ ተጠቃሚ ሁነው የጥገኝነት አመልካች ማስረጃ ይሰጥዎታል፡

የ9 ወራት ቆይታ የተገባደደ ከሆነ ያቀረቡት የመልሶ መክፈት ጥያቄ እንደ በድጋሚ የመመርመር ጥያቄ (ክፍል 3.4. « በድጋሚ ስለመመርመር »ን ይመልከቱ) ተደርጎ ይታያል።

## 3.4. በድጋሚ ስለመመርመር

CNDA አበቱታዎን ውድቅ ካደረገ ወይም የOFPRA ዉሳኔ እጅዎ ከደረሰበት ቀን አንስቶ በተገደበው የአንድ ወር ቆይታ ይግባኝ ያላቀረቡ ከሆነና አዲስ የመከራከሪያ ፍሬሃሳብ ካለዎት ብቻ አበቱታዎ በድጋሚ እንዲመረመርልዎ መጠየቅ ይችላሉ፡ ይህም ማለት ፍሬኃሳቡ፤

- ከCNDA ውሳኔ ቦኃላም ይሁን በፊት የነበረ ነገር ግን እርስዎ ያወቁት ቦኃላ ከሆነና
- በተፈጥሮው ወደአገርዎ ቢመለሱ በግል ይደርስብኛል ያሉትን የማሳደድ ፍራቻና ሊገጥሙዎት የሚችሉ አደጋዎችን የሚገልጽ ከሆነ ነው፡

አንድን ማህበር ወይም ጠበቃ ማማከር ይችላሉ፡

የድጋሚ መመርመር ጥያቄ ማቅረብ የሚችሉት ፥ ወደ የጥገኝነት አመልካቾች የመጀመሪያ አቀባበል መዋቅር (SPADA) በመመለስ ከዚያም በጊሼ ኡኒክ (ክፍል 2ን ይመልከቱ) እንደአዲስ በመመዝገብ ነው፡

ከዚህ የምዝገባ ቀን አንስቶ በ8 ቀናት ቆይታ ውስጥ ለOFPRA የድጋሚ መመርመር ጥያቄ ማቅረብ አለብዎት፡ አበቱታዎ የተሟላ ካልሆነ ጽ/ቤቱ በ4 ቀናት ቆይታ ውስጥ እንዲያሟሉ ይጠይቅዎታል፡

ቀጥሎም፥ OFPRA የአበቱታዎን ተቀባይነት በተመለከተ የቅድሚያ ግምገማ በማድረግ ከቀረበበት ቀን አንስቶ በ8 ቀናት ውስጥ ይወስናል፡ በዚህ የምርመራ ወቅት እርስዎን መጥራት የግድ አስፈላጊ አይሆንም፡
ይህ ምርመራ እንደተገባደደ፥ ያቀረቧቸው ምክንያቶች ከለላ የማግኘት ዕድልዎን ከፍ የማያደርጉ ከሆነ OFPRA አበቱታዎ ተቀባይነት የለውም የሚል ውሳኔ ይሰጣል፡

OFPRA አበቱታዎ ተቀባይነት አለው የሚል ውሳኔ ከሰጠ ልዩ ትዕዛዝ ከለለ በስተቀር በተፋጠነ የምርመራ ሂደት በጥልቀት የሚመረመር ይሆናል፡

በድጋሚ የመመርመር አበቱታን በተመለከተ OFPRA የሚሰጠውን ዉሳኔ በመቃወም ለCNDA (ክፍል 3.2ን ይመልከቱ) ይግባኝ ማቅረብ ይቻላል።

**በድጋሚ የመመርመር አበቱታዎ ወቅት የመቆየት መብት ተጠቃሚ ነዎት ?**

በድጋሚ የመመርመር ጥያቄው ለመጀመሪያ ጊዜ (ክፍል 3.1 « የ OFPRA ውሳኔ ማሳወቅን ተከትሎ የመቆየት መብት ስለመቋረጥ » ን ይመልከቱ) የቀረበ ከሆነ፥

- ፕሬፌክቱሩ አበቱታዎ የቀረበው ከአገር የማስወጣት/የማራቅ ሂደትን ለማስተጓገል ብቻ ነው ካለና OFPRA አበቱታዎ ተቀባይነት የለውም የሚል ውሳኔ ከሰጠ የመቆየት መብትዎ የOFPRA ውሳኔ እጅዎ ከደረሰበት ቀን አንስቶ ይቋረጣል፡ እርስዎን የማስወጣት ሂደት ሊተገበር ይችላል፡

- OFPRA አበቱታዎ ተቀባይነት የለውም የሚል ውሳኔ ከሰጠ ነገር ግን ፕሬፌክቱሩ አበቱታዎ የቀረበው ከአገር የማስወጣት ሂደትን ለማስተጓገል አይደለም የሚል አረዳድ ካለው የOFPRA ውሳኔ እጅዎ ከደረሰበት ቀን አንስቶ የመቆየት መብትዎ ይቋረጣል፡ ሆኖም CNDA አበቱታዎን መርምሮ እስኪወስን እርስዎን የማስወጣት ሂደት እንዲገታ ለአስተዳደራዊ ፍርድ/ቤት ማመልከት ይችላሉ፡

- OFPRA ለአበቱታዎ ተቀብሎ በድጋሚ መርምሮም በውሳኔ ውድቅ ካደረገ የOFPRA ውሳኔ እጅዎ ከደረሰበት ቀን አንስቶ የመቆየት መብትዎ ይቋረጣል፡ ሆኖም CNDA አበቱታዎን መርምሮ እስኪወስን እርስዎን የማስወጣት ሂደት እንዲገታ ለአስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ማመልከት ይችላሉ፡

በድጋሚ የመመርመር ጥያቄዎ ለሁለተኛ ጊዜ የቀረበ ከሆነ የመቆየት መብት አይከበርልዎትም፡ እርስዎን የማስወጣት ሂደት የOFPRA ውሳኔንም ሳይጠብቅ ሊተገበር ይችላል።

# 4. የጥገኝነት አመልካች ቁሳዊ አቀባበልና መብቶች

እንደጥገኝነት አመልካች ቀጥሎ የተዘረዘሩት ቁሳዊ የአቀባበል መብቶች ይኖሩዎታል፥

- በአንድ የጥገኝነት አመልካቾች መጠለያ ማዕከል (CADA) ወይም በአስቸኳይ ሁኔታ የመጠለያ ማዕከል ውስጥ ለእርስዎ አስፈላጊ ከሆነም ለቤተሰብዎ አባል መጠለያ ማግኘት (ክፍል 4.1 ይመልከቱ) ፣
- ለጥገኝነት አመልካቾች የሚሰጥ ወርሃዊ የኑሮ ድጎማ (ADA) መጠኑ ከቤተሰብዎ ጥንቅር የሚዛመድ (ክፍል 4.2ን ይመልከቱ) ማግኘት ነው፡

በጊሼ ኡኒክ አበቱታዎን ሲያስመዘግቡ የአቀባበል አቅርቦትና ቁሳዊ ሁኔታ በOFII ማብራሪያ ይሰጥዎታል (ክፍል 2.2.2ን ይመልከቱ)፡

በተጨማሪም ማካሄድ በሚገባዎ የአስተዳደርና ማህበራዊ ህደቶች፣ የጥገኝነት አበቱታ ፋይልዎ ሂደትና በትምህርት፣ በሕክምናና በሥራ መስክ ማግኘት በሚገባዎ ማህበራዊ ጥቅማጥቅሞች በማስፈጸም ረገድ ዕገዛና ክትትል (ክፍል 4.3 እስከ 4.5ን ይመልከቱ) ያገኛሉ።

## 4.1. የጥገኝነት አመልካች መጠለያ

### ■ መጠለያ የሚገኝበት ሥፍራ

የመጠለያ ሥፍራዎች የጥገኝነት አመልካቾች መቀበያ ማዕከል (CADA) እና አጠቃላይ የጥገኝነት አመልካቾች የአስቸኳይ ሁኔታ መጠለያ (HUDA) ናቸው፡ የመጠለያ ማዕከላት በመንግስት ወጪ የሚሰሩ ናቸው፡ ባመዛኙ የሚተዳደሩት በማህበራት ነዉ፡

ወደ 100 000 የሚጠጉ ለጥገኝነት አመልካቾች አገልግሎት የሚውሉ የመጠለያ ቦታዎች በመላው የፈረንሳይ ክልሎች በአፓርታማ፣ በጋራ ማዕከል ወይም በሆቴል ክፍሎች መልክ ተሰራጭተው ይገኛሉ፡ በCADA ወይም በHUDA ከተጠለሉ፥ ከሌላ ሰው ወይም ቤተሰብ በጋራ የሚገለገሉባቸው ክፍሎች እንደ (ምግብ ማብሰያ ሥፍራ፣ መታጠቢያና መጸዳጃ) ሊኖሩ ይችላሉ፡

የመጠለያ አገልግሎት ተጠቃሚ ለመሆን ጊዜው ያላለቀ የጥገኝነት አመልካች ማስረጃ መያዝ አለብዎት፡

በCADA ወይም በHUDA ከተጠለሉ በአስተዳደራዊና ህግነክ (በጥገኝነት አበቱታ፣ ጤናና ማህበራዊ) እንዲሁም ማግኘት በሚገባዎ የማህበራዊ ድጋፍ ጥቅሞች በተለይም (ሕክምና፣ የልጆች ትምህርትና በመሳሰሉት) ህደቶች የሚያስፈልግዎትን ክትትል ያገኛሉ፡ በሆቴል ክፍል ውስጥ የተጠለሉ ከሆነ፥ ይህን ክትትል በየጥገኝነት አመልካቾች የቅድሚያ አቀባባል መዋቅር (SPADA) አማካይነት ያገኛሉ።

### ■ ወደ መጠለያ ሥፍራ ስምሪት

የአቀባበል ቁሳዊ ሁኔታ (CMA)፥ መጠለያና የጥገኝነት አመልካቾች ድጎማ (ADA)ን ያካተተ አቅርቦት መሆኑን በጊሼ ኡኒክ (GUDA) የጥገኝነት አበቱታዎን ሲያዝመዘግቡ በOFII ተገልጾልዎታል፡

- **ይህን የአቀባበል አቅርቦት ኃሳብ ካልተቀበሉ** ፥ CMA ተጠቃሚ እንዲሆኑ በድጋሚ ኃሳብ አይቀርብልዎትም፣
- **የአቀባበል አቅርቦቱን ኃሳብ ከተቀበሉ** ፥ OFII የጥገኝነት አበቱታዎን ምድብና ክፍት መጠለያ (በዞን፣ በክልልና በአገር ደረጃ) ግምት ውስጥ በማስገባት ወደ አንዱ CADA ወይም HUDA እንዲጠለሉ ይመራዎታል፡

የጥገኝነት አበቱታዎን ካስመዘገቡበት ክልል ውጪ ወደሚገኝ መጠለያ ሊመሩ ይችሉ ይሆናል፡ ይህን ሥምሪት ካልተቀበሉም የሚሰጠውን የጥገኝነት አመልካቾች ድጎማ አያገኙም፤ የሌላ መጠለያ ኃሳብም አይቀርብልዎትም፡ ክፍት መጠለያ ካልተገኘልዎ OFII እርስዎን ወደ SPADA በመምራት መጠለያ እንዲያፈላልግልዎ ያደርጋል።

## የመጠለያ ሥፍራ መግቢያና መልቀቂያ

**በCADA ወይም በHUDA ከተጠለሉ** የጥገኝነት አበቱታዎ ሂደት (OFPRA እና CNDA) እስኪጠናቀቅ ድረስ እዚያው መቆየት ይችላሉ፡

ሆኖም ግን አንዳንዴ የOFPRA ዉሳኔ አበቱታን ውድቅ ካደረገ የሚጠለሉት ለተወሰነ ቆይታ ብቻ ይሆናል (ክፍል 4.2. « ቁሳዊ የአቀባበል አቅርቦት የሚቋረጥብዎ መቼ ነው ? »ን ይመልከቱ)፡

**የስደት ሙሉ መብት ካገኙ ወይም የሰብአዊ ከለላ ተጠቃሚ ከሆኑ** (በመጨረሻ የOFPRA ወይም የCNDA- ተስማሚ ውሳኔ) ፥ የተጠለሉበትን CADA ወይም HUDA በሶስት ወራት ቆይታ-አንዴ ብቻ የሚታደስ- ውስጥ መልቀቅ አለብዎት፡ ከዚህ ጊዜ በመተላለፍ በመጠለያው የሚቆዩ ከሆነ በፍ/ቤት የውሳኔ ሂደት እንዲለቁ ይደረጋል፡

የጥገኝነት አበቱታዎ ውድቅ ከተደረገ (በመጨረሻ የOFPRA ወይም የCNDA- ተስማሚ ያልሆነ ውሳኔ) የCADA ወይም የHUDA መጠለያን ፥ የመቆየት መብትዎ ሲያበቃ (ክፍል 3.1 እና 3.2 « የመቆየት መብት ስለመቋረጥ »ን ይመልከቱ) የሕግ ውሳኔ ካለ በስተቀር መልቀቅ አልብዎት፡

**ከዚህ ጊዜ በመተላለፍ በመጠለያው የሚቆዩ ከሆነ** በግዳጅ እንዲለቁ የማድረግ እርምጃ ይወሰዳል፡ ይህ ከሆነ፥ የክልሉ ፕሬፌ ወይም የCADAው ወይም የHUDAው ሥራአስኪያጅ መጠለያውን እንዲለቁ በጽሁፍ ያዙዎታል፡ ይህንንም አክብረው ካልለቀቁ፥ የክልሉ ፕሬፌ ወይም የCADAው ወይም የHUDAው ሥራአስኪያጅ እርስዎን በግዳጅ የማስወጣት የማዘዣ ውሳኔ እንዲሰጥ ለአስተዳደራዊ ፍ/ቤት ሊያመለክቱ ይችላሉ፡ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የፖሊስ ኃይል ወይም በጀንዳርም *(ጠብመንጃ ባነገቱ ሕግ አስከባሪዎች)* እንዲለቁ ይደረጋል።

## 4.2. የጥገኝነት አመልካቾች ድጎማ (ADA)

የጥገኝነት አመልካቾች ድጎማ (ADA) ማነጅሜንት በOFII የሚሰራ ሆኖ ክፊያ የሚፈጸመው በአገልግሎትና ክፊያ ኤጀንሲ አማካይነት ነው፡

ይህ ድጎማ የሚከፈልዎት OFII በሚስጥዎት ካርድ አማካይነት ይሆናል፡ እንደጥገኝነት አመልካች የመቆየት መብት እስካለዎት ወይም የጥገኝነት አበቱታዎን ለመመርመር ኃላፊነት ወዳለበት ሌላ አገር እስኪተላልፉ ድረስ የሚሰጥ ድጎማ ነው።

### ■ ADAን ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችሉ ሁኔታዎች

የጥገኝነት አመልካቾች ድጎማ ተጠቃሚ የሚሆኑት፥

1- የጥገኝነት አመልካች መሆንዎ ማስረጃ ካለዎት፤

2- ዕድሜዎ ቢያንስ 18 ዓመት ከሞላና

3- የጥገኝነት አመልካች ከሆኑ፥ በጊሼ ኡኒክ የቀጠሮ ቀን በOFII የቀረበልዎትን የአቀባበል ቁሳዊ አቅርቦት ኃሳብ የተቀበሉ ከሆነ ነው።

**የጥገኝነት አመልካች ማስረጃ ሳልይዝ የአቀባበል ቁሳዊ አቅርቦት ተጠቃሚ መሆን እችላለሁ ?**

ከፍ ብሎ እንደተመለከተው፥ የአቀባበል ቁሳዊ አቅርቦት ተጠቃሚ ለመሆን በአገልግሎት ላይ ያለ የጥገኝነት አመልካች ማስረጃ መያዝ ያስፈልጋል፡

ሆኖም ግን፤ የጥገኝነት አበቱታዎ የድጋሚ ምርመራ ጥያቄ ያቀረቡ ከሆነ ወይም ያለበቂ ምክንያት (ክፍል 2.2.1 « የጥገኝነት አበቱታዎ ምደባ »ን ይመልከቱ) በጣም ዘግይተው ጥገኝነት ያመለከቱ ከሆነ የጥገኝነት አመልካች ማስረጃ እያለዎትም የአቀባበል ቁሳዊ አቅርቦት ሊከለከሉ ይችላሉ፡

በሌላ በኩል OFPRA በተፋጠነ የምርመራ ሂደት አበቱታቸው (ከተረጋጋ አገር የመጡ፣ ለህዝብ ሰላምና ደህንነት አስጊ መሆን ሳቢያ) ውድቅ የሆነባቸውና የጥገኝነት አመልካች ማስረጃቸው የተሰረዘባቸው ወይም ያልታደሰላቸው ከOFPRA ውሳኔ ቦኃላ ለCNDA የይግባኝ አበቱታ ካቀረቡ የአስተዳደራዊ ወይም የስደት ፍ/ቤት መርምሮ እስኪወስን ድረስ የአቀባበል ቁሳዊ አቅርቦት ተጠቃሚ ይሆናሉ፡ በእንዲህ አይነቱ ሁኔታ አቅርቦቱ ሊዛመድ ወይም በቁሳዊ ዕርዳታ ሊተካ እንደሚችል መታወቅ አለበት።

## የጥያቄ አቀራረብ

የጥገኝነት አመልካች ከሆኑ፥ በጊሼ ኡኒክ የጥገኝነት አበቱታዎን ካስመዘገቡ ቦኃላ በOFII የቀረበልዎትን የአቀባበል ቁሳዊ አቅርቦት ኃሳብ ከተቀብሉ የጥገኝነት አመልካቾች ድጎማ የማግኘት መብትዎ ተፈጻሚ መሆን ይጀምራል፡

የጥገኝነት አመልካቾች ድጎማ ክፊያ የሚጀምረው፥ የጥገኝነት አበቱታዎ ከተመዘገበ ቦኃላና እጅግ ቢዘገይ ከምዝገባው ቀን እንስቶ በ21 ቀናት ውስጥ ለ OFPRA ካቀረቡ ነው።

## የድጎማው መጠን

የጥገኝነት አመልካች ድጎማ ተጠቃሚ የሚሆኑት የወር ገቢዎ ከ RSA (*ሬቨኑ-ደ-ሶሊዳሪቴ-አክትቭ*) ያነሰ ከሆነ ነው፡
የዚህ ድጎማ መጠን የሚሰላው የቤተሰብዎን ቁጥር፣ ገቢዎንና የመጠለያ ዘይቤዎን መሰረት ባደረገ ልኬት ነው።

## ክፊያዉ

የጥገኝነት አመልካች ድጎማ የመጀመሪያ ክፊያ የሚደረገው የጥገኝነት አበቱታዎ ለOFPRA ከቀረበ ቦኃላ ነው፡ የሞባይል ስልክ ቁጥርዎን ለ OFII ሰጥተው ከሆነ ድጎማው ካርድዎ ላይ መላኩን በአጭር መለዕክት (SMS) እንዲደርስዎ ይደረጋል፡

ይህ ድጎማ በፈረንሳይ መቆየትዎ እስከሚያበቃበት (ክፍል 3.1 እና 3.2 « መቆየት መብት ስለሚቋረጥ »ን ይመልከቱ ) ወር መጨረሻ ድረስ የሚከፈልዎ ይሆናል፡

ይህ ድጎማ የጥገኝነትዎ አበቱታ የመጨረሻ ውሳኔ በእጅዎ ከደረሰበት ወር ቀጥሎ ባለው ወር መገባደጃ ላይ የሚቋረጥ ይሆናል።

## ይግባኝ ስለመጠየቅ

በማናቸውም ረገድ በመቆየት መብትዎ፣ በቤቱሰብ ወይም ገቢዎን በተመለከተ ለውጥ ከተከሰተ OFIIን ማሳወቅ ይኖርበታል፡ ADAን በተመለከተ የተሰጠ ውሳኔ ላይ ተቃውሞ ካሉዎት በድጋሚ እንዲታይልዎ ለOFII ማመልከት የሚችሉ ሲሆን አከራካር ጉዳዮችን የመዳኘት ሥልጣን የአስተዳደራዊ ፍ/ቤት ነው።

**ቁሳዊ የአቀባበል አቅርቦት የሚቋረጥብዎ መቼ ነው ?**

*የቁሳዊ አቀባበል አቅርቦት ተጠቃሚነትዎ በጥገኝነት አበቱታ ሳቢያ የመቆየት መብትዎ በሚያበቃበት ወር መጨረሻ የሚቋረጥ ይሆናል፡*

OFPRA በተፋጠነ የምርመራ ሂደት አበቱታቸውን (ከተረጋጋ አገር የመጣ፣ ለህዝብ ሰላምና ደህንነት አስጊ) በማለት ውድቅ የሆነባቸውና የመቆየት መብታቸው የOFPRAን ውሳኔ ተከትሎ የተቋረጠባቸው፥ ፍ/ቤት ያቀረቡትን ከአገር የማስወጣት ዉሳኔ ዕገዳ አበቱታ ውድቅ እስኪያደርግ ወይም CNDA መርምሮ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ የአቀባበል ቁሳዊ አቅርቦቱ ተጠቃሚ ይሆናሉ (ክፍል 5.1 ይመልከቱ)፡

*ሙሉ የስደት መብት ወይም የሰብአዊ ከለላ ተጠቃሚነት ከተከበረልዎ ውሳኔው እጅዎ ከደረሰበት ወር ቀጥሎ ባለው ወር መጨረሻ የሚቋረጥ ይሆናል፡*

*ሆኖም ግን የአቀባበል ቁሳዊ አቅርቦቱ የሚከተሉት ሁኔታዎች ከተከሰቱ ይቋረጣል፤*

- ያለበቂ ምክንያት መጠለያዎን ከለቀቁ፣
-በባለሥልጣናት ሲጠሩ የመገኘት ግዴታዎን ካልተወጡ፣ የሚጠየቁትን መረጃዎች ካልሰጡ ወይም ለጥገኝነት አበቱታዎ ቃለምልልስ ካልቀረቡ፣
- OFII ሌላ ክልል ወደሚገኝ መጠለያ ወይም SPADA መርቶዎት በተወሰነው የአምስት ቀናት ቆይታ ካልደረሱ፣
- OFII ወደሌላ ክልል መርቶዎት ከዚያም ያለ OFII ፍቃድ ከለቀቁ፣
- የገቢዎን ትክክለኛ መጠን ከደበቁ፣
- ቤተሰብዎን በተመለከተ ሃሰት መረጃ ከሰጡ፣
- የተለያየ የጥገኝነት አበቱታ በተለያየ ማንነት ካቀረቡና
- ጠባይዎ ሁከት የሚጋብዝ ሆኖ የመጠለያ ማዕክልዎን የውስጠ ደንብ ክፉኛ ከጣሱ ነው፡

*ይህ እርምጃ ከመወሰዱ አስቀድሞ እርስዎም በጉዳዩ ላይ ኃሳብዎን በጽሁፍ ለOFII እንዲያቀርቡ ይደረጋል፡ ገቢዎን የመደበቅ፣ ቤተሰብዎን በተመለከተ የተሳሳተ መረጃ መስጠትና የተለያየ አበቱታ በተለያየ ማንነት ማቅረብን የሚመለከት ከሆነ ያላግባብ የተከፈለዎ ትርፍ ገንዘብ እንዲመልሱ ሊጠየቁ ይችላሉ።*

## 4.3. ትምህርት ማግኘት

*የጥገኝነት አመልካቾች ልጆች ት/ቤት የመግባት ዕድል የሃገሪቱ ዜጎች ልጆች ካላቸው ዕድል ጋር ተመሳሳይ ነው፡*

በትምህርት ኮድ (አንቀጽ L. 111-2) እንደተደነገገው *« ሁሉም ህጻናት፤ የወላጆች ጥረት የተሟላ ይሆን ዘንድ በመማሪያ ተቋም በትምህርት የመኮትኮት መብት አላቸው »*፡ እንደዚሁም ከፍ ብሎ በተጠቀሰው ኮድ አንቀጽ

L. 131-1 « ከ6 እስከ 16 ዓመት ላሉት የፈረንሳይና የውጭ ዜጎች የሁለቱም ፆታ ህጻናት መማር ግዴታ ነው » በሚል የተደነገገውን ማወቅ አስፈላጊ ይሆናል፡

የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ምዝገባ በከተማ አስተዳደር (ሜሪ-) የሚፈጸም ነው፡ ለሚያስመዝግቡት ልጅ የእርስዎን ማንነት/ትሥሥር፣ አድራሻዎንና የልጁን የክትባት ማስረጃዎች መያዝ ያስፈልጋል፡

የሁለተኛ ደረጃ (ኮሌጅ ወይም ሊሴ-) ምዝገባ ከሚኖሩበት አድራሻ በቅርብ በሚገኝ ተቋም ይፈጸማል፡

የአስተዳደርዊ፣ ህጋዊና ማህበራዊ ክትትል ድጋፍ የሚሰጡዎ የመጠለያዎ ተቋም ይሁን የOFII ስምምነት (ክፍል 2.1ን ይመልከቱ) ያለው የመጀመሪያ አቀባበል መዋቅር (SPADA) እነዚህን ህደቶች መፈጸም ይችሉ ዘንድ ዕገዛ ያደርግልዎታል።

## 4.4. ሕክምና ማግኘት

### ■ ሕክምና የት ይሰጣል?

- **የሕክምና ባለሙያ ጋ (ከሆስፒታል ዉጪ)**

ለማናቸውም የጤና ችግር ወደ አንድ የጠቅላላ ሕክምና-« généraliste » ዶክተር በመሄድ ካማከሩ ምርመራ ካደረገልዎ ቦኃላ ተገቢ መድኃኒት ያዝልዎታል፡ ተጨማሪ ምርመራ ወይም የሕክምና ዕርዳታ የሚያስፈልግዎ ከሆነ ወደ እስፔሻሊስት ወይም ወደ ረዳት የሕክምና ባለሚያዎች (ነርስ፣ የፊዚዮቴራፒስት ማሳጅ) ይመራዎታል፣

- **በፋርማሲ፥** መድኃኒት ለመግዛት ወይም ምክር ለመጠየቅ፣

- **በሆስፒታል፥** ለድንገተኛ ዕርዳታ ወይም በቀጠሮ ለአንዳንድ ምርመራና እስፔሻሊስት በማማከር ያገኛሉ፡

**እነዚህ የሕክምና አገልግሎቶች የሚሰጡት በክፊያ ነው፡ ሆኖም ግን ክፊያው ባለዎት የሕክምና ዋስትና** (የሚቀጥለውን ፓራግራፍ ይመልከቱ) የሚሸፈን ሊሆን ይችላል፡

**የሕክምና ዋስትና ማስረጃ እስኪያገኙ ድረስ ቀጥሎ በተዘረዘሩት ተቋማት ያለክፊያ መታከም ይችላሉ ፥**

- ለጠቅላላ ሕክምና፥
  - ወደቋሚ የሕክምና አገልግሎት መስጫ (PASS) መሄድ፡ ሐኪም ያዩዎታል፣ መድኃኒትም በነፃ ይሰጥዎታል፡ ይህም ባብዛኛው ሆስፒታል ውስጥ የሚገኝ አገልግሎት ነው፡
  - ብቃት ወዳላቸው አንዳንድ ማህበራት እንደ*Médecins de Monde*, le COMEDE እና የመሳሰሉት ህደውም የጠቅላላ ሕክምና ዶክተር ማማከርን፣ የጥርስ ሕክምናና እስፔሻሊስት (የማህጸን፣ የዓይን፣ የስነልቦናና የመሳሰሉ) ዕርዳታ በነፃ ማግኘት ይችላሉ፡

- ለየት ላሉ የጤና ችግሮች፥
    - ለእርግዝና ክትትልና ከ6 ዓመት በታች ለሆኑ ህፃናት ክትባት ወደ *PMI* (እናቶችና ህፃናት የጤና እንክብካቤ) ማዕከል መሄድ፣
    - ለቲቢ ምርምራ፥ ወደ CLAT (የቲቢ መከላከያ ማዕከል) መሄድ፣
    - ለኤይድስ፣ ሄፓታይቴስ እና በግብረሥጋ ግንኙነት ለሚተላለፉ በሽታዎች ምርመራ ወደ የነፃ መረጃ አገልግሎት ማዕከል (CeGIDD) መሄድ፣
    - ለወሊድ (እርግዝና) መከላከያ ዜይበ ፥ ወደ ቤተሰብ ዕቀዳ ማዕከል (CPEF) መሄድ፣
    - ከሱስ ጋር ለተያያዘ ወደ የሱሰኝነት ክትትል፣ መከላከያና ሕክምና ማዕከል (CSAPA) መሄድ ነው፡

**እነዚህ የሚገኙበትን ሥፍራ ለማወቅ ከመጀመሪያ አቀባበል መዋቅርዎ፣ ከመጠለያ ማዕከልዎ ወይም በአካባቢው ከሚገኝ ሆስፒታል ጠይቀው ማግኘት የሚችሉ ሲሆን በ** [http ://annuairesante.ameli.fr](http://annuairesante.ameli.fr) ድረገጽ ላይም ያገኛሉ፡

**ለድንገተኛ ወይም አጣዳፊ የጤና ችግር** 15 ወይም 112 የስልክ ቁጥር ይደውሉ፡ መደወል ካልቻሉ በቅርብ ወደሚገኘው ሆስፒታል የድንገተኛ ሕሙማን ክፍል መሄድ ይችላሉ።

## ■ የሕክምና ወጪዎን የሚሸፍን የጤና መድን ዋስትና እንዴት ያገኛሉ?

**ፈረንሳይ አገር የሕክምና አገልግሎት የሚገኘው በክፊያ ቢሆንም የሕክምና ውጪዎን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የሚሸፍን የሕክምና ዋስትና ማግኘት ይችላሉ፡**

ይህም አጠቃላይ የሕክምና ዋስትና (*protection universelle maladie -PUMa*) ሽፋን መስጠት እንዲሁም ከገቢ ጋር የተያያዘ የማሟያ እገዛ (*Complémentaire santé solidaire -CSS*) የሚመለከት ነዉ፡

ይህም አጠቃላይ የሕክምና ወጪ፥ መነጽር፣ የጥርስ ሕክምና (የሃሰት ጥርሶች)፣ ወዘተ የሚሸፍን ይሆናል፡ በተጨማሪም የሕክምና አገልግሎት የቅድሚያ ክፊያ እንዳይጠበቅብዎና የትራንስፖርት አገልግሎትም በቅናሽ እን ዲያገኙ ያደርጋል፡

**ይህንን ተጠቃሚ ለመሆን በአድራሻዎ ወደሚገኘው የጤና መድን ፈንድ (*caisse primaire d'assurance maladie- CPAM*) ቀጥሎ በተዘረዘረዉ መሰረት ማመልከት ይኖርብዎታል፥**

- **ለታዳጊ ልጆችዎ የጥገኝነት አበቱታዎ እንደተመዘገበ ወዲያዉኑ፥ የ « ሕክምና ኢንሹራንስ መብት መክፈቻ » እና የ«ማሟያ እገዛ» ቅጾችን በመሙላት የጥገኝነት አመልካች ስለመሆንዎ ከሚገልጽ ማስረጃ በማያያዝ ማቅረብ አለብዎት ፣**

- **ለራስዎ (እና ለባለቤትዎ) በፈረንሳይ ከሶስት ወራት ቆይታ ቦኋላ፥** በድጋሚ ቅጾቹን በመሙላት የጥገኝነት አመልካች መሆንዎ ከሚገልጸዉ ማስረጃ በተጨማሪ ከሶስት ወራት በላይ ፈረንሳይ ዉስጥ የቆዩ መሆኑንዎን የሚገልጽ ማስረጃ ለምሳሌ እንደ ፥

  በመጠለያ ማዕከል ከሶስት ወራት በላይ መጠለልን የሚገልጽ በማዕከሉ የተሰጠ ማስረጃ፣ በአድራሻ አገልግሎት ከሶስት ወራት በላይ ቆይታ ያለዉ ማስረጃ፣ ከሶስት ወራት በላይ የቆየ የጥገኝነት አመልካች ማስረጃ፣ ማንኛዉም ከየቅድሚያ የስደተኞች አቀባበል ተቋም (SPADA) ከሶስት ወራት በፊት የተሰጠ ዶክሜንት፣ ሶስተኛ ወገን ያስጠለለ ከሆነ ማስጠለል የጀመረበትን ቀንና አድራሻ በመግለጽ በራሱ ስም ከሶስት ወራት ወዲህ የተመዘገበ (የቤት ኪራይ፣ የመብራት ፍጆታ የክፊያ ደረሰኝ፣ ወዘተርፌ)ጋር አያይዘዉ ማቅረብ ይጠበቅብዎታል፡

አስቸኳይ ሕክምና የሚያስፈልገው ልጅ ወይም ልጆች ካሉዎት፥ የዚህን አስፈላጊነት ማስረጃ ካቀረቡ የጤና መድን ሽፋን ጥያቄዎ በተፋጠነ ህዴት እንዲጠና ያደርጋል፡

በዚህ ሂደት ላይ ከቅድሚያ አቀባበል መዋቅርዎ (SPADA) ፣ ከመጠለያ ማዕከልዎ (CADA, HUDAና ከመሳሰሉት) ወይም ከሆስፒታል ማሕበራዊ አገልግሎት ዕገዛ ጠይቀዉ ማግኘት ይችላሉ፡

**የጤና መድን ሽፋን የሚያገኙት የሚጠይቁበትን ፋይል ለCPAM ካስገቡበት ቀን አንስቶ ይሆናል፡**

**በመሆኑም ለልጆችዎ (የጥገኝነት አበቱታዎን እንዳስመዘገቡ ወዲያዉኑ) ለራስዎና ለበለቤትዎ ደግሞ በፈረንሳይ የሶስት ወራት ቆይታዎ እንደተገባደደ ወዲያዉኑ ጥያቄዎን ማስገባት ይጠበቅብዎታል፡**

ሕክምና ሲያስፈልግዎ ወደሀኪም፣ ወደሆስፒታል ወይም ወደፋርማሲ ይዘዉ መሄድ የሚኖርብዎት ማስረጃ የሰጥዎታል፡

ይሄዉም ከጤና መድን ፈንድ በቅጽዎ ላይ በተመለከተው አድራሻ ይላክልዎታል፤ በቅጹ ላይ የመጠላያ አድራሻዎን ማመልከት አለብዎት፡

የጤና መድን ዋስትናዎ የጥገኝነት አበቱታዎ ምርመራ ህዴት እስኪጠናቀቅ ድረስና የዓለምአቀፍ ጥበቃ ካገኙም የሚያገለግል ይሆናል፡ የማሟያ ዕገዛ (CSS) የአገልግሎት ጊዜ አንድ ዓመት በመሆኑ በየዓመቱ በማስረጃ ዶክመንቱ ላይ የአገልግሎት ገደብ ከ4 እስከ 2 ወር በማስቀደም እንዲታደስልዎ በድጋሚ መጠየቅ አለብዎት፡

**የጤና መድን ዋስትና ሽፋን እስኪያገኙ ባለዉ ጊዜ ዉስጥ ከዚህ በላይ « ሕክምና የት ይሰጣል ? » በሚለዉ አርዕስት ሥር ወደተዘረዘሩት የነጻ ህክምና ተቋማት በመሄድ አስፈላጊዉን ሕክምና ማግኘት ይችላሉ፡**

**የሚያስፈልግዎ (አስቸኳይ ሕክምናም) በሆስፒታል ይሰጥዎታል፥** ይህም የሚሆነዉ የሚያስፈልግዎት ሕክምና ጊዜ የማይሰጥ ከሆነ ነው፥ ለምሳሌ በጥልቁ መቁሰል፣ ስብራት፣ ቃጠሎ፣ በአደገኛና ተላላፊ በሽታ መያዝ፣ ማናቸዉም የታዳጊዎችና የዕርጉዝ ሴቶች ሕክምና (በተለይም ከዕርግዝና በፊትና ቦኋላ የሚከናወን የመከላከያ ምርመራ፣ ማዋለድ፣ ዕርግዝናን ማቋረጥና የመሳሰሉ) ናቸዉ፡

**ለሕክምና ወደሆስፒታል ሲሄዱ ያለክፊያ መታከም ይችሉ ዘንድ የጥገኝነት አመልካች ማስረጃዎን ይዘው መሄድ አለብዎት፡**

**<u>ለማስታወስ</u>**

**የጤና መድን ዋስትና ለማግኘት በመኖሪያ አድራሻዎ ለሚገኘዉ CPAM የጥገኝነት አበቱታዎን እንዳስመዘገቡ ለታዳጊ ልጆችዎ ወዲያዉኑ ማመልከት፥ ለራስዎ (ወይም ለባለቤትዎ) ደግሞ በፈረንሳይ ቆይታዎ 3 ወራት ስሞላ ማመልከት አለብዎት፡**

**በተረፈም የጤና መድን ዋስትና ተጠቃሚ እስኪሆኑ ድረስ ባለዉ ቆይታዎ በአንዳንድ ተቋማት ሕክምና በነጻ የሚሰጥዎ ሲሆን፤ የሚያስፈልግዎት (አስቸኳይ ሕክምና) በሆስፒታል ይሰጥዎታል፥ የጥገኝነት አመልካች ስለመሆንዎ ማስረጃዎን ማሳየት ያስፈልጋል፡**

**ያሉበት ሁኔታ በየትኛዉም ረገድ ከተለወጠ CPAMን ማሳወቅ፥ አዲስ የጥገኝነት አመልካች ማስረጃ ኮፒ መላክ፣ የአዲስ አድራሻዎ ማስረጃ ኮፒ መላክ፣ የዓለም አቀፍ ጥበቃ መብት ካገኙ የመኖሪያ ካርድ ስለመጠየቅዎ ማስረጃ ኮፒ መላክ አለብዎት።**

## 4.5. ሥራ-ዓለም ስለመግባት

እንደ የጥገኝነት አመልካች፥ OFPRA ከእርስዎ ጋር ባልተያያዘ ስበብ አበቱታዎ ከቀረበበት ቀን አንስቶ በስድስት ወራት ቆይታ ውሳኔ ካልሰጠበት የሥራ ፍቃድ መጠየቅ ይችላሉ፡

ይህ ከሆነ ፥ እርስዎ ከወደፊት ቀጣሪዎ ጋር በመሆን የሥራ ፍቃድ እንዲሰጥዎ በሚኖሩበት ክልል ጉዳዩ ለሚመለከተው የአገልግሎት ክፍል (SMOE/DIRECCTE) ጥያቄ ማቅረብ ያስፈልጋል፡

የሥራ ፍቃድን በተመለከተ ጥያቄው ከቀረበበት ቀን አንስቶ በሁለት ወራት ቆይታ ውስጥ ፕሬፈው/DIRECCTE/SMOE በአጋራ የሚወስኑት ይሆናል፡ በዚህ ቆይታ ውስጥ ካልተመለሰልዎ እንደተፈቀድ የሚወስድ ይሆናል፡ ውሳኔው ለእርስዎና ለወደፊት ቀጣሪዎ ተልኮ የመቆየት መብት እስካለዎት ድረስ የሚያገለግል ይሆናል፡

ለሥራ ፍቃድ ስምምነት ከተገኘ፥ ፕሬፌው ፍቃዱ ከ3 ወራት በላይ ለረዘም የሥራ ውል ወይም በOFII በኩል ባሉት ወቅታዊ ሥራዎች የሚያገለግል መሆኑን ይገልጻል፡

ሆኖም ግን፥ በሚጠይቁት የሥራ መስክ ሰራተኛ ማግኘት ችግር ካልሆነ በስተቀር በጠየቁት ክልልና የሥራ መስክ ያለውን የሥራ ዕድል ግምት ውስጥ በማስገባት ፍቃዱን ሊከለክሉ ይችላሉ፡

ጊዜያዊ የሥራ ፍቃድ የያዙ ከሆነና የሥራ ውልዎ ቅጥር ጊዜው መገባደድና ከእርስዎ ጋር ግንኙነት በሌለው ምክንያት ከተቋረጠ እንደ ሥራ ፈላጊ በፖል አምፕሏ (Pôle emploi) እንዲመዘገቡ መጠየቅ ይችላሉ፡

ነጠላ (ብቸኛ) ታዳጊ ሆነዉ፥ የሥራ ፍቃድ የተሰጠዎት ለተወሰነ ጊዜ ሙያዊ የስልጠና ውል እንዲፈጽሙ ከሆነና ከማርች 1, 2019 ወዲህ የጥገኝነት አበቱታ ካቀረቡ በውልዎ መቀጠል ይችላሉ፡

በመጨረሻም ወደ ሥራ ዓለም ከገቡ የሥራ ኮድ በሚፈቅደው ደንብ መሰረት የሙያ ስልጠና ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ።

# 5. የጥገኝነት አበቱታዎ ውድቅ መሆን በመቆየት መብትዎ ላይ ያለው ተጽዕኖ

## 5.1. በOFPRA ወይም በCNDA ዉሳኔ ውድቅ መሆን

### ■ የOFPRA ውሳኔ ማሳወቅን ተከትሎ የመቆየት መብት መቋረጥ

✓ ለCNDA ይግባኝ ማቅረብ የሚያግድ አይሆንም

በክፍል 3.1 እንደተመለከተው ከሚከተሉት የOFPRA ውሳኔዎች መካከል የሚመለከትዎ ካለ በአገሩ ብሔራዊ ግዛት የመቆየት መብትዎ የሚቋረጥ ይሆናል፥

1. አበቱታዎ ተቀባይነት ካጣ ፥ ተፈጻሚነት ያለው ከለላ (ጥበቃ) ከአንድ አገር የተሰጠዎ ሁኖ ይህ አገር የአውሮፓ ህብረት አባል ካልሆነም ተመልሰው የመግባት ፍቃድ አሉዎት (ክፍል 3.3 ይመልከቱ) ፤
2. የአበቱታ ፋይልዎ ከተዘጋ (ክፍል 3.3 ይመልከቱ) እና
3. አበቱታዎ ተቀባይነት ካጣ፥ እርስዎን ከአገር የማስወጣት ሂደት እያለ በድጋሚ እንዲመረመር በቀረበ የመጀመሪያ ጥያቄ ከሆነ ነው፡

በነዚህ ሁኔታዎች፤ የጥገኝነት አመልካች ማስረጃዎ ይሰረዛል ወይም አይታደስም፡ በግዳጅ የፈረንሳይን ምድር እንዲለቁ ሊደረግ ይችላል፡ ለ CNDA ይግባኝ ማቅረብ ስለማያግድ በማናቸውም ጊዜ ሊተገበር ይችላል፡

የጥገኝነት አበቱታዎን ጥያቄ እንዳነሱ OFPRAን ካሳወቁም የመቆየት መብትዎ የሚቋረጥና ለCNDA ይግባኝ ማቅረብ የሚያግደዉ አይሆንም፡

✓ **ለCNDA ይግባኝ ማቅረብ በራሱ ዕገዳ እይጥልም**

ከሚከትሉት የOFPRA ውሳኔዎች መካከል የሚመለከትዎ ካለም በአገሩ ብሔራዊ ግዛት የመቆየት መብትዎ የሚቋረጥ ይሆናል፥

1. አበቱታዎ ተቀባይነት ካጣ ፥ የየድጋሚ ምርምራ የመጀመሪያ ጥያቄ የሚመለከትዎ ከአገር የማስወጣት እርምጃ ሳይኖር፤
2. አበቱታዎ በዉሳኔ ውድቅ ከሆነ ፥ በየድጋሚ ምርመራ ጥያቄ መሰረት ተመርምሮም፤
3. በOFPRA የተፋጠነ ምርመራ ሂደት ውድቅ የተደረገ ከሆነ ፥ የደህንነት ዋስትና ካለበት የተረጋጋ አገር የመጡ በመሆንዎ፤
4. በOFPRA የተፋጠነ ምርመራ ሂደት ውድቅ የተደረገ ከሆነ ፥ በብሄራዊ ግዛት መቆየትዎ ለህዝብ ሥነአኗኗር ከፍተኛ ስጋት በመሆኑና
5. በOFPRA ተቀባይነት ያጣ ወይም ውድቅ የተደረገ አበቱታ፥ እርስዎን የሚመለከት ከአገር የማስወጣት ወይም የአስተዳደራዊ ወይም ህጋዊ ክልከላ ምክንያት በቁም እሥር ወይም የጥበቃ ማዕከል ታግተዋል (ክፍል 2.2.1 « በአስተዳደራዊ ወይም በመደበኛ ፍ/ቤት የተላለፈ እርስዎ ከአገር የማስወጣት እርምጃ ሂደት ወይም አገር የመልቀቅ ፍርድ አለ ? »ን ይመልከቱ ) ፡

ከ1 እስከ 4 ባሉት ሁኔታዎች ፥ የጥገኝነት አመልካች ማስረጃዎ ይሰረዛል ወይም አይታደስም፤ በግዳጅ ከፈረንሳይ ግዛት እንዲለቁ የማድረግ ሂደት ሊገጥምዎት ይችላል ፡

የሚመለከትዎ አገር የመልቀቅ ግዴታ (OQTF) እንደተላለፈብዎ ፥ የጥገኝነት አበቱታዎ ምርመራ እንዲፋጠን የቁም እሥር ወይም የጥበቃ ማዕከል ውስጥ እንዲገቡ ሊደረግ ይችላል፡ ይህም የጥገኝነት አበቱታዎ መንስኤ ለመረዳት እንዲሁም የብሔራዊ ደህንነትና የህዝቡ ሥነአኗኗር ረገድ አስፈላጊ ከሆነ ነው፡

ይግባኝ መጠየቅ በራሱ ዕገዳ የማይጥል ቢሆንም፥ የተጣለብዎትን OQTF በመቃወም ለአስተዳደራዊ ፍ/ቤት በሚያቀርቡት አበቱታ እርስዎን ከአገር የማስወጣት እርምጃ ላይ የይግባኝ አበቱታዎን ለCNDA እስኪያቀርቡ ድረስ ወይም ካቀረቡም CNDA መርምሮ እስኪወስን ዕገዳ እንዲጣል መጠየቅ ይችላሉ፡

ለማንኛውም፥ የጥገኝነት አበቱታ ውድቅ መሆንን መሰረት ያደረገ የOQTF እርምጃ በአስተዳደራዊ ፍ/ቤት ፊት ውሳኔው ከደረሰበት ቀን አንስቶ በአሥራ አምስት ቀናት ቆይታ ውስጥ ቀርቦ መቃውም ይቻላል፡ ፍ/ቤቱም በስድስት ሳምንታት ጊዜ ዉስጥ ይወስናል፡ በቁም እሥር ወይም በጥበቃ ማዕከል ዉስጥ ከታገቱ የይግባኝ ማቅረቢያ የቆይታ ገደብ 48 ሳዓት ብቻ ሲሆን ፍ/ቤቱም በ72 ሳዓት ዉስጥ ዉሳኔ ይሰጣል፡

OQTF በመቃውም የሚቀርብ ይግባኝ ዕገዳ የሚጥል ነው፡ የተቃውሞ አበቱታዎን የማቅረብ ቆይታ ሳይገባደድ ወይም አበቱታዎን ለአስተዳደራዊ ፍ/ቤት ካቀረቡ ፍ/ቤቱ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት እርስዎን ከአገር ማስወጣት አይቻልም፡

የተጣለብዎት OQTF የጥገኝነት አበቱታዎ ከመመዝገቡ በፊት በመሆኑ ይግባኝ ማቅረብ ዕገዳ የማይጥልበት ከሆነ፤ በቁም እሥር ወይም የጥበቃ ማዕከል ከገቡበት አንስቶ በ48 ሳዓት ውስጥ በቀጥታ የአስተዳደራዊ ፍ/ቤት ዕገዳ እንዲጥልበት መጠየቅ ይችላሉ፡ የዚህ ዕገዳ ጥያቄ እርስዎን የማስወጣት እርምጃ እንዲገታ ያደርጋል፡

የተጣለብዎትን OQTF ካልተቃወሙ ወይም ይግባኝ የማይቀርብበት OQTF ከሆነና እንዳይተገበር ዕገዳ እንዲደረግ ካልጠየቁ የይግባኝ ወይም የዕገዳ አበቱታ ገደብ ሲጠናቀቅ በማናቸውም ጊዜ እርስዎን ከአገር ማስወጣቱ ተፈጻሚ ሊሆን ይችላል፡ በተጨማሪም፥ ለይግባኝ ወይም የዕገዳ አበቱታ ገደብ ከተጠናቀቀበት ወር መጨረሻ አንስቶ የአቀባበል ቁሳዊ አቅርቦት ተጠቃሚነትዎም ይቋረጣል፡

በተራ ቁጥር 5 ሥር ያለውን ሁኔታ በተመለከተ ፥ የOFPRA ውሳኔን ተከትሎ በ48 ሳዓት ውስጥ እርስዎን ከአገር የማስወጣት ሂደት፥ ይግባኝዎ በCNDA ተመርምሮ እስኪወስን (ክፍል 2.2.1« በአስተዳደራዊ ወይም በመደበኛ ፍ/ቤት የተላለፈ እርስዎን ከአገር የማስወጣት እርምጃ ሂደት ወይም አገር የመልቀቅ ፍርድ አለ ? »ን ይመልከቱ) ድረስ እንዲታገድ ለአስተዳደራዊ ፍ/ቤት ማመልከት አለብዎት።

**እርስዎን ከአገር የማስውጣት ሂደት ላይ ዕገዳ እንዲጣል ላቀረቡት አበቱታ ውሳኔ ምንድነው ?**

በአበቱታዎ ውስጥ ያቀረቧቸው መከራከሪያ ፍሬ ኃሳቦች በአገር ለመቆየትዎ በቂ ማረጋገጫ ከሆኑ የአስተዳደራዊ ፍ/ቤቱ በጥያቄዎ መሰረት ይግባኝዎ በ CNDA ተመርምሮ ውሳኔ እስኪሰጥበት ድረስ እንዲቆዩ ይወስናል፡

ይህ ከሆነ የይግባኝ አበቱታ ለCNDA የማቅረብ ገደብ እስኪጠናቀቅ ድረስ ወይም ይግባኝ ቀርቦ ከሆነ CNDA ውሳኔ እስኪሰጥበት ድረስ የመቆየት መብት አለዎት፡ እንደአስፈላጊነቱም፥ የአስተዳደራዊ ፍ/ቤቱ ውሳኔ የቁም እሥሩ ወይም በጥበቃ ማዕከል መታገትዎ በህዝብ ሰላምና ደህንነት ሳቢያ ካልሆነ በስተቀር እንዲነሳ ያደርጋል፡ የአቀባበል ቁሳዊ አቅርቦትም ለCNDA ይግባኝ ለማቅረብ የተገደበው ቆይታ ከተጠናቀቀበት ወር መጨረሻ ወይም ችሎቱ ውሳኔ ከሚስጥበት ወር መጨረሻ አንስቶ የሚቋረጥ ይሆናል፡ ፍ/ቤቱ ያቀረቡትን ከአገር የማስወጣት ሂደት ዕገዳ ጥያቄ ውድቅ ካደረገ እርስዎን ከአገር ማስወጣት ሊተገበር ይችላል፡ የአቀባበል ቁሳዊ አቅርቦትም ፍ/ቤቱ ውሳኔውን ካሳወቀበት ወር መጨረሻ እንስቶ ይቋረጣል፡

የተጣለብዎት OQTF በፍላጎት አገር እንዲለቁም የጊዜ ገደብ ያካተተ ከሆነ፥ ይህ ቆይታ የአስተዳደራዊ ፍ/ቤቱ የዕገዳውን ጥያቄ ውድቅ ካደረገበት አለዚያም CNDA ዉሳኔ ከሰጠበት አንስቶ የሚቆጠር ይሆናል።

## ■ የ CNDA ዉሳኔ በይፋ ችሎት መነበቡን ወይም ማሳወቅን ተከትሎ የመቆየት መብት ስለመቋረጥ

ከዚህ ለየት ባሉ ሁኔታዎች ፥ የጥገኝነት አበቱታዎ በመጨረሻ ውሳኔ ውድቅ ሲሆን የመቆየት መብትዎ የሚቋረጥ ይሆናል፡ ይሄውም፥

- የOFPRA ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለCNDA የሚቀርብበት ቆይታ (አንድ ወር) ይግባኝ ሳያቀርቡ ከተገባደደ ወይም
- የይግባኝ አበቱታዎን ለCNDA በተገደበው ቆይታ አቅርበው ነገር ግን ችሎቱ በማዘግ ውሳኔ ሰጥቶ ዉሳኔውን በይፋ ካነበበት ወይም ካሳወቀበት አንስቶ የሚቋረጥ ይሆናል፡

ይህ ከሆነ ፈረንሳይን መልቀቅ ይኖርብዎታል፡ ፈረንሳይን በግዳጅ እንዲለቁ ሊደረግ ይችላል።

**ለመንግስት ምክር ቤት የሰበር አበቱታ ማቅረብ የመቆየት መብት ያስገኛል ?**

የCNDA ወሳኔ በመቃወም የሰበር አበቱታ ለመንግስት የመማክርት ጉባዔ ማቅረብ ይችላሉ፡ ይህ አበቱታም የችሎቱ ዉሳኔ እጂዎ ከደረሰበት አንስቶ በሁለት ወር ዉስጥ ለመንግስት የመማክርት ጉባዔ መድረስ አለበት፡

የመንግስት መማክርት ጉባዔ ይህን አበቱታዎን በአጠቃላይ በድጋሚ የሚመረምር ሳይሆን የስደት ፍ/ቤቱ ውሳኔ የህግ ሂደትን ያከበረና በአፈጻጸም ላይ ስህተት አለመኖሩን ብቻ የሚያይ ይሆናል፡

ይህን የሰበር አበቱታ ማቅረብዎ የመቆየት መብት ተጠቃሚ ስለማያደርግዎ የመንግስት ምክር ቤቱ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት እርስዎን ከአገር የማስወጣቱ እርምጃ ሊተገበር ይችላል።

## 5.2. ወደአገር መመለሻ የሚሰጥ ዕርዳታ

ፕሬፌክቱሩ እርስዎን የሚመለከት አገር የመልቀቅ ግዴታ (OQTF) ሲያስታውቅዎ ፥ ሁኔታውን የሚያሟሉ ከሆነ በገዛ ፍቃድዎ አገር መልቀቅ የሚችሉበትን የጊዜ ገደብ ባብዛኛው የ30 ቀናት ቆይታ ይሰጣል፡
በዚህ በተሰጠዎ የቆይታ ገደብ ወደአገርዎ ለመመለስ የሚሰጥ ዕርዳታ ተጠቃሚ ለመሆን ማመልከት ይችላሉ፡ ይህን ለማድረግ ለፈረንሳይ የኢሚግሬሽንና ውሂደት ጽ/ቤ (OFII) ማመልከት አለብዎት፡

✓ **ለመመለሻ የሚሰጥ ዕርዳታ**

የመመለሻ ዕርዳታ በህገወጥ የቆይታ ሁኔታ ውስጥ ያሉ የውጪ አገር ዜጎች ወደሃገራቸ መመለስ የሚችሉበትን ሁኔታ ለማመቻቸት የሚሰጥ ነዉ፡ ይህ ዕርዳታ ተጠቃሚ ለመሆን አገር የመልቀቅ ትዕዛዝ እንደደረሰ ወዲያው መጠየቅ ያስፈልጋል፡ በዚህም፥ የተሰጠውን በገዛ ፍቃድ የመልቀቂያ ቆይታን ጥቅም ላይ ማዋል ይቻላል፡
ዕርዳታው የመመለሱ ሁኔታ የተሳካ እንዲሆን ያለመ ሲሆን፥ ለዚህም OFII በሚከተሉት ላይ ዕገዛ ያደርጋል፤

- **ለጉዞው አስተዳደራዊና ቁሳዊ ዝግጅት ማድረግን** በተመለከተ የተጠቃሚውና ቤተሰቡ በገዛ ፍቃዳቸው ወደሃገራቸው መመለስ የሚያስችሉ ቁሳዊ አቅርቦት እንደ፥
  - የአውሮፕላን ትኬት መያዝ ፤

- የጉዞ ሰነዶች እንዲያገኙ ማድረግ ፤
- በፈረንሳይ ከሚኖሩበት ሥፍራ ከፈረንሳይ መውጫ አየር ማረፊያ ድረስ መዉሰድ ፤
- በመዉጫ የአየር ማረፊያው የአቀባበልና የፎርማሊቲ ሂደት ዕገዛ መስጠትን ያካተተ ነው፡

- ከፈረንሳይ ከሚነሱበት ሥፍራ እስከመድረሻ አገር **የትራንስፖት ወጪ** የመመላሻ አገሩ ባስቀመጠው ገደብ ውስጥ የሻንጣን ጨምሮ መሸፈን፤
- ለተመላሹ የውጪ ዜጋ በሚለቅበት ወቅት አንዴ የሚሰጥ **የገንዘብ ዕርዳታ** ነው፡

### ✓ ለመልሶ ማቋቋም የሚሰጥ ዕርዳታ

ከፍ ብሎ ከተመለከተው ዕርዳታ በተጨማሪ ወይም በተናጠል፥ ወደሃገራቸው ለተመለሱ የውጪ ዜጎች እኮኖሚያዊና ማህበራዊ የመልሶ ማቋቋም ድጋፍ ሊቀርብ ይችላል፡

ይህ ድጋፍ አንዳንድ ሁኔታዎች ከተሟሉ፥ የጥገኝነት አበቱታዎች ውድቅ ለሆነባቸውም የውጪ ዜጎችና ቤተሰቦቻቸው ሊሰጥ ይችላል፡

የመልሶ ማቋቋም ዕርዳታ በ3 ደረጃ የተመደበ ነው፡ እንደሁኔታውና የተመላሹን ፍላጎት በማገናዘብ እነዚህ ዕርዳታዎች ሊጣመሩ ይችላሉ፥

- **እንደደረሱ የሚሰጥ የማህበራዊ መልሶ ማቋቋም ዕርዳታ** (ደረጃ 1)

  አስቸኳይ ዕርዳታ የቁሳቁስ ወይም የገንዘብ ፥ መኖሪያን ለማመቻቸት ወይም ለመጠለያ ለተወሰነ ጊዜ፤

  የሕክምና እንዲሁም ለልጆች ትምህርትና ትምህርት መሳሪያዎች ወጪ የሚውል ዕርዳታ ነው፡

  ይህ ድጋፍ ለተወሰነ ጊዜ የማህበራዊ ክትትልን ለምሳሌ እንደ የቤተሰብ ፍላጎት ግምገማ ሊያካትት ይችላል፡

- **በሥራ ቅጥር የመልሶ ማቋቋም ዕርዳታ** (ደረጃ 2)

  ይህም የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፤

  ○በተመለሱበት አገር ለሥራ ቅጥር፤

  ○ለሥራ ፍለጋና

  ○ለሙያ ስልጠና የሚውል ነው፡

- **በግል የሥራ ፈጠራ የመልሶ ማቋቋም ዕርዳታ** (ደረጃ 3) ናቸው።

### 5.3. በግዳጅ ወደ አገር ስለመመለስ

በገዛ ፍቃድዎ አገር እንዲለቁ የተሰጠዎ የጊዜ ገደብ ካለና በዚሁ ገደብ ያልለቀቁ ከሆነ የፈረንሳይ ቆይታዎ ሕገወጥ ይሆናል፡

ይህ ከሆነ እንግዲህ በፖሊስ ከድንበር ወዲያ ሊሸኙ ይችላሉ ፡ ይህ አሸኛኘት በቅድሚያ በቁም እስር ወይም በጥበቃ ማዕከል የመታገት አስተዳደራዊ ዉሳኔ/እርምጃ ሊያጠቃልል ይችላል፡

የተላለፈብዎ OQTF በገዛ ፍቃድዎ የመልቀቂያ ቆይታ ገደብ ያላካተተ ከሆነ፥ ዉሳኔዉ እጅዎ ከደረሰበት ጊዜ አንስቶ ቆይታዎ ህገወጥ ሆኖ በማናቸውም ጊዜ ተይዘዉ ሊሸኙ ይችላሉ።

# 6. የከለላ ተጠቃሚዎች ያላቸው መብቶች

ሙሉ የስደት ከለላ ወይም የሰብአዊ ከለላ ተጠቃሚነት ከተከበረልዎ፥ በፈረንሳይ ባለሥልጣናት ጥበቃ ይሰጥዎታል፡ ከአገሪዎ ባለሥልጣናት ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት ማድረግ አይችሉም፡ ባለዎት ስጋቶች ሳቢያም ወደአገርዎ መሄድም አይችሉም፡

አስተዳደራዊና ሕጋዊ ጥበቃዎ በOFPRA የሚከወን ይሆናል፡ ይህ ማለት የወሳኝ ኩነት (የስቪል ሁኔታዎ) ዶክሜንትና የአስተዳደር ማስረጃዎችን፥ ካጠናቀረ በኃላ የሚስጥዎ ይሄው ተቋም ነው።

## 6.1. ኑሮ በፈረንሳይ

**እንደስደተኛ** ለአሥር ዓመት የሚያገለግል የመኖሪያ ካርድ-የአገልግሎት ጊዜ ሲያበቃ- በፈረንሳይ የትም ቦታ መዘዋወር የሚይስችልዎ ይሰጥዎታል፡

ሙሉ የስደት መብት ከለላ እንደተሰጠዎ የሚገልጽ ደብዳቤ ስደርስዎ በሚኖሩበት አድራሻ ወደሚገኘው ፕሬፌክቱር መሄድ ይኖርብዎታል፡ የመኖሪያ ካርድ እንዲሰጥዎ ከጠየቁበት ቀን አንስቶ በ8 ቀናት ቆይታ ውስጥ ፕሬፌክቱሩ ለ6 ወር የሚይገልና የሚታደስ ( « reconnu réfugié » የተጻፈበት) የመጀመሪያ ሬሴፒሴ ይስጥዎታል፡

ይህ ሬሴፒሴ በፈለጉት የሥራ መስክ የመሰማራት መብት ይሰጥዎታል፡ የመኖሪያ ካርድዎ እስኪደርስዎ ድረስ የሚታደስ ይሆናል፡ OFPRA የሲቪል ሁኔታዎን ካጠናቀረ በኃላ የመኖሪያ ካርድ ያገኛሉ፡

**እንደ የሰብአዊ ከለላ ተጠቃሚ፤** ከማርቸ 1 2019 ወዲህ ለአራት ዓመት የሚያገለግል ካርድ በየትኛውም የፈረንሳይ ግዛት ያለችግር መዘዋወር የሚያስችልዎ ካርድ ይስጥዎታል፡

ሙሉ የሰብአዊ ከለላ ተጠቃሚ መሆንዎን የሚገልጽ ደብዳቤ ሲደርስዎ በሚኖሩበት አድራሻ ወደሚገኘው ፕሬፌክቱር መሄድ ይኖርብዎታል፡ የመኖሪያ ካርድ እንዲሰጥዎ ከጠየቁበት ቀን አንስቶ በ8 ቀናት ቆይታ ውስጥ ፕሬፌክቱሩ ለ6 ወር የሚይገልና የሚታደስ ( « *a obtenu le bénéfice de la protection subsidiaire* » የተጻፈበት) የመጀመሪያ ሬሴፒሴ ይስጥዎታል፡ ይህ ሬሴፒሴ በፈለጉት የሥራ መስክ የመሰማራት መብት ይሰጥዎታል፡ የመኖሪያ ካርድዎ እስኪደርስዎ ድረስ የሚታደስ ይሆናል፡ OFPRA የሲቪል ሁኔታዎን ካጠናቀረ በኃላ የመኖሪያ ካርድ ያገኛሉ፡

በፈረንሳይ የአራት ዓመት መደበኛ ቆይታ በኃላ የአሥር የመኖሪያ ካርድ ይሰጥዎታል።

## 6.2. የቤተሰብ ቆይታ

### ■ ለቤተስብዎ አባላት የቆይታ/የመኖሪያ መብት/ፍቃድ

**ሙሉ የስደት ከለላም ሆነ የሰብአዊ ከለላ ተጠቃሚ ከሆኑ**፥ የሚከተሉት ከእርስዎ ጋር ተመሳሳይ የሆነ የመኖሪያ ካርድ የማግኘት መብት አላቸው፤

- ባለቤትዎ ወይም በሲቪል ትሥሥር ያሉዎት ጓደኛዎ ከ18 ዓመት ዕድሜ በላይ ከሆነ/ከሆነች፤ ጋብቻው ወይም የሲቪል ትሥሥሩ የጥገኝነት አበቱታ ከማቅረብዎ በፊትና ጋብቻው ወይም የሲቪል ትሥሥሩ ከተከበረ ቢያንስ አንድ ዓመት የሆነና የጋራ ህይወቱ አሁንም ካለ፣

- ባለቤትዎ ወይም በሲቪል ትሥሥር የሕይወት ጓደኛዎ የሆኑትና በቤተሰብ የማሰባሰብ/ማገናኘት ፍቃድ ፈረንሳይ የሚኖሩ ከሆነ (ከሥር « ቤተሰብ የማሰባሰብ/የማገናኘት መብት»ን ይመልከቱ)
- ልጆችዎ ከ18 ዓመት ዕድሜ በላይና መሥራት ከፈለጉ ከ16 ዓመት ዕድሜ ያላቸው እንዲሁም
- እርስዎ ታዳጊና ያላገቡ ከሆኑ ወላጆችዎ ናቸዉ፡

የቤተሰብዎ አባላት የመኖሪያ ካርድ ለማግኘት በሚኖሩበት አድራሻ ለሚገኘው የፕሬፌክቱር ጽ/ቤት ማመልከት አለባቸው።

## ■ ቤተሰብ የማሰባሰብ/የማገናኘት መብት

የከለላ መብት ሲከበርልዎ ፥ የቤተሰብዎ አባላት ከፈረንሳይ ውጪ ከሆኑ፤ ከለላ እንደተደረገልዎ ወዲያዉ ገቢዎም ሆነ መጠለያዎ ግምት ዉስጥ ሳይገባ በቤተሰብ የማሰባሰብ/ማገናኘት ሂደት እንዲመጡ ማድረግ ይችላሉ፡

ይህ ሂደት የሚከተሉትን የሚመለከት ይሆናል፥

- ባለቤትዎ ወይም በሲቪል ትሥሥር ያሉዎት ጓደኛዎ ከ18 ዓመት ዕድሜ በላይ ከሆነ/ከሆነች፤ ጋብቻው ወይም የሲቪል ትሥሥሩ የጥገኝነት አበቱታ ከማቅረብዎ በፊት የተፈጸም ከሆነ፣
- ሕይወት የሚጋሩት ጓደኛዎ ዕድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነና የሲቪል ትሥሥሩ የጥገኝነት አበቱታ ከማቅረብዎ በፊት የነበረ የተረጋጋና ቀጣይነት ያለው ከሆነ፣
- ልጆችዎ ከ19 ዓመት በላይ ከሆኑ ያላገቡ ከሆነ፣
- እርስዎና የትዳር ጓደኛዎ ከቀድሞ ጋብቻ ያሏችሁ ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆቻችሁ፣ እነዚህም፥
  - ✓ የወላጅ ግንኙነቱ ከእርስዎ ወይም ከትዳር ጓደኛዎ ብቻ የሆነና ሌላኛው ወላጁ የሞተ ወይም የወላጅነት መብቱን የተነፈገ ከሆነ፣
  - ✓ እንደሁኔታው ለእርስዎ ወይም ለትዳር ጓደኛዎ በዉጪ አገር የሕግ ውሳኔ ባሳዳጊነት የተሰጡዎትን ነው፡ የዚህ ውሳኔ ኮፒና የሌላኛው ወላጅ የታዳጊውን ወደፈረንሳይ መምጣት የፈቀደበት ማስረጃ ማቅረብ ያስፈልጋል፡
- እርስዎ ታዳጊና ያላገቡ ከሆነ የወላጅ ኃላፊነት ካባቸው ወላጆችዎ መጥተው ከታዳጊ ልጃቸው ጋር መሆንና መንከባከብ ይችላሉ፡

የቤተስብዎ አባላት ወደ ፈረንሳይ ለመምጣት ከኤምባሲ ወይም ቆንስላ ባለሥልጣናት ከ3 ወር በላይ የሚያገለግል ቪዛ መጠየቅ ይችላሉ፡ ባለሥልጣናቱም ለጥያቄው በአጭር ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ይሰጣሉ፡ ከስደተኛው ወገን የቤተሰብ ቢሮ የሚጠየቅ ደብዳቤ አይኖርም፡

በሬፑብልኩ ሕጎች መሰረት የተደነገጉና በፈረንሳይ የቤተሰብ መሰረታዊ መርሆዎችን የማያከብሩ ከሆነ፥ የቤተሰብ ማሰባሰብ መብት ላይፈቀድልዎ ይችላል፡ እንደዚሁም ማናቸውም የቤተሰብዎ አባል ፈረንሳይ መኖሩ ለሕዝብ ሰላምና ደህንነት ስጋት ከሆነ ወይም የስደት ከለላ አስፈላጊ የሚያደርግ የማሳደድና የማሰቃየት ድርጊት መፈጸሙ ወይም በዚህ ድርጊት መተባበሩ ከተረጋገጠ ቤተሰብ ከማሰባሰብ ህደቱ የሚገለል ይሆናል፡

ጋብቻዎ የጥገኝነት አበቱታዎ ከቀረበ ቦኃላ ከሆነ የቤተሰብ ማሰባሰብ ጥያቄዎን ለOFII ማቅረብ አለብዎት።

## 6.3. የመቋቋም ጎዳና

### ■ ከፈረንሳይ የኤምግሬሽንና ዉህደት (መቋቋም) ጽ/ቤት (OFII) ጋር የሚፈረም የሬፑብሊክ ዉህደት(የመቀላቀል) ውል

እንደ ስደተኛ ወይም የሰብአዊ ከለላ ተጠቃሚ፥ የሬፑብሊክ ዉህደት (የመቀላቀል) ውል (CIR) መፈረም የእርስዎ ኃላፊነት ነው፡ ይህ በእርስዎና በመንግስት መካከል የሚፈረመው ውል ፈረንሳይ ማህበረሰብ ውስጥ ለመቀላቀል የሚያደርጉትን ጥረት ማቅለል ታሳቢ ያደረገ ነዉ

ይህ ውል የሚከተሉትን አገልግሎቶች እንዲያገኙ ያደርጋል፥

- የ4 ቀናት የሲቭል ስልጠና፥ መሰረታዊ ግንዛቤዎች፣ በፈረንሳይ የሕይወት መርሆችና እሰቶችን እንዲሁም የመብትና ግዴታ ሚዛን መጠበቅ ላይ ትኩረት የሚሰጥ፣
- የቋንቋ ስልጠና፥ ችሎታዎን በመመዘን የፈረንሳይኛ ቋንቋ እንዲማሩ፣ ስልጠናው ሲጠናቀቅ መደበኛ ሰርተፊከት እንዲያገኙ፣
- የሙያ ሥምሪት ምክርና ወደሥራ ዓለም አገባብና ሙያዊ መቋቋም አስመልክቶ ግንዛቤ እንዲያገኙ ማመቻቸትና
- ፊላጎትዎን ግንዛቤ ዉስጥ ባስገባ ክትትል አቀባበልዎንና ዉህደትዎን አመቺ ማድረግን ነው።

ተጨማሪ በቂ መረጃ ከሚኖሩበት ክልል የOFII መምሪያ ጽ/ቤት በመጠየቅ ማግኘት ይችላሉ።

## 6.4. የማህበራዊ ድጋፎችን የማግኘት መብት

### ■ መጠለያ ማግኘት

የጥገኝነት አበቱታዎ ሀድት ላይ እያለ በCADA ወይም በለሎች ብሔራዊ የመቀበያ ሥፍራዎች ተጥለው ከቆዩ የከለላ መብት ከተከበርልዎ በኃላ ለተጨማሪ 3 ወራት አንዴ ለሚታደስ ቆይታ በዚሁ መጠለያዎ መቆየት ይችላሉ፡

ከለላ እንደተደረገለት ሰው፥ በአንድ ጊዜያዊ የመጠለያ ማዕከል (CPH) ዉስጥ ለመጠለል ለOFII ማመልከት ይችላሉ፡ ተያያዥ ሁኔታዎችን የሚያሟሉ ከሆነና ክፍት ቦታ ከተገኘ በመጀመሪያ ዘጠኝ ወራት ከዚያም ለሶስት ወራት ለሚታደስ ቆይታ መጠለል ይችላሉ፡

የመጠለያ ማዕከሉ የሰራተኞች ቡድን እርስዎ የሚያደርጉትን የመቋቋም ጥረት የግል ሁኔታዎን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ያደርጉልዎታል፡

በሌላ በኩል፥ በግል ባለንብረቶች የሚከራዩት የመኖሪያ ቤቶችም ሆነ የማህበራዊ ኪራይ ቤቶች ተጠቃሚ ለመሆን በቀጥታ ለሚመለከታቸው ተቋማት የማመልከቻ ፋይል ማቅረብ ይችላሉ።

### ■ ወደ ሥራ ዓለም የመግባት መብት

**የስደተኛ መብት ከተከበረልዎ** « *Reconnu réfugié* » የሚል ጽሁፍ የያዘ የመጀመሪያ ሬሴፒሴ ሲደርስዎ ወደሥራ መሰማራት ይችላሉ፡

**የሰብአዊ ከለላ ተጠቃሚነት ከተከበረልዎም** « *A obtenu le bénéfice de la protection subsidiaire* » የሚል ጽሁፍ የያዘ የመጀመሪያ ሬሴፒሴ ስደርስዎ ወደሥራ መሰማራት ይችላሉ፡

በጊዜያዊ የሥራ ቅጥር ውል (CDD) ወይም በቋሚ የሥራ ቅጥር ውል (CDI) ሊሰማሩ ይችላሉ፡ እንደዚሁም በሥራ ፈላጊዎች ዝርዝር ላይ ተመዝገበው የግል ክትትል ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ፡ ስልጠና መግባትም ይችላሉ፡

የስደተኛ ቤተሰብ የመኖሪያ ካርድም ሆነ  የሰብአዊ ከለላ ተጠቃሚ ቤተሰብ የመኖሪያ ካርድ የያዙ አባላት ወደ ሥራ የመግባት መብት አላቸው።

አንዳንድ የሥራ መስኮች ክፍት የሚሆኑት ለተወሰኑ የትምህርት ማስረጃዎች እና/ወይም ዜግነት ነው፡ ከባሕር ማዶ የፈረንሳይ ክልሎች የተሰጡ የመኖሪያ ፍቃድ በፈረንሳይ (ሜትሮፖል) የመሥራት መብት አይሰጡም።

### ■ ሕክምና የማግኘት መብት

**የሕክምና አገልግሎት የሚሰጠው የት ነው ? ክፍል** 4.4 « ሕክምና ማግኘት/የሕክምና አገልግሎት የሚሰጠው የት ነው ? »ን ይመልከቱ፡

**የሕክምና ዋስትና እንዴት ማግኘት ይቻላል ?**

- **እስካሁን ድረስ የሕክምና ዋስትና ለማግኘት ለ CPAM (የሕክምና እንሹራንስና ማሟያ CMU ሽፋን) ካላመለከቱ**

**ክፍል** 4.4 « ሕክምና ማግኘት/» «የሕክምና ወጪዎን የሚሸፍን የጤና መድን ዋስትና እንዴት ያገኛ? »ን ይመልከቱ፡

የሕክምና ዋስትና ለማግኘት ሲያመለክቱ የሚከተሉት ሰነዶች ተያያዥ መሆን አለባቸው፤

- በፕሬፌክቱሩ የተሰጠዎ « *Reconnu réfugié* » ወይም « A obtenu le bénéfice de la protection subsidiaire » የሚል ጽሁፍ የያዘ የመጀመሪያ ሬሴፒሴ፣
- ልጆች ከእርስዎ ጋር ካሉ ጊዜያዊ የቤተሰብ ማስረጃ፣
- የመጠጊያ/የመኖሪያ አድራሻዎ ማስረጃን ነው፡

- **የሕክምና ዋስትና ለማግኘት አመልክተው ከሆነ፥**

ከCPAM የደረሰዎት ማስረጃ አለ፡ የሕክምና ዋስትናና ጠይቀውም ከሆነ የCMU ሽፋን አለዎት፡ ለማንኛውም የ CMU ሽፋን የአገልግሎት ጊዜ (በማስረጃው ቀኑ ተጠቅሷል) ሳያበቃ 2 ወራት በፊት እንዲራዘምልዎ ማመልከቻዎን በድጋሚ ማቅረብ አይርሱ፡

የመኖሪያ ካርድ መጠይቅዎን የሚያረጋግጥ የሬሴፒሴዎና በOFPRA የተሰጠዎትን የወሳኝ ኩነት ዶክሜንቶች ኮፒ ለCPAM መላክ አለብዎት፡

ከዚህ ቦኃላ እንግዲህ አዲስ ማስረጃ ከአዲስ የማህበራዊ ዋስትና ቁጥር ጋር ይደርስዎታል፡

እርስዎም ከCPAM « *carte Vitale* » የሕክምና ዋስትና መረጃዎችን የያዘ ካርድ እንዲስጥዎ መጠየቅ ይችላሉ፡ ይህ ካርድ በነጻ የሚሰጥና በነበረዎት የሕክምና ዋስትና ማስረጃ ምትክ በሁሉም የሕክምና አገልግሎት ጥያቄ ወቅት መያዝ ያለብዎት ይሆናል።

## ■ የማሕበራዊና ቤተሰብ ነክ ጥቅማጥቅሞች

የተቀመጡ መስፈርቶችን የሚያሟሉ ከሆነ የተለያዩ ድጋፎችና ጥቅማጥቅሞችን እንደ (revenu de solidarité active፣ ከሥራ ጋር የተያያዘ የሽልማት(ጉርሻ) ክፊያ ፣ የቤት ክራይ ድጎማ እንዲሁም የአካለ ስንኩላን ድጎማ) እና ልጆች ካሉዎትም የቤተሰብ ድጎማ ማግኘት ይችላሉ፡

ማህበራዊ ድጋፍ ኑሮን ማሸነፍ/መቋቋም ይችሉ ዘንድ አነስተኛ ገቢ ወይም ገቢዎን ለመደጎም በተለይም ከመኖሪያ ጋር የተያያዙ ወጪዎን ለማገዝ የሚሰጡ የገንዘብ ዕርዳታዎች ናቸው፡ በተጨማሪም ከወሊድ፣ ከመዋዕለ ሕጻናት ባለሚዎች፣ ከትምህርት ቤት መልሶ መከፈትና በአጠቃላይ ለልጆች እንክብካቤና ከትምህርታቸው ጋር ለተያያዙ ወጪዎች የሚደረግ የገንዘብ ድጋፍ ነው፡

የማህበራዊ ድጋፍና አንዳንድ የቤተሰብ ጥቅማጥቅሞች አነስተኛ ገቢ ላላቸው ብቻ የሚሰጡ ናቸው፡ የሚከፈሉትም በመቶዎች የሚቆጠሩና በተለያዩ የፈረንሳይ ክፍሎች በሚገኙት የቤተሰብ አበል ፈንድ (caisse d'allocations

familiales, CAF) *እና የግብርና ማህበራዊ መድን ፈንድ (les caisses de mutualité sociale agricole)* በሚባሉት ተቋማት ነው፡

እነዚህን ድጋፎች ለመረዳትና ለመጠየቅ በአድራሻዎ በቅርበት ወደሚገኘው የቤተሰብ አበል ፈንድ መሄድ ወይም ኦንላይን በድሬገጽ www.caf.fr እና www.msa.fr መፈጸም ይችላሉ፡

ማሳሰቢያ ፡ RSA ወይም ከሥራ ጋር የተያያዙ የሽልማት ክፊያን ለማግኘት ማመልከት ይጠበቅብዎታል፡ ያሉዎት መብቶች የሚጠኑት የስደት ወይም የሰብአዊ ከለላ ተጠቃሚነት ከተከበርልዎ ቦኃላ ይሆናል።

## 6.5. የውጭ አገር ጉዞ

የጥበቃ/ከለላ ተጠቃሚ ከሆኑና ከፈረንሳይ ውጪ መጓዝ ከፈለጉ የጉዞ ሰነድ ከፕሬፌክቱር ጠይቀው ማግኘት ይችላሉ፡

**ስደተኛ ከሆኑ** ለአምስት ዓመት የአገልግሎት ጊዜ ያለው የጉዞ ሰነድ ያገኛሉ፡ የ45 ዩሮ የግብር ክፊያ አለው፡

**የሰብአዊ ከለላ ተጠቃሚ ከሆኑ** አራት ዓመት የአገልግሎት ጊዜ ያለው የጉዞ ሰነድ ያገኛሉ፡ የ40 ዩሮ የግብር ክፊያ አለው፡

እነዚህን የጉዞ ሰነዶች በፈረንሳይ የዲፕሎማሲና ቆንጽላ ጽ/ቤቶች ማሳደስ አይቻልም፡ በመሆኑም ጉዞ ከመጀመርዎ በፊት የጉዞ ሰነድዎ ለታለመው ቆይታ የሚያገለግል መሆኑን ማረጋገጥ አለብዎት፡

ከፈረንሳይ ውጪ እያሉ የጉዞ ሰነድዎ የአገልግሎት ጊዜ ከተገባደደ (ከጠፋብዎ ወይም ከተሰረቀብዎ)፥ ባሉበት አገር ውስጥ ለሚገኙ የፈረንሳይ የዲፕሎማሲ ወይም ቆንጽላ ባለሥልጣናት በማመልከት በሚሰጥዎ የይለፍ ፍቃድ (*un laissez-passer*)ና የአገልግሎት ጊዜው ባልተገባደደ የመኖሪያ ፍቃድዎ ተመልሰው ወደፈረንሳይ መግባት ይችላሉ፡

ስደተኛ ወይም የሰብአዊ ከለላ ተጠቃሚ ከሆኑ፥ ታዳጊና የውጭ ዜጋ በፈረንሳይ ያለና የከለላ ተጠቃሚ ያልሆነ ልጅዎ፤ ለአንድ ዓመት የሚያገለግል የመታወቂያ ወረቀትና የጉዞ ሰነድ ማግኘት ይችላል፡ የ15 ዩሮ የግብር ክፊያ አለው።

**ወደ አገርዎ መጓዝ ይችላሉ ?**

ይህ የጉዞ ሰነድ ወደ አገርዎ መሄድ አያስችልዎትም፡ ወደአገርዎ ከተመለሱ ከእንግዲህ ለስጋት የተጋለጡ አይደሉም የሚል ግንዛቤ በመውሰድ OFPRA የሰጠዎትን ከለላ ሊያቋርጥ ይችላል (ክፍል 6.7 ይመልከቱ)፡

ነገርግን እጅግ የተለየ ሁኔታ ሲከሰት (ለሚሳሌ የቅርብ ዘመድ ሞት ወይም በጽኑ መታመም) ለፕሬፈክቱር ካመለከቱ ለ3 ወር የሚያገለግል « sauf-conduit- የመጓጓዣ ሰነድ » ወደአገርዎ መጓዝ የሚያስችልዎ ሊሰጥዎት ይችላል።

## 6.6. ዜግነት የማግኘት መብት

**ሙሉ የስደት መብት** ከተከበረልዎ ወዲያውኑ የፈረንሳይ ዜግነት እንዲሰጥዎ መጠየቅ ይችላሉ፡

**የሰብአዊ ከለላ ተጠቃሚ ከሆኑ** ፥ የፈረንሳይ ዜግነት እንዲሰጥዎ ከመጠየቅዎ በፊት ለ5 ዓመት በመደበኛነት መኖሪዎን ማረጋገጥ ይጠበቅብዎታል፡

የፈረንሳይ ዜግነት ለመጠየቅ አንዳንድ መስፈርቶችን (ለምሳሌ ፈረንሳይኛ ቋንቋ መቻልን) ማሟልላት ይጠበቅብዎታል፡

የዜግነት ጥያቄ ፋይልዎን ወደአንዱ የዜግነት ጉዳይ መምሪያ (*plateforme de naturalisation*) ማቅረብ ይኖርብዎታል።

## 6.7. የከለላ መቋረጥ

- ✓ **ማጭበርበር** ፥ የተደረገልዎ ከለላ በማጭበርበር የተገኘ ከሆነ OFPRA ተጠቃሚ የሆኑትን ከለላ ሊያቋርጥ ይችላል፣
- ✓ **ከለላ/ጥበቃ ሊሰጥዎ የሚያስችል አዲስ ዜግነት አግኝተው በፈረንሳይ የተደረገልዎ አለማቀፍ ከለላ ጥቅም አልባ ሲሆን፣**

- ✓ **ከእንግዲህ በአገርዎ ላይ ስጋት የሉዎትም፡** OFPRA በሚከተሉት ሁኔታዎች ሳቢያ በአገርዎ የሚያሰጋዎት ሁኔታ የለም የሚል ግንዛቤ በመውሰድ ጥበቃዎን ሊያቋርጥ ይችላል፤
  - በገዛ ፍቃድዎ ወደአገርዎ ህደው ቆይታ አደረጉ፣
  - ከአገርዎ ባለሥልጣንት ጋር ግንኙነት ፈጠሩ፣
  - ከለላ እንዲደረግልዎ መንስኤ የሆኑ ሁኔታዎች በብቃት በዘላቂነት መለወጣቸው ከተስተዋለ ነው፡

- ✓ **ልዩ ድንጋጌ፥** ፀረ ሰላም ድርጊት፣ ኢ-ሰብአዊ የጦር ወንጀል፣ ከባድ ወንጀልና ከተባበሩት መንግስታት መርሆዎች የሚቃረን ድርጊት የፈጸሙ መሆንዎ ከታወቀ OFPRA ጥበቃዎ እንዲቋረጥ ያደርጋል፡

- ✓ **በፈረንሳይ መኖርዎ ለማህበረሰብና ለመንግስት ሰላም/ደህንነት ከባድ ስጋት ከሆነ፥**

**- ስደተኛ ከሆኑ** በሚከተሉት ምክንያቶች ጥበቃዎ ይቋረጣል፤

- ○ በምክንያታዊነት ፈረንሳይ መኖርዎ ለመንግስት ደህንነት ከፍተኛ ስጋት ሁኖ ከተገመተ፣
- ○ በመጨረሻ ሕጋዊ ውሳኔ በፈረንሳይ፣ በሌላ የአውሮፓ አባል አገር፣ በልይችተንስቴን፣ በሱዊዘርላንድ፣ በኖርዌይ ወይም በአይስላንድ በወንጀል ወይም በፍትህብሔር ከሽብር ጋር በተያያዘ ወንጀል ተከሰው ወይም የአሥር ዓመት እስራት የተፈረደብዎ ሁነው በፈረንሳይ መኖርዎ ለሕዝብ ደህንነት ከፍተኛ ስጋት ከሆነ ነው፡

- የሰብአዊ ከለላ ተጠቃሚ ከሆኑ **በፈረንሳይ መኖርዎ ለማህበረሰብና ለመንግስት ሰላም/ደህንነት ከባድ ስጋት ከሆነ ጥበቃዎ እንዲቋረጥ ይደረጋል፡**

# አባሪ ፡ አስፈላጊ አድራሻዎች

*ይህ ዝርዝር ሁሉንም ያካተተ አይደለም፡*

## 1. ብሔራዊ አድራሻዎች

■ ተቋማት

**Office français de protection des réfugiés et apatrides (OFPRA)**
201, rue Carnot
94 136 FONTENAY-SOUS-BOIS CEDEX
ስልክ : 01 58 68 10 10
ፋክስ : 01 58 68 18 99
http://www.ofpra.gouv.fr/

**Cour nationale du droit d'asile (CNDA)**
35, rue Cuvier
93 558 MONTREUIL-SOUS-BOIS Cedex
ስልክ : 01 48 10 40 00
ፋክስ : 01 48 18 41 97
http://www.commission-refugies.fr/

**Office français de l'immigration**
**et de l'intégration (OFII)**
44, rue Bargue
75 015 PARIS
ስልክ : 01 53 69 53 70
ፋክስ : 01 53 69 53 69
http://www.ofii.fr

■ ዓለማ አቀፍ ድርጅት

**Haut-Commissariat des Nations-Unies**
**pour les Réfugiés (HCR)** Représentation en France
7, rue Henri Rochefort
75017 PARIS
ስልክ. : +33 (0)1 44 43 48 58
ፋክስ : +33(0)1 44 43 48 61
www.unhcr.fr/fr-fr

■ ማህበራት

**Association des chrétiens pour l'abolition**
**de la torture (ACAT)**
7, rue Georges Lardennois
75 019 PARIS
ስልክ : 01 40 40 42 43 / ፋክስ : 01 40 40 42 44
http://www.acatfrance.fr/

**Act'up**
9, rue des Dunes
75 019 PARIS

ስልክ : 01 75 42 81 25
http://www.actupparis.org/

**ARDHIS**
Centre LGBT Paris-Île-de-France,
63, rue Beaubourg, 75003 Paris
ስልክ : 01 43 57 21 47
https://ardhis.org/WP3/

**Amnesty International - section française**
72-76, boulevard de la Villette
75 019 PARIS
ስልክ : 01 53 38 65 65 / ፋክስ : 01 53 38 55 00
http://www.amnesty.fr/

**Association Primo Lévi**
107, avenue Parmentier
75 011 PARIS
ስልክ : 01 43 14 88 50 / ፋክስ : 01 43 14 08 28
http://www.primolevi.asso.fr/

**Association d'accueil aux médecins et personnels de santé réfugiés en France (APSR)**
Hôpital Sainte Anne
1, rue Cabanis
75 014 PARIS
ስልክ : 01 45 65 87 50 / ፋክስ : 01 53 80 28 19
http://www.apsr.asso.fr

**Comité d'aide exceptionnelle aux intellectuels réfugiés (CAEIR)**
43, rue Cambronne
75 015 PARISስልክ : 01 43 06 93 02 / ፋክስ : 01 43 06 57 04
**Centre d'action sociale protestant (CASP)**
20, rue Santerre

75 012 PARIS
ስልክ : 01 53 33 87 50 / ፋክስ : 01 43 44 95 33
http://www.casp.asso.fr

**CIMADE - Service œcuménique d'entraide**
91 rue Oberkampf
75011 PARIS ስልክ : 01 44 18 60 50 / ፋክስ : 01 45 56 08 59
http://www.cimade.org

**Comité médical pour les exilés (COMEDE)**
Hôpital de Bicêtre
78, rue du Général Leclerc
BP 31
94 272 LE KREMLIN BICÊTRE
ስልክ : 01 45 21 39 32 / ፋክስ : 01 45 21 38 41

http://www.comede.org

**Croix rouge française**
98 rue Didot,
75694 Paris Cedex 14 ስልክ : 01 44 43 11 00
ፋክስ : 01 44 43 11 01
http://www.croix-rouge.fr

**Fédération des associations de soutien aux travailleurs immigrés (FASTI)**
58, rue des Amandiers
75 020 PARIS
ስልክ : 01 58 53 58 53 / ፋክስ : 01 58 53 58 43
http://www.fasti.org

**Forum réfugiés**
28, rue de la Baïsse - BP 1054
69 612 VILLEURBANNE CEDEX
ስልክ : 04 78 03 74 45/ ፋክስ : 04 72 97 05 81
http://www.forumrefugies.org

**France Terre d'Asile (FTDA)**
24, rue Marc Seguin
75 018 PARIS
ስልክ : 01 53 04 39 99 / ፋክስ : 01 53 04 02 40
http://www.france-terre-asile.org

**Groupe accueil solidarité (GAS)**
17, place Maurice Thorez
94 800 VILLEJUIF
ስልክ : 01 42 11 07 95 / ፋክስ : 01 42 11 09 91
http://www.gas.asso.fr/

**Groupe d'information et de soutien des immigrés (GISTI)**
3, villa Marcès
75 011 PARIS
ስልክ : 01 43 14 60 66 / ፋክስ : 01 43 14 60 69
http://www.gisti.org

**Ligue des droits de l'homme (LDH)**
138, rue Marcadet
75 018 PARIS
ስልክ : 01 56 55 50 10 / ፋክስ : 01 56 55 51 21
http://www.ldh-france.org

**Mouvement contre le racisme et pour l'amitié entre les peuples (MRAP)**

43, boulevard Magenta
75 010 PARIS
ስልክ : 01 53 38 99 99 / ፋክስ : 01 40 40 90 98
https://www.mrap.fr/

**Secours catholique CEDRE**
23, boulevard de la Commanderie
75 019 PARIS
ስልክ : 01 48 39 10 92 / ፋክስ : 01 48 33 79 70
http://www.secours-catholique.asso.fr

**Service national de la pastorale des migrants (SNPM)**
58, avenue de Breteuil
75007 PARIS ስልክ : 01 73 36 69 47
https://migrations.catholique.fr/

## 2. የክልል አድራሻዎች

### ■ Guichets uniques(ጊሼ ኡኒክ)

AUVERGE-RHONE-ALPES
- Isère
  12 Place de Verdun, 38000 Grenoble
- Puy-de-Dôme

18 Boulevard Desaix, 63000 Clermont-Ferrand
- Rhône

106 rue Pierre Corneille, 69003 Lyon

BOURGOGNE-FRANCHE-COMTE
- Côte-d’Or

51 rue de la Préfecture, 21041 Dijon
- Doubs

8 bis rue Charles Nodier, 25035 Besançon
- Saône-et-Loire

196 rue de Strasbourg, 71000 Mâcon

BRETAGNE
- Ille-et-Vilaine

3 av. de la Préfecture, 35026 Rennes

CENTRE
- Loiret

181 rue de Bourgogne, 45042 Orléans

GRAND-EST
- Marne

38 rue Carnot, 51036 Châlons-en-Champagne
- Moselle

9 rue de la Préfecture, 57000 Metz

- Bas-Rhin

5 place de la République, 67073 Strasbourg

- Haut-Rhin

7 rue Bruat 68020 Colmar

HAUTS DE FRANCE

- Nord

12/14 rue Jean Sans Peur, 59039 Lille

- Oise

1 place de la Préfecture, 60000 Beauvais

ILE-DE-FRANCE

- Paris

92 boulevard Ney, 75018 Paris

- Seine-et-Marne

12 rue des Saints Pères, 77000 Melun

- Yvelines

1 rue Jean Houdon, 78000 Versailles

- Essonne

Boulevard de France, 91000 Evry

- Hauts-de-Seine

167-177 avenue Joliot Curie, 92000 Nanterre

- Seine-Saint-Denis

13 rue Marguerite Yourcenar, 93000 Bobigny

- Val-de-Marne

13/15 rue Claude Nicolas Ledoux, 94000 Créteil

- Val-d'Oise

5 avenue Bernard Hirsch, 95010 Cergy-Pontoise

NORMANDIE

- Calvados

Rue Daniel Huet, 14038 Caen

- Seine-Maritime

7 place de la Madeleine, 76000 Rouen

NOUVELLE-AQUITAINE

- Gironde

2 esplanade Charles de Gaulle, 33000 Bordeaux

- Vienne

Bâtiment Haussmann, Impasse des Ecossais, 86000 Poitiers

- Haute-Vienne

19 rue Cruveilhier, 87000 Limoges

OCCITANIE

- Haute-Garonne

1 place Saint-Etienne, 31038 Toulouse

- Hérault

34 place des Martyrs de la résistance, 34000 Montpellier

PROVENCE-ALPES-COTE D'AZUR

- Alpes-Maritimes

17 bd du Mercantour 06200 Nice

- Bouches-du-Rhône

66 bis Rue Saint-Sébastien, 13006

PAYS-DE-LA-LOIRE

- Loire-Atlantique

6 quai Ceineray, 44035 Nantes

- Maine-et-Loire

Place Michel Debré, 49934 Angers

OUTRE-MER (services « asile » des préfectures)

- Martinique

Rue Victor Sévère, 972000 Fort-de-France

- Guadeloupe

Grand camp, Immeuble situé à côté de la SIG, 97139 Abymes

- Guyane

23 rue Arago, 97300 Cayenne

- La Réunion

6 rue des Messageries, CS 51079 97404 Saint Denis Cedex

- Mayotte

BP 979 97600 Mamoudzou.

## ■ Préfectures (ፕሬፈክቱር)

ALSACE

- Haut-Rhin
  7, rue Bruat, 68 020 Colmar
- Bas-Rhin
  5, place de la République, 67 073 Strasbourg

AQUITAINE

- Gironde
  2, esplanade Charles de Gaulle,
  33 000 Bordeaux
- Dordogne
  2, rue Paul Louis Courier, 24 000 Périgueux
- Landes
  24, rue Victor Hugo, 40 021 Mont-de-Marsan
- Lot-et-Garonne
  Place de Verdun, 47 920 Agen

• Pyrénées-Atlantiques
2, rue du maréchal Joffre, 64 021 Pau

AUVERGNE
• Puy-de-Dôme
18, boulevard Desaix,
63 000 Clermont-Ferrand
• Allier
2, rue Michel de l'Hospital, 03 000 Moulins
• Cantal
2, cours Monthyon, 15 000 Aurillac
• Haute-Loire
6, avenue du Général de Gaulle
43 000 Le Puy-en-Velay

BOURGOGNE
• Saône-et-Loire
196, rue de Strasbourg, 71 000 Mâcon
• Nièvre
40, rue de la Préfecture, 58 000 Nevers
• Yonne
Place de la Préfecture, 89 000 Auxerre
• Côte d'Or
53, rue de la Préfecture, 21 041 Dijon

BRETAGNE
• Ille-et-Vilaine
3, avenue de la Préfecture, 35 026 Rennes
• Côtes d'Armor
1, place Général de Gaulle, 22 000 Saint-Brieuc
• Finistère
42, boulevard Dupleix, 29 000 Quimper
• Morbihan
24, place de la République, 56 000 Vannes

CENTRE
• Loiret
181, rue de Bourgogne, 45 042 Orléans
• Cher
Place Marcel Plaisant, 18 000 Bourges
• Eure-et-Loir
Place de la République, 28 000 Chartres
• Indre
Place de la Victoire et des Alliés,
36 000 Châteauroux
• Indre-et-Loire
15, rue Bernard Palissy, 37 925 Tours

- Loir-et-Cher
  Place de la république, 41 000 Blois

CHAMPAGNE-ARDENNE
- Ardennes
  Esplanade du Palais de Justice,
  08 000 Charleville-Mézières
- Aube
  2, rue Pierre Labonde, 10 000 Troyes
- Haute-Marne
  89, rue Victoire de la Marne,
  52 011 Chaumont

- Marne
  38, rue Carnot,
  51 036 Châlons-en-Champagne

FRANCHE-COMTE
- Doubs
  8, bis Rue Charles Nodier, 2 5035 Besançon
- Jura
  8, rue de la Préfecture, 3 9000 Lons-le-Saunier
- Haute-Saône
  1, rue de la Préfecture, 70 013 Vesoul
- Territoire de Belfort
  Place de la République, 90 000 Belfort

GUADELOUPE
- Palais d'Orléans, Rue Lardenoy,
  97 109 Basse-Terre 97109, Guadeloupe

ILE-DE-FRANCE
- Paris : 92, boulevard Ney, 75 018 Paris
- Seine-et-Marne
  12, rue des Saints Pères, 77 000 Melun
- Yvelines
  1, rue Jean Houdon, 78 000 Versailles
- Essonne
  Boulevard de France, 91 000 Evry
- Hauts-de-Seine
  167-177, avenue Frédéric et Irène Joliot Curie, 92 000 Nanterre
- Seine-Saint-Denis
  1, esplanade Jean Moulin, 93 007 Bobigny
- Val-de-Marne
  21-29, avenue du Général De Gaulle,
  94 038 Créteil cedex

• Val d'Oise
5, avenue Bernard Hirsch, 95 010 Cergy-Pontoise

LANGUEDOC-ROUSSILLON
• Hérault : 34, place des Martyrs de la résistance, 34 000 Montpellier
• Aude : 52, rue Jean Bringer,
11 000 Carcassonne
• Gard : 10, avenue Feuchères, 30 000 Nîmes
• Lozère : rue du faubourg Montbel,
48 005 Mende
• Pyrénées-Orientales : 120, avenue Emile Roudayre, 66 000 Perpignan

LIMOUSIN
• Corrèze : 1, rue Souham, 19 000 Tulle
• Creuse : 4, place Louis Lacrocq, 23 000 Guéret
• Haute-Vienne : 1, rue de la Préfecture,
87 000 Limoges

LORRAINE
• Moselle : 9, place de la Préfecture
570 00 Metz
• Meuse
40, rue du Bourg, 55 000 Bar-le-Duc
• Meurthe-et-Moselle
1, rue Préfet Claude Erignac, 54 000 Nancy
• Vosges : Place Foch, 88 026 Epinal

MIDI-PYRENEES
• Haute-Garonne
1, place Saint-Étienne, 31 038 Toulouse
• Ariège
2, rue de la préfecture Préfet Claude Erignac, 09 000 Foix
• Aveyron
7, place Général de Gaulle, 12 000 Rodez
• Gers
7, rue Arnaud de Moles, 32 000 Auch
• Lot
Cité Bessières, Rue Pierre Mendes France, 46000 Cahors
• Hautes-Pyrénées
Place du Général de Gaulle, 65 000 Tarbes
• Tarn
Place de la Préfecture, 81 013 Albi
• Tarn-et-Garonne
2, allée de l'Empereur, 82 013 Montauban

NORD-PAS-DE-CALAIS
• Nord
12/14, rue Jean sans Peur, 59 039 Lille

• Pas-de-Calais
9, esplanade Jacques Vendroux, 62 100 Calais

BASSE-NORMANDIE
• Calvados
Rue Daniel Huet, 14 038 Caen cedex 09
• Manche
Place de la Préfecture, 50 002 Saint-Lô
• Orne
39, rue Saint-Blaise, 61 018 Alençon

HAUTE-NORMANDIE
• Seine-Maritime
7, place de la Madeleine, 76 000 Rouen
• Eure
Boulevard Georges Chauvin, 27 000 Evreux

PAYS DE LOIRE
• Loire-Atlantique
6, quai Ceineray, 44 035 Nantes
• Vendée
29, rue Dellile, 85 009 La Roche-sur-Yon
• Maine-et-Loire
Place Michel Debré, 49 934 Angers
• Mayenne
46, rue Mazagran, 53 015 Laval
• Sarthe
Place Aristide Briand, 72 041 Le Mans

PICARDIE
• Oise
1, place de la Préfecture, 60 000 Beauvais
• Aisne
27, rue Paul Doumer, 02 000 Laon
• Somme
51, rue de la République, 80 000 Amiens

POITOU-CHARENTES
• Charente
7-9, rue de la Préfecture, 16 023 Angoulême
• Charente-Maritime
38, rue Réaumur, 17 000 La Rochelle
• Deux-Sèvres
4, rue Duguesclin, 79 099 Niort
• Vienne
7, place Aristide Briand, 86 000 Poitiers

PROVENCE-ALPES-COTE-D'AZUR

- Bouches-du-Rhône
  66 bis, rue Saint-Sébastien, 13 006 Marseille
- Vaucluse :
  28, boulevard Limbert, 84 000 Avignon
- Alpes-Maritimes
  147, boulevard du Mercantour, 06 200 Nice
- Alpes-de-Haute-Provence
  Avenue Demontzey, 04 002 Digne les Bains
- Hautes-Alpes
  28, rue Saint-Arey, 05 000 Gap
- Var
  Boulevard du 112e régiment d'infanterie,
  83 070 Toulon

RHONE-ALPES
- Isère
  12, place de Verdun, 38 000 Grenoble
- Savoie
  Château des Ducs de Savoie,
  73 018 Chambéry
- Haute-Savoie
  Rue Louis Revon, 74 000 Annecy
- Rhône
  106, rue Pierre Corneille, 69 003 Lyon
- Ain
  4,5 avenue Alsace Lorraine, 01 012 Bourg en Bresse
- Ardèche
  5, rue pierre Filliat, 07 000 Privas
- Drôme
  3, boulevard Vauban, 26 000 Valence
- Loire
  2, rue Charles de Gaulle, 42 022 Saint-Etienne

## ■ Directions territoriales de l'Office français de l'immigration et de l'intégration (OFII)

Direction centrale
44, rue Bargue
75 732 Paris Cedex 15
ስልክ : 01 53 69 53 70

Amiens (02, 60, 80)
275, rue Jules Barni – Bât. D
80 000 Amiens
ስልክ : 03 22 91 28 99 / amiens@ofii.fr

Besançon (25, 70, 39, 90)
3, avenue de la Gare d'Eau
25 000 Besançon
ስልክ : 03 81 25 14 39 / besancon@ofii.fr

Bobigny (93)
13, rue Marguerite Yourcenar
93 000 Bobigny
ስልክ : 01 49 72 54 00 / Seine-saint-denis@ofii.fr

Bordeaux (24, 33, 40, 47,6 4)
55, rue Saint Sernin,
33 002 Bordeaux Cedex
ስልክ : 05 57 14 23 00 / bordeaux@ofii.fr
Caen (14, 50, 61)
Rue Daniel Huet
14 038 Caen Cedex 9
ስልክ : 02 31 86 57 98 / Caen@ofii.fr

Cayenne (973
17/19, rue Lalouette BP 245
97 325 Cayenne
ስልክ : 05 94 37 87 00 / cayenne@ofii.fr

Cergy (95)
Immeuble « Ordinal » Rue des Chauffours,
95 002 Cergy Pontoise Cedex
ስልክ : 01 34 20 20 30 / cergy@ofii.fr

Clermont-Ferrand (03, 15, 63, 43)
1, rue Assas
63 033 Clermont Ferrand
ስልክ : 04 73 98 61 34 / Clermont-ferrand@ofii.fr
Créteil (91, 94)
13/15, rue Claude Nicolas Ledoux
94 000 Créteil
ስልክ : 01 41 94 69 30 / creteil@ofii.fr

Dijon (21, 58, 71, 89)
Cité administrative Dampierre
6, rue du Chancelier de l'Hospital
21 000 Dijon
ስልክ : 03 80 30 32 30 / dijon@ofii.fr

Grenoble (74, 38, 73
Parc Alliance - 76, rue des Alliés
38 100 Grenoble

ስልክ : 04 76 40 95 45 / grenoble@ofii.fr

Lille (59, 62)
2, rue de Tenremonde
59 000 Lille
ስልክ : 03 20 99 98 60 / lille@ofii.fr

Limoges (23, 19, 87)
19, rue Cruveihier
87 000 Limoges
ስልክ : 05 55 11 01 10 / limoges@ofii.fr

Lyon (01, 07, 26, 42, 69)
7, rue Quivogne
69 286 Lyon Cedex 02
ስልክ : 04 72 77 15 40 / Lyon@ofii.fr
Marseille (13, 20, 04, 05, 83, 84)
61, boulevard Rabatau
13 295 Marseille Cedex 08
ስልክ : 04 91 32 53 60 / Marseille@ofii.fr

Antenne Mayotte OFII (976)
N15 Espace Coralium, RN1 – CS 80058 Kaweni, 97 600 Mamoudzou
ስልክ : 02 069 62 23 54 / mayotte@ofii.fr

Melun (77)
2 bis, avenue Jean Jaurès
77 000 Melun
ስልክ : 01 78 49 20 00 / Melun@ofii.fr

Metz (54, 55, 57, 88)
2, rue Lafayette
57 000 Metz
ስልክ : 03 87 66 64 98 / metz@ofii.fr

Montpellier (30, 34, 48, 66)
Le Régent - 4, rue Jules Ferry
34 000 Montpellier
ስልክ : 04 99 77 25 50 / montpellier@ofii.fr

Montrouge (92, 78)
221, avenue Pierre Brossolette
92 120 Montrouge
ስልክ : 01 41 17 73 00 / montrouge@ofii.fr

Nantes (44, 53, 49, 72, 85)
93 bis, rue de la Commune de 1871
44 400 Rezé

ስልክ : 02 51 72 79 39 / nantes@ofii.fr

Nice (06)
Immeuble SPACE- Bât. B
11, rue des Grenouillères
06 200 Nice
ስልክ : 04 92 29 49 00 / nice@ofii.fr

Orléans (18, 28, 36, 37, 45, 41)
4, rue de Patay
45 000 Orléans
ስልክ : 02 38 52 00 34 / orleans@ofii.fr

Paris (75)
48, rue de la Roquette
75 11 Paris
ስልክ : 01 55 28 19 40 / paris@ofii.fr

Pointe-à-Pitre (971, 972)
Immeuble Plazza - Boulevard Chanzy
97 110 Pointe à Pitre
ስልክ : 05 90 90 01 83 / guadeloupe@ofii.fr

Poitiers (16, 17, 79, 86)
86, avenue du 8 Mai 1945
86 000 POITIERS
ስልክ : 05 49 62 65 70 / reims@ofii.fr

Reims (08, 10, 51, 52)
26/28, rue Buirette
51 100 Reims
ስልክ : 03 26 36 97 29 / reims@ofii.fr

Rennes (22, 29, 35, 56)
8, rue Jean Julien Lemordant
35 000 Rennes
ስልክ : 02 99 22 98 60 / rennes@ofii.fr

La Réunion (974)
Préfecture de la Réunion, Place du Barachois
97 405 Saint Denis Cedex
ስልክ : 02 62 40 75 69 / ofii-reunion@ofii.fr

Rouen (27,76)
Immeuble Montmorency 1
15, place de la Verrerie
76 100 Rouen
ስልክ : 02 32 18 09 94 / rouen@ofii.fr

Strasbourg (67,68)
4, rue Gustave Doré - CS 80115
67 069 Strasbourg Cedex
**ስልክ** : 03 88 23 30 20 / strasbourg@ofii.fr

Toulouse (09, 12, 19, 23, 32, 31, 65, 87, 46, 81, 82)
7, rue Arthur Rimbaud, CS 40310
31 203 Toulouse Cedex2
**ስልክ** : 05 34 41 72 20 / toulouse@ofii.fr